ጎልቶ አልወጣም:: የተረጋጋ ነገር የላትም:: ቴዎድሮስ አቤት ባለመኖሩ እንጂ እንዲህ ሰትሆን የእሱ መኖር ብዙ ነገር ያቀልላታል:: እህቶቿ ይዘውት የት እንደ ሄዱ አላወቀችም:: ቀና ብላ አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ አለች:: እንደ አገዳ ቀጥ ብለው የወጡትን እግሮቿን አገጣጥማ በመጠኑ ብድግ አደረገቻቸው:: የሌላ ሰው እግር እንደምታይ ሁሉ ትኩር ብላ ተመለከተቻቸው:: እንደ ዱሮው ውበታቸው አልሳባትም ወደታች አወረደቻቸውና እንደ ገና ዐይኖቿን በመስኮቱ ወደ ውጭ ላከቻቸው:: ሰልቂሳ ማርያም ቤተክርስቲያንን የከበበው ደን ተቀበላት:: ደኑ የማታ ፀሐይ እርፎበት በራሱ ጥላ ጠቆር ብሏል::

ገና ልጅ---ገና ተማሪ እያለች ጀምሮ ቤተክርስቲያኗን ታውቃታለች:: በዚያ የልጅነት ጊዜዋ ከጓደኞቿ ጋር ሰልቂሳ ማርያም ቤተክርስቲያን ደጋግማ ሄዳለች:: ለጽድቅ ሳይሆን የሰንበት መከፈልት ቂጣ ለማግኘት:: እሷና ጓደኞቿ የጸሎቱን የመጨረሻ ሰዓት በጉጉት እየናፈቁ ይጠብቁ ነበር:: በእለቱ ተረኛ መነኩሲት እንደ እድል የሚታደለው የሰንበት መከፈልት ቂጣ ቱልቁ እንዲደርሳቸው እየጸለዩ:: ጸበልም ይታደላል:: አንትሩፋት ግን ለእሱም ቢሆን አይጓጉም::ዐይናቸው የሚያርፈው መከፈልቱ ላይ ብቻ ነበር:: እሱንም ቢሆን ለበረከትነቱ አስበው አይደለም:: ጣሙን ይወዱታል:: በልተው አይጠግቡትም:: በአንዲት በጎ ፍቃደኛ መነኩሴ ባለቀ ጉልበት በየመንደሩ ዱቄት ተለምኖ የሚጋገረው የሰንበት ቂጣ ጣዕሙ ልዩ ነው:: ሀና ማርያም ቤተክርስቲያን ብዙ ሰው ስለሚሄድ መከፈልቱ ያንሳል:: የሰልቂሳ ማርያሙ ግን ትልልቅ ነው:: ውሻ በቁልቁለት አይጎትተውም:: ለዚያ ነበር ያን ሁሉ የእግር መንገድ አቋርጠው መሄዳቸው:: ዳገት መውጣታቸው- ቁልቁለት መውረዳቸው::

ትሩፋት ከጓደኞቿ ጋር ሰልቂሳ ማርያም ቤተክርስቲያን አይደለም የትም ለመሄድ የእንጀራ እናቷን ፈቃድ ማግኘት ይጠበቅባት ነበር:: በልጅነት ጊዜዋም እንደ ፈለገችው የትም የመሄድ መብት አልነበራትም:: ዛሬ ደግሞ ራሷን ችላ ካሰበችው ቦታ እንደ ፈለጋት ብድግ ብላ የትም መንቀሳቀስና መሄድ አትችልም:: ቤተክርሲያን መሄድ የሶሻሊዝምን መርህ መቃወም ሰለሆነ ያስጠቁራል:: በዚያም ላይ እሁድ እሁድ የአብዮታዊ ንቃቱ ስብሰባ የትም አያሰናዝርም:: እስረኛ ባሏን እንኳ ለመጠየቅ ሰንት ሰቃይ ታያለች::

የሶሻሊዝንምን ርዕዮተ-ዓለም እንደ መቃወም ባይቆጠርባት ኖሮ ዛሬ ሰልቂሳ ማርያም ቤተክርስቲያን መሄድ አሰኝቷት ነበር:: እንደ ልጅነቷ ጊዜ ለትልቅ መከፈልት ብላ አይደለም:: ከከተማ ወጣ ብሎ ጭልል--ጸጥ--ረጭ ያለ ቦታ ፍለጋ:: ፀጥታ በነገሰበት በዚያ የሰልቂሳ ማርያም ቤተክርስቲያን ተራራማ ቦታ በመንፈስ ሰማዬ ለማየት ለመድረስ:: አዋኪ ሳይኖር ለብቻ ከፈጣሪ ጋር የልብን ለመነጋገር--- በጣም አብዝታ ልትማልድለት የምትፈልገው ብዙ ነገር ነበራት:: የዚችን አገር እጣ ፈንታ ለምን ሲኦልና መከራ ብቻ እንዳደረገው እሱን እንድዬን ለመጠየቅ:: የሕዝቡን መከራ እንዲያሳጥረው ለመማለድ:: በዚያች የሳር ጣሪያዋ በወጉ ባልተከፈከፈ፣ ግድግዳና ማገሩዋ በደንብ ተዋቅሮ ምርግ



ባልተመረገች የሳር ጎጆ ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ብትገኝ ትወዳለች:: እነዚያ የኑሮ ጫና ያደቀቃቸው ገበሬ ቀሳውስት ልማዳዊውን የኦርቶዶክስ ሐይማኖት ስነስርዓት በወጉ ያካሂዳሉ:: የተዋበ ሕንጻ ኖሯት ዓይን ባታማልልም መንፈስን የሚመስጥ የቅዳሴ ዜማ ይንቆረቆርባታል:: እጣን ይታወድባል:: ይሄ ሁሉ መንፈስን ገዝቶ የሚይዝ እንዳች ኃይል ያለው ይመስላታል ትሩፋት:: ዙሪያዋን ከብብ አድርጎ የያዛት ጫካ ለፀሎቱ ግዝፈት ይሰጠዋል:: ራስን ዝቅ አድርጎ ለፈጣሪ ማስገዛትን ያለፍናል የሰልቂሳ ማርያም ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ::

ትሩፋት ላስቲክ በለበሰው መስኮቷ አሻግራ እየተመለከተች የተመኘችው ነገር ቢኖር ከዚህ ከሰልቂሳ ቤተክርስቲያን ጫካ ውስጥ መሆንን ነበር:: ፀሐይ ማደርያዋን ልትይዝ የቸኮለች ይመሰል ቶሎ ድንግዝግዝ አለ:: ትሩፋት ዐይኗን ከሰልቂሳ ማርያም ጫካ ላይ ሳትነቅል መተከዟን ቀጠለች::

«እንስሳት በልጠውናል:: እድሜ ልካቸውን በማይናወጥ የተፈጥሮ ሕግ ተገዝተው ኖረው ይሞታሉ:: የሰው ልጅ አወቅሁ----ነቃሁ --- በቃሁ--- ተመራመርሁ የሚለው-- ተሞኝቷል:: እርግጥ ነው ተፈጥሮን በቁጥጥር ስር ለማዋል ጥሯል:: በራሱ ሕግ ለመገዛት ያላሰለሰ ሙከራ አድርጓል:: እውነት ነው የሰው ልጅ በረቀቀ አእምሮው ብዙ ግኝቶችን አግኝቷል:: ኑሮውን የሚያቀሉለት አስገራሚ ሰራዎችን ሰርቷል:: ይኸ ሁሉ ሆኖ ግን እድሜውን ሙሉ ሳይረካ እንደ ባከነ ይሞታል:: ምክንያቱም ምንም ዓይነት ዋጋ የማይጠይቁትንና የማያስከፍሉትን ግን ለኑሮው ደስታ፣ እርካታና ሰላም የሚሰጡትን እጅግ ውብ ነገሮች ዘንግቷል ወይም አውቆ ትቷቸዋል:: ፍቅርና ሰላምን-- መተሳሰብና መተዛዘንን--- ተቻችሎና ተስማምቶ መኖርን ከሕይወቱ ገፍትሮ አውጥቷቸዋል:: እያወቀ-- አውቆ ወደ ጎን ገፍቷቸዋል:: ለዚህም ዋጋ እየከፈለ ይገኛል:: ደስታ ርቆታል:: ሰላሙ ጠፍቷል:: በምንም ነገር የማይረካ ሆኗል:: ጸጋ ርቆት በስጋት፣ በጭንቀትና በመከራ ውስጥ ራሱን ከቶ ይኖራል:: ከዚህ የበለጠ ቅጣት ምን አለ?

የሰው ዘር በሙሉ በዚች ዓለም እስካለ ድረስ ተስማምቶ ቢኖር-- በውስጧ ያለውን ሀብት እኩል ተካፍሎ ቢጠቀም---እስከ እለተ ሞቱ በፍቅርና በሰላም አብሮ ቢኖር--- አቤት! ዓለም እንዴት ውብ በሆነች ነበር:: የሰው ልጅ ሰለጠንኩ ብሎ ጨረቃን ቢረግጥ-- ማርስ ላይ ቢወጣ ፍቅር፣ ሰላም፣ ደስታና እርካታ ካላገኘበት ምን ያደርግለታል? ምንስ ይጠቅመዋል? ፍቅር--- ሰላም---ደስታና እርካታ ከሌለው ሰማየ ሰማያት ከደረሰ ፎቅ ውስጥ ቢኖር ፋይዳው ምንድን ነው? የሰው ዘር በሙሉ ምን ነከቶን ይሆን? አብረን ተከባብረን፣ ተዋደንና ተፋቅረን ተፈጥሮ የለገሰችንን በረከት እኩል መቋደስ ያቃተን...» እያለች ያው ዞሮ ዞሮ የነገሯ ሁሉ ማሳረጊያ ወደሆነው ከንቱ የትግል ጊዜ ተመሰሰች:: የዚያ ሁሉ ወጣት እልቂት--ያ ሁሉ ትኩስ ጉልበት ያለው እምራች ዜጋ ወህኒ ቤት ተከርችሞበት በከንቱ ጊዜው መንጎዱ ቆጫት:: እንዲህ እዝን ብላ ማስቂያ በሌለው ጥያቄና ምርምር ውስጥ ገብታ ስትባዝን

«አትዬ ልጆቹ ቀሩ:: ሳንቺ መከለስ ነገር ላቅርብልሽ?» የልጅ አግሯ ሰራተኛ ድምጽ መቋጫ ከሌለው ትካዜዋ ገላገሳት:: ቀኑብሽ ቅልጥፍጥፍ ያለች ኮረዳ ናት:: ቶሎ ቶሎ ማኩረፏ ነው እንጂ ስራዋ አንጀት ያርሳል:: አሁን ሰው አሁን አፈር የሚያደርጋት አመሏ ግን ሰው ያሰቅቃል:: ትሩፋትማ እሷ ባኮረፈች ቁጥር የገዛ ቤቷ ልትገባበት ያስጠላታል:: መጨረሻ ሳይም የተለያዩት በዚሁ አኩራፊ ባህሪዋ የተነሳ ነበር::

«አሁንማ የአራት ሰዓት ደረሰ አይደል ቀኑ:: ልጆቹ ሊመጡ አብረን ብንበላ ይሻላል» አለች ትሩፋት::

«አንግዲያው የአግር ውሃ እሙቄልሻለሁ እስካዚያ እግርሽን ታጠቢ» ብላ ውሃውን ለማምጣት ወደ ኩሽና ተመለሰች:: ሲያሰኛት ትሩፋት እምቢ ብትላት እንኳ በግድ እግሯን ጎትታ አሸት አድርጋ ታጥባታለች:: በባዝሊን ማሸቱንም ትችልበታለች:: እንዲህ ስታደርግ ታዲያ «ባይመጡ» ትላታለች ትሩፋት:: ቀኑብሽ ትስቃለች:: ስትስቅ ጉርድርድ ያለው ቀይ ፊቷ ሁሉ ይስቃል:: ትንንሽ አይኖቿ ጥፍት ይላሉ:: ደስ ትላለች::

«ደህና አመሻችሁ ቤቶች? አናትሽ አለች?» እልፍነሽ ነበረች:: ከትሩፋት ጋር ጎረቤታሞች ናቸው::

«እግዜር ይመስገን:: እዎ እለች ግቢ አትዬ አልፍነሽ» አለች ቀኑብሽ::

«ምን እያደረገች ነው? ይህንጊዜ እዚያው አይደከም አልጋዋ ላይ ተጋድማ ይሆናል» አለች እልፍነሽ:: ትሩፋት የምትታወቀው የሚነበብ መጽሐፍ ይዛ አልጋ ሳይ ጋደም በማለቷ ነው:: አቤት ውስጥ ካለች መገኛዋ አልጋ ሳይ ነው::

«ይህዋ አላልኩም። ኧረ የአልጋውም ጡር አለው:: ቀንም ለሊትም ስትተኚበት ድምጽ ባያሰማም ወደ ፈጣሪው አቤት! ማለቱ አይቀርም» አለች እልፍነሽ ወደ ውስጥ እየዘለቀች::

«ደህና አመሸሽ አልፍዬ?» እለች ትሩፋት ተነስታ ወደ ሳሎን እየመጣች:: ተያይዘው ሶፋው ላይ ተቀመጡ:: አዲስ ዘመን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አንድ ላይ ያስተምራሉ:: በዚያ ላይ ቡና የሚጣጡ ጎረቤታሞች ናቸው:: ይበልጥ የሚያቀራርባቸው ግን ሁለቱም የዚያች ከንቱ ድርጅት አባል የነበሩ በመሆናቸው ነበር:: ከዚህም ሌላ ሁለቱም ብቸኛ የቤተሰብ ኃላፊዎች ናቸው:: የትሩፋት ባለቤት ይነበብ ባህርዳር ወህኒ ቤት ታስሮ እየማቀቀ ይገኛል:: የእልፍነሽ ባለቤት ወርቁ ደግሞ ሁለት ልጆችን ካፈሩ በኋላ ሚስቱንና ልጆቹን ትቶ ለትጥቅ ትግሉ ሜዳ የወጣ ሰው ነበር:: ሁሉም ምህረት እየጠየቀ ሊገባ እሱ ግን እስካሁን አልተመለሰም:: የትሩፋት ወንድም ድልነሳም እንዲሁ:: ይህም እርስ በርስ እንዲተዛዘኑና እንዲቀራረቡ ምክንያት ሆኗል::

«እልፍዬ ቡና ይፈላ አይደል?» አለች ትሩፋት::





«የንፍገት ካልሆነ በስተቀር እንደ በሽተኛ ለምን ትጠይቂኛለሽ? አንቺ እንደ ሆንሽ ለቡና ግድ የለሽም:: አድባሯም ያሰኛታል አትይም:: ይልቅስ አነራሔል ቴዲን ይዘው እኛ ቤት እየተጫወቱ ነው:: ጭልል ብሎልኝ ሳለ እንዲፈላ ነው ሹልከ ብዬ የመጣሁ:: ቀኑብሽን ጥሪያት ቶሎ የቡና እቃዋን ታቀራርብ» አለች እልፍነሽ:: የቡና ነገር አይሆንላትም:: ሲበዛ ሰብኛ ናት::

«ጊዜው ገፍቷል ብዬ እንጂ እኔማ ስንጫወት ብናመሽ ደስታውን ችየው ነው አልፍዬ» አለች ትሩፋት::

«አመሸሽ ብሎ የሚቆጣ ባል የለብኝ:: እንኳን ማምሸት ባድርስ ማን ተቆጣጣሪ አለብኝ መሰለሽ ትሩፌ እያወቅሽ:: እድሜ ለደርግ መንግሥት! እድሜ ለአብዮት! ትዳሬ ፈርሷል» ብላ እንባዋ በዐይኗ ግጥም አለ:: ዞራ ዞራ የወሬዋ መቋጫ የባለቤቷ ወጥቶ መቅረት ነው:: ትንሽ ቆይታ ደግሞ እንባ ማስከተሏ የተለመደ ነገር ሆኗል::

«እልፍዬ በዚህ ጉዳይ ላይ ስንት ጊዜ እንነጋገር? ማን ያውቃል? የወርቁን መኖር አንድ ቀን ትሰሚ ይሆናል:: ሁሉም ታጋይ ምህረት ጠይቆ አልገባም ወደ ሱዳንና ወደ ሌላው አለም የተሰደደው ታጋይ ብዙ ነው ይባላል:: እኔስ የአንዱን ወንድሜን የድልነሳን ሞት ሽረት መቼ አወቅሁ:: አንደእኔና አንቺ የሚወዷቸውን ያጡ ብዙ ኢትዮጵያዊያን መኖራቸውን አስቢ» አለች ትሩፋት:: እየተቆጣቻትም---እያጽናናቻትም::

«የማዝነው ወርቁ ቀረብኝ ብዬ መስሎሽ ከሆነ ተሳስተሻል:: የማዝነው ለልጆቼ ነው:: ታሪክ ስለሌለው አባታቸው ሳስብ ምን ብዬ እንደምነግራቸው ይጨንቀኛል:: ሞቶም ከሆነ የተሰዋለት-- ተሰዶም ከሆነ የተሰደደለት ድርጅት እንዲህ ተንኮታኩቶ ታሪክ አልባ ሆኖ መቅረቱ ነው የሚያንገበግበኝ:: ለልጆቼ ስለአባታቸው እንዲህ ነው ብዬ የምተርከለት ታሪክ አለመኖሩ ነው የሚቆጨኝ::»

«ይገባኛል አልፍዬ:: በዚያ የትግል መስከ ለተሳተፍን ሁሉ የማይሽር ቁስል ነው:: በአንቺ ላይ ብቻ የተከሰተ አይደለም:: ሆኖም ግን ዓላማችን ግቡን መትቶ ያሰብነው ባይሳካም ለኢትዮጵያ ጭቁን ሕዝብ በጎ አሰቦ--- በጎ አልሞ-- ብሩህ ራዕይ ለንቆ ድንቅ ታሪክ ሊሠራ ቆርጦ የተነሳ ትውልድ አካል ነበርን:: በዚህ ልትጽናኚና ልትኮሪ ይገባል» አለች ትሩፋት::

«አስኪ አስቢው ትሩፌ፤ አባታችሁ የታገለውና የሞተው እናንተ ፍትህ፣ ዲሞክራሲና እኩልነት በሰፈነባት ነጻ በሆነች አገር ውስጥ እንድትኖሩ ነበር ግን -- ብዬ የምቀጥለው ታሪክ ምንድን ነው? «ነበር ግን ሳይሳካ ቀረ» ብዬ ነው የምነግራቸው:: ከንቱ የሆነ ታሪክ ብተርከላቸው እነሱስ እንዴት ያምኑኛል? ለዚህ ነው ታሪክ አልባው ወርቁ የሚያስለቅሰኝ» አለች አልፍነሽ:: እንባዋ መንታ መንታ ሆኖ እየወረደ:: ቀኑብሽ የቡና እቃዋን

አቀራረበች:: ፍሙ ትርከከ ያለው የምድጃው እሳት ቤቱን አሞቀው:: እጣኑን በለል አደረገችው:: መቼም ያ መናጢ ኩርፊያዋ ባይመጣ ታውቅበታለች:: ቤቱ ሕይወት ዘራ::

«ብፈጠረሽ እልፍዬ ሁሉንም ነገር ለእግዜር እንስጠውና ጊዜ ይፈታው ይሆናል:: መቼም እምባገነኑ የደርግ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እንዲህ እንደ ተጫወተ ለዘለዓለም አይኖርም እመኚኝ:: አሁን ያስፈላሽውን ቡና በሰላም እንጠጣ» አለች ትሩፋት:: እልፍነሽ የባለቤቷን የወርቁን ሁኔታ ካነሳች እልቅሳ አታባራም:: ሰው ታስጨንቃለች::

«ምን ሳድርግ ብለሽ ነው ትሩፌ የቀለለኝ እየመሰለኝ እኮ ነው:: ከአንቺ ሌላስ ለማን አተነፍሰዋለሁ መሰለሽ-- እሺ በቃ!» ብላ እየተነፋረቀች እንባዋን ጠራረገች:: ትሩፋት ወደ ደረቷ አስጠግታ አቀፈቻት:: ልቦቻቸው የጋራ ሰቃያቸውን ተጋሩ::

******

ኢሕአፓ ስትፈራርስ ምህረት እየጠየቀ የገባው ሰው ሁሉ ቀድሞ ትቶት የሄደውን የሕይወት መንገዱን ቀጥሏል:: ተማሪ የነበረው ትምህርቱን ጀምሯል:: የመግሥት ሠራተኛ ሆኖ ኮብልሎ የነበረው ታጋይ ከጥቂት ውጣ ውረድ በኋላ ጥሎት የሄደውን የደመወዝ ስኬል እየያዘ ሥራውን ቀጥሏል:: ስደትን ምርጫዉ ያደረገው ታጋይ ደግሞ ከተሰደደበት አገር ሆኖ ድምጹን ማሰማት ጀመሯል:: ትርፋት ከድልነሳ ደብዳቤ ደርሷት ከፖስታ ቤት ደብዳቤውን ወስዳ ከቤት እስከትደርስ እንኳ አላስችል ብሏት መንገድ ላይ ነበር የከፈተችው::

ለውድ እህቴ ትሩፋት ማንያዘዋልና በአጠቃላይ ለመላ ቤተሰቡ! እንደምን አላችሁልኝ? እኔ ስደተኛው ወንድማችሁ ሱዳን ውስጥ በሕይወት አገኛለሁ:: ትሩፌ እስከዛሬ ያላወቅሁት ነገር ለካ ናፍቆትን በቃላት ማስቀመጥ እንዲህ ይከብድ ኖሯል! እንዴት መግለጽ እንዳለብኝ ግራ ገባኝ:: ምን አለፋሽ ሁላችሁም ዐይኔ ውስጥ በቅላችሁ ዐይኔ ውስጥ አላችሁ::

ትሩፌ! በሕይወት መኖሬን ሳሰበው የሚያስደሰተኝ ከእናንተ ጋር የመገናኘት ተስፋ ያለኝ መሆኑን ሳሰበው ነው:: አንቺን ሳስብ ደግሞ ከልጅነት የጀመርሽ ለእኛ ስትይ በተሰባበረ ጠርሙስ ላይ የሄድሽ ያህል ሆኖ ይሰማኛል:: ለዚህ አባባሌ አንድ ምሳሌ ላስታውስሽ:: አንድ ቀን ሦስታችንም የትምህርት ቤት ሰዓት ረፍዶብን ደረሰን:: መምህሩ አለንጋቸውን ይዘው አርፋጁን ሁሉ ይቀጣሉ:: የእኔና የራሔል ተራ ሲደርስ እጅሽን ዘርግተሽ አፈታቸው ቆምሽ:: በእኛ ፈንታ አንቺ ልትገረፊልኝ መፈለግሽንን ስትነግሪያቸው ትኩር ብለው ተመለከቱሽና 'ትሩፋት አንቺም እንደ ክርስቶስ!' አሉሽ:: ቀሪውን አርፋጅ ሁሉ ሳይቀጡ ከፍል እንድንገባ አደረጉ:: ይህንን ባሰብኩ ቁጥር እንባዬ ይመጣል:: ትሩፌ አንቺ ለእኛ እህት ብቻ አይደለሽም እናትም አባትም ሆነሽ አሳድገሽናል:: ምንጊዜም እወድሻለሁ::





ባብዬንና ታትዬን በሕይወት ካሉ አንድ ቀን ወደ አገሬ የመግባት እድል ሲኖረኝ አገኛቸው ይሆናል:: ራሔል ሥራ ይዛ የቤተሰቡን ጫና ታግዝሽ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ:: ሌሎቹ እህቶቻችን እድግው ትልልቆች ሳይሆኑ አይቀሩም::

ትሩፌ ኢሕአሠ ከላይ እንዳልሆነ ሆኖ ሲናድ እታች ያለነው ተሰባስበን ትግሉን እንደ ገና ለመቀጠል ፈለግን:: ሳይኖረው እያበላ--- የጠጣውን እያጠጣ--- የለበሰውን እያለበሰ-- መንገድ እየመራ ከቦታ ቦታ እያዘዋወረ እቅፎ ደግፎ ይዞን የነበረው ገበሬ የድርጅቱን መከፋፈልና መበታተን ወዲያው ነበር የተገነዘበው:: የእቋም ለውጥ ሲያደርግ ደግሞ ውሎ አላደረም:: ከደርግ መንግሥት ጋር የወገነ መሆኑን ለማሳየት እያነቀ በገፀ በረከትነት ሊያቀርበን አቆበቆበ:: በገበሬውም መፍረድ አይቻልም:: እሰንልህ ሰንለው ከርመን ለደርግ ፋሽስታዊ መንግሥት አጋልጠነው ስንሄድ ምን ማድረግ ነበረበት? እኔ እመራው ከነበረው ጋንታ ውስጥ የነበርን ጓዶች ብዙዎቻችን ትግሉን እንደ ገና ለመጀመር ከአገር ውስጥ ይልቅ ሱዳን መሄዱ እንደሚሻል ተነጋግረን ወደዚያው አመራን::

ሱዳን ውስጥ ከገባን በኋላ የገጠመን ግን እንዲህ በደብዳቤ ተጽፎ የሚያልቅ አይደለም:: ሌላው ቀርቶ ሕይወታችንን ለማቆየት እንኳ ከብዙ አደጋ ራሳችንን መጠበቅ ነበረብን:: እኛን መስለው ከተሰደዱ የደርግ አባላት፣ የሕወሃት አባላትና የሻብያ አባላት እጅ ላይ እንዳንወድቅ መጠንቀቅ ነበርን:: በማይረባ ተራ ጠብ ምክንያት ለሞት ያበቋቸው ጓዶቻችን ቁጥር ቀላል አልነበረም:: ሌላው ችግር ደግሞ ሱዳን ውስጥ ሥራ ማግኘት እጅግ ከባድና ፈታኝ ነበር:: በስንት ድካምና ፈተና የተወሰን ጓዶች ሥራ ተገኘልኝ:: የእኔ ሥራ ፋርማሲ ውስጥ መድሃኒት የያዙ ካርቶኖችን ከመኪና ላይ ማውረድና በየቦታቸው መደርደር ነበር:: ይችኑ ሥራ ላለማጣት በትጋት እሰራለሁ:: የፋርማሲው ባለቤት በሥራዬ ወደደኝ፤ አቀረበኝ:: ለመግባባት ያህል ትንሽ የአረብኛ ቋንቋ ችዬ ስለነበር ይኸም ሳያስደስተው አልቀረም::

ትሩፌ ከአንቺ ፍቅርን፣ መረዳዳትን፣ ታማኝትንና ሀቀኝነትን ተምሬያለሁ:: ወደ ፊት የሕይወቴ መመሪያ እንዲሆኑን እጥብቄ አስብ ነበር:: በዚች እድሜዬም በመጠኑም ቢሆን ተግባር ላይ ሳውላቸው ሞክሬያለሁ:: በሰደት ኑሮዬ ግን ታማኝነት ተሻረ:: ለነፍሰ ማቆያ ዳቦ በልተው ማደር የነበረባቸው ሥራ የሌላቸው ብዙ ጓዶች ነበሩ:: ገንዘብ ያስፈልገናል:: እኔ ወንድምሽ ታድያ እሳት የላስኩ ሌባ ሆንኩልሽ:: ፋርማሲው ውስጥ መድሀኒት እየሰረቅሁ እወጣና ውጭ ይሸጥ ነበር::

ዉዷ እህቴ! ስደት ከፉ ነው--ያዋርዳል:: በዚሁ ስርቆት የተነሳ አንድ ቀን የገጠመኝን አስጨናቂ ጊዜ ላውራልሽ:: የፋርማሲው ባለቤት ጥሎበት በእኔ ላይ ከፍተኛ እምነት ነበረው:: ከእሱ አልፎ ባለቤቱንና ልጆቹን ሊያስተዋውቀኝና እቤቱ ሊወስደኝ ብዙ ቀን ጠይቆኛል:: እኔ ደግሞ ሁሌ ሰበብ አላጣም:: የሆነ ያልሆነ ምክንያት እየፈጠርኩ አቀርበታለሁ:: አንድ ቀን 'ዛሬ የፈለገ ምክንያት ብትፈጥር አልቀበልህም:: ልጆቼንና

ባለቤቴን ማየት አሰብሁ' ብሎ ውጥር አድርጎ ያዘኝ። በአጋጣሚ ያን ቀን ደግሞ በዛ ያለ መድሀኒት ሰርቄ ይዣለሁ። በካልሲዬ ውስጥ--በሱሪዬ ስርና በኪሶቼ ምን አለፋሽ ደብቄ ያልያዝኩበት ቦታ አልነበረም። ተመልሼ ሱቅ ውስጥ አልገባ ነገር ዘግተን ወጥተናል። የያዝኩትን መድሀኒት ሁሉ የታባቴ ላድርሰው? ተጨነኩሁ! አላበኝ! ለሌላ ጊዜ እንዲያስተላልፍልኝ ላግባባው ብሞክርም አልሆነም። ደመነፍሴን መኪናው ውስጥ እንደ ገባሁ ወንበሩ ጫፍ ላይ ቁጢጥ ብዬ በተጠንቀቅ ተቀመጥሁ። ስደት ብዙ ፈተና አሳይቶኛል። ያቺን ቀን ግን በፍጹም ተወዳዳሪ አላገኘሁላትም። በዓለም ላይ ሲኖሩ የአመነን ሰው እንደ መክዳት ያለ አሳፋሪና ከባድ ኃጥያት ይኖር አይመስለኝም።

ደግነቱ የፋርማሲው ባለቤት የእኔን ሁኔታ ሳያጤን ስለ ሰሜኑና ደቡብ ሱዳን የፖለቲካ ሁኔታ የሚያወራልኝ በስሜት ነበር። የአፍሪካ ፖለቲካ የአፍሪካውያን ሁሉ እዳ መሆኑን ይበልጥ የተገነዘብኩት ያንን ባለፋርማሲስት ካየሁ በኋላ ነበር። ያለው ሰው ቢሆንም በአገሩ ፖለቲካ በያገባኛል ስሜት ብከንከን ይል ነበር። አቤቱ እስከንደርስ ድረስ ሱዳን በማይረቡ የስልጣን ጥመኞች ፍጥጫ ሕዝቧ እርስ በእርስ ግጭት ውስጥ ገብቶ እንዳይጨራረስ ያለውን ስጋት እየገለጸልኝ ነበር።

አቤቱ ስንደርስ የተንጣለለ ግቢ አለው። የቤቱ ውስጡም ደስ ይላል። ከትንሽ ቆይታ በኋላ ሁለት ሕፃናት ልጆቹ እየጠሯሯጡ ተከታትለው ገቡ። አባታቸውን በፍቅር እያቀፉ ሳሙ። እኔን በእንግዳ ስሜት ትኩር ብለው ተመለከቱኝ። አባታቸው እንዲተዋወቁኝ ወደእኔ ገፋ አደረጋቸው። ሰላም አሉኝ። ከሰላምታው በኋላ ለቀውኝ ይሄዳሉ ስል ጭራሽ እየተሯሯጡ ይላፉኝ ጀመር። ጭንቀቴና ስጋቴ እንዳይታወቅብኝ የማጫውታቸው መስዬ መከላከል ያዝኩ። የልጅ ነገር ለካ እነሱ ያጫወትኳቸው መስሏቸው እየተሯሯጡ ልፊያቸውን አጠናከሩብኝ። ምን ይዋጠኝ!? የያዝኩት መድሀኒት ከአሁን አሁን ወደቀብኝ---ተንኮሻኩሾ ድምጽ አሰማብኝ እያልኩ በወጥመድ እንደ ተያዘች አይጥ ነፍሴ ተጨንቃ ትቃትት ጀመር።

ባለቤቱ ሻይና ዳቦ በትሪ ይዛ ገባች። በአክብሮት ተዋወቅኋት። ሻዩን ፊቴ ላይ አኖረችልኝ። ከግብዣው ይልቅ በልቤ በጣም አድርጌ ያመሰገንኳት ልጆቹ ወደ ውስጥ እንዲገቡ በማድረጓ ነበር። ከሻይ በኋላ እየተጫወትኩ እምሽቴ እራት እንድበላ ጠይቀውኝ ነበር። ሌላ ጊዜ እንደምመጣ ነግሬ እንደ ውሻ ጭራዬን ወሽቄ ተሰናብቼ ሹክክ ብዬ ወጣሁ።

ትሩፌ እውነት እልሻለሁ በሰንት አውደ ውግያ ላይ ውያለሁ። የደርግ ወታደር ከፍተኛ የጦር መሳሪያ የእሳት ላንቃ በላዬ ላይ እያፏጨ ከሞት ጋር ፊት ለፊት ተፋጥጫለሁ። እንደ ዚያን ቀን ግን የሕይወት ፈተናና ጭንቅ ገጥሞኝ አያውቅም። ከዚያ ሱዳናዊ ቤት ከደረሰብኝ ጭንቀት ይልቅ ገሀነመ እሳት መውረድ ሳይቀለኝ አይቀርም። አቤት ደርሼ ለጓደኞቼ ስነግራቸው ሁሉ ላብ በላብ ሆኜ ሰውነቴ ይንቀጠቀጥ ነበር።





ትሩፌ ሙች! እስከዛሬ ድረስ ጥፋተኝነት ይሰማኛል። ከሰራሁት ኃጥያት ሁሉ ይሄኛው የከፋ ሳይሆን አይቀርም። ሲታመኑ ታምኖ አለመገኘትን የመሰለ ከፉ ሥራ አይኖርም። ይኸውልሽ ታድያ በማስታወሻዬ ላይ ይችን የኑዛዜ ግጥም አሰፈርኩ

ላመኑት ከህደት ለፍቅር ጥላቻ፣

ይቅር የማይሉት የኃጢያት ዳርቻ።

ሲያምኑት የከዳ ሰው ሲያጎርሱትም ነካሽ፣

የለም ከዚህ በላይ ሰብእናን አቆሻሽ።

ወይ አለመታደል ወይ ብርቱ ውርደት፣

ሲታመኑ ---ታምኖ አለመገኘት።

ትሩፌ ጥሩ የኑዛዜ ግጥም አይደለች? የአንቺ ዛር ሳይሰፍርብኝ አልቀረም መሰል ስሜቴን በግጥም መግለጽ እወዳለሁ። በልጅነቴ ሁሌ እንደምትይኝ 'ጎበዝ የእኔ ወንድም በርታ!' አልሽኝ አይደል?

ይኸውልሽ ሰሞኑን ደግሞ አንድ አስደሳች ዜና ለስደተኞች ሁሉ መጥቶልናል። የተለያዩ አገሮች ጥገኝነት ሊፈቅዱልን ነው። መጠለያ ገብተን እየተመዘገብን እንገኛለን። የስደት ጥሩ ባይኖረውም ወደ አውሮፓና አሜሪካ የመሄድ እድል ይኖረናል ብዬ አስባለሁ። በይ ትሩፌ በቀጣዩ ደብዳቤ እስከምንገናኝ ቤተሰቡን በሙሉ እኔን ሁነሽ ሳሚልኝ።

ወንድምሽ ድልነሳ ማንያዘዋል

ከሱዳን ----ካርቱም።

እንብባ ስትጨርስ ሳታስበው ደብዳቤውን በሁለት እጇ ደረቷ ጋር ልጥፍ አድርጋ ያዘችው። ዐይኗ ከደን አለ። በተከደነው ዓይኗ ውስጥ ትንሹ ድልነሳን አየችው።

*******

እንደ አለመታደል ሆኖ አልፍነሽ የባለቤቷን ወሬ አላገኘችም። ምህረት ጠይቆ ገባ የተባለን ሰው ሁሉ እያፈላለገች አጠያይቃለች። ስለ መኖሩ--ወይ ስለ መሰደዱ ወይም ስለ ሞቱ እንዲህ ሆኗል የሚላት ሰው አንድም አልተገኘም። እንደ አልፍነሽ ሁሉ ሀዘኑን በቤቱ ጣራ ሰር ይዞ የተቀመጠው ኢትዮጵያዊ ብዙ ነው። ይህንን ሀቅ ብትረዳም ልታቀለው አልቻለችም። እንባዋን ያለገደብ ረጨችው። ትሩፋት ልታጽናናት ብዙ ጣረች። አልፍነሽ

መጽናናት አቃታት፡፡ ጧት ማታ እያለቀሰች ይባስ በሽታ ላይ ልትወድቅ ሆነ፡፡ ትሩፋት መላው ሁሉ እስኪጠፋት ድረስ አብራት ተጨነቀች፡፡

«ስደትን ምርጫው አድርጎ ይሆናል እኮ እልፍዬ፡፡ የስደት ኑሮ ደግሞ ባይመቸው ይሆናል፡፡ በትዕግስት መጠበቁ ይሻላል፡፡ በጭንቀትና በለቅሶ ምን የምትቀይሪው ነገር ይኖራል? የባሰ በሽታ ላይ ወድቀሽ እንዳታርፊውና ልጆችሽን እናት እንዳታሳጫቸው፡፡ ለልጆችሽ ለትይ መበርታት ይኖርብሻል» አለቻት ትሩፋት ቆጣ ብላ፡፡

«እሱስ እውነትሽን ነው ትርፌ ከእንግዲህ ያለኔ ማን አላቸው?» አለች እልፍነሽ እንባዋን እየጠራረገች፡፡ ትሩፋት ጓደኛዋን ለማጽናናት ትሞክር እንጂ ሁለቱም ወርቁን በተመለከተ በውስጣቸው የተረፈ ተስፋ አልነበረም፡፡

«ሰሞኑን እስረኞች ሁሉ ሲለቀቁ ነው እየተባለ ወሬው ሁሉ ይሄው ሆኗል፡፡ ሰውየውን ተዘጋጅተሽ ጠብቂው፡፡ በባዶ ቤት እንዳትቀበይው፡፡ አለች እልፍነሽ፡፡ የተከፋ ፊቷን ፈገግታ ለማላበስ እየሞከረች፡፡

«እሱ ይፈታ እንጂ-- እኛ እንደሆነው ይሆን ነበር፡፡ ደግሞስ ሲመጣ ያደርሳል እኮ እልፍዬ ምን የሚያስቸኩል ነገር አለ ብለሽ?» አለች ትሩፋት፡፡

«አንቺም ቢሆን ጳዳ- ነቃ ብለሽ ጠብቂው፡፡ ወድያውም እኮ አዲስ እንደ ተጋባችሁ ቁጠሪው፡፡ ከአራት ዓመት መለያየት በኋላ መገናኘት እንዲህ ቀልድ እንዳይመስልሽ» አለች እልፍነሽ እየሳቀች፡፡ ያ መራር ሀዘን ጋብ አለና ወደ መቀላለድ ገቡ፡፡

«መቼ ተለየሁትና፡፡ የቀበሌ ስብሰባ-- የወጣቶች ሰብሰባ-- የሴቶች ሰብሰባ.... የሰብሰባ መዓት እያዋከበኝ-- ስብሰባ በቀረሁ ቀን ደግሞ ምን ያደርጉኝ ይሆን? የሚለው ሰቀቀን እያባነነኝ--- እሳር መከራዬን እያየሁ ሁሉን ችዬ በየሳምንቱ እየተመላለስኩ የምጠይቀውን ከምን ልትቆጥሪው ይሆን? እንኳን እራት ዓመት አራት ሳምንት እንኳ ሳንተያይ የቀረንበት ጊዜ የለም፡፡ እሱስ ለይቶለት አንዴ ታሰሯል እኔ ነኝ እንጂ በመመላለስ እግሬ የቀጠነው» አለች ትሩፋት እሷም ፈገግ ብላ፡፡ የወርቁ ነገር ቀርቶ የጨዋታው ርዕሰ--ነገር በመቀየሩ ደስ አላት ትሩፋት፡፡

«አይ የእኔ ዋሾ! የእኔ ቀጣፊ! አሁን ምን እያልኩሽ እንደ ሆነ እጣሽው እና ነው ልታጭበረብሪኝ መሞከርሽ፡፡ ምናለ አሁን የሳሳች ልቤን የአዲስ ዘመን ኩታራና ይሄ ሰው በላ መንግሥት ያደከሟት እንሶ አንቺ ደሞ ባትጨመሪባት፡፡» ብላ እየሳቀች እየቻት፡፡ «አማላጅ ልኮ ጥሎሽ እስጥለን ነው እጅሽን የምንሰጠው፡፡ ቀልድ እንዳይመስልሽ፡፡ እራት አመት ታትም የቆየ ብር እንባር ያለጥሎሽ_ እንዲሁ አናሰብርም» አለች እልፍነሽ፡፡ ተሳሳቁ፡፡





«እሱ ለመፈታት ያብቃው እንጂ የጨሌ ጥሎሽ ይጥልልኛል፡፡ እስር ቤት የጨሌ ጌጣጌጥ እይደል የሚፈበረከው፡፡»

«መፈታታቸውማ አይቀርም፡፡ ይሄ ከፉ አምባገነን መንግሥት ምኑ ሞኝ መሰለሽ እስሮ የሚቀልባቸው፡፡ መግደል ያለበትን ሁሉ ገድሎ ጨርሷል፡፡ አውራ ጠላቱን ኢሕአፓን አሽመድምዶ አጥፍቷል፡፡ ከእንግዲህ ለምኑ ይሰጋ ብለሽው?» ስትል ፊቷን ሀዘን እንደገና ውርስ አደረገው፡፡

ባህርዳር ከተማ ላይ በተካሄደው የጅምላ ጭፍጨፋ ኢትዮጵያ ስንት ሊጠቅሟት የሚችሉ ልጆቿን አጥታለች፡፡ ትሩፋት የይነበብንና የፍቅሩን በሕይወት መኖር ወይ አለመኖር ለማወቅ ግድ እሁድን መጠበቅ ነበረባት፡፡ እንደ ተለመደው ስንቅ ቋጥራ ቅያሬ ልብስ ይዛለች፡፡ እንዲሁም ለፍቅሩ የማይቀረውን ሁለት ፓኮ ሲጋራ፡፡ ወደ ወህኒ ቤቱ ግቢ ለትቃረብ የልቧ ምት ጨመረ፡፡ ጉልበቷ የተብረከረከ መሬትም የከዳቻት መሰላት፡፡ አዙሯት ከመውደቋ በፊት ከዋና መንገዱ ወጣ ብላ ዳር ላይ ካገኘችው ድንጋይ ላይ አረፍ አለች፡፡ ለስንት ደቂቃ እንደ ሆነ ባታውቅም ብዙ የተቀመጠች መሰላት፡፡

«አንድ ለው አብሮኝ መኖር ነበረበት» ስትል ተቆጨች፡፡ ብቻዋን መምጣቷ ትክክል ያለመሆኗ የገባት አሁን ነው፡፡ እውነታውን ስታይ፡፡ የመጣውን ሁሉ በፀጋ ለመቀበል ዝግጁ የሆነች መስሏት ነበር፡፡ አሁን ግን ፈራች፡፡

«በእኔ በራሴ ላይ ሲመጣ ለምን እንዲህ እሆናለሁ ግን? ስንት ጓዶች ተሰውተዋል፡፡ ስንቶችስ ተረሽነዋል፡፡ ይህን ያህል ራስ ወዳድ መሆን ከእኔ ይጠበቅ ነበር» ስትል ራሷን ወቀሰች፡፡ ያኔ ባታ ወህኒ ቤት ከጎኗ እየተነጠሉ የተወሰዱትን ጓዶች አሰበቻቸው፡፡ መጀመሪያ በዐይኗ ሥር የመጡት እነኛ ሁለት ሴት ገበሬዎች ነበሩ፡፡ ከዚያ አገሬ-- ፍቅርተ--- ንጹህ--- ለተብርሀን--- ምሚና..... መጨረሻ ላይ እያዩ መጣባት፡፡ ሆሟ መረረ፡፡ የመጣውን ሁሉ ለመቀበል ዝግጁ የሆነች መሰላት፡፡

ራስ ወዳድ በመሆኗ ራሷን እየወቀሰች እንደ ምንም ተደፋፍራ ወህኒ ቤቱ አካባቢ ቀረበች፡፡ ሄዳ ከተሰበሰበው እስረኛ ጠያቂ ቤተሰብ ጋር ተቀላቀለች፡፡ ተራዋ ደርሶ ስንቅ ስታስመረምር ፍርሀቷ እንደ ገና አገረሸባት፡፡ በማንኪያ ታምሶ እንድትቀምስ የተሰጣት የቅምሻ እንጀራ ደም ደም አላት፡፡ መዋጥ አቅቷት አፏ ውስጥ ተንቀዋለለ፡፡ እየተናነቃት እንደ ምንም ታግላ ብትውጠውም ስቅታ አስከተለባት፡፡ ትንፋሿ እስኪያጥር ድረስ ህቅ እያደረጋት የፍቅሩንና የይነበብን መምጣት ለትጠባበቅ ጊዜው ዓመት የወሰደ መሰላት፡፡ በሕይወቷ እንደ ዚያች አለት ሰዓት ረዝምባት አያውቅም፡፡ ስቅታው ደግሞ አላቆም አላት፡፡

« አፍንጫሽን ያዥ»

«ትንፋሽሽን እምቅ አድርገሽ ይዘሽ ወደ ውስጥ ዋጭ....» እስረኛ ለመጠየቅ የተሰበሰበው ሰው የሚያውቀውን መላ ሁሉ መከራት:: ሰቅታው እየባሰባት ሲሄድ የተመለከተ አንድ ወጣት ልጅ ከአቅራቢያ ወዳለ ቤት ሩጦ ሄዶ ውሀ አመጣላት:: ደጋግማ እየተንነጨች ዋጠችበት:: ሰቅታው ጨርሶ ባይተዋትም እየተሻላት መጣ::

እንዲህ ትንፋሽ አጥሯት በጭንቅ ቆማ መንገድ መንገዱን ስትመለከት ይነበብ ብቻውን ሲመጣ ከሩቅ አየችው:: ስሟን ደጋግሞ ሲጠራት እንኳ የሰማችው ዘግይታ ነበር:: ቀና ብላ ስታየው ዐይኑ ቀልቷል:: የቀይ ዳማ ፊቱ ጠቁሯል:: በጣም የተጎሳቆለና ከእድሜው በላይ ያረጀ ሆኖ ታያት:: እንባዋ አሸንፏት እንዳይወርድ የመጨረሻውን ጥረት አደረገች:: የይነበብ እንባ ግን ከቀሉ ዐይኖቹ እየወረደ ጉንጮቹን አራሳቸው:: ያኔ የእሷም እንባ ጉንጮቿን አልፎ ደረቷ ላይ ተንጠባጠበ:: ትሩፋት ብዙ ጊዜ አታለቅስም:: ማልቀስ ከጀመረች ግን ማቆሚያ የላትም:: ለቅሶዋ መሪር ነው:: እንደ ሁልጊዜው ብዙ ሳይነጋገሩ የመለያያ ሰዓቱ እንኳ ሳይደርስ ተሰናብታው ሄደች::

በዚህ በመረረ የሀዘን ሰዓት ብቻዋን መሆን ነው የፈለገችው:: መንገዱን ሁሉ በደመነፍስ ስትጓዝ ፍቅሩ ከአዕምሮዋ አልወጣም:: ያኔ ስድስተኛ ከፍል እያሉ የነበረው ትንሹ ፍቅሩ ሁለመናው ትዝ አላት:: ያደርጋት የነበረችው ጥቁር ቁምጣ ሱሪ--- ከላይ ይለብሳት የነበረችው ቡኒ እጀ ጉርድ ሹራብ--- እንደ ወይዘሮ ሴት ልስልስ ያሉት ጫማ የሌላቸው ባዶ እግሮቹ--- ግርም የሚያደርጓት ረጃጅም የእጅ አጣቶቹ--- በአውን ያየችው እስኪመስላት ድረስ ዐይኗ ስር ድቅን አለባት:: ደግሞ በቤት ጠረጋው ጊዜ በእንችነሽ ምክር ተገፋፍታ ሳያስበው በጥፊ ስታጮለው የነበረው ሁኔታ መጣባት--- አብናት ተመልሶ ሲሄድ አድሮባት የነበረው ፀፀት ሁሉ ታሰባት:: ስምንተኛ ከፍል ላይ ደብተሯን፣ መጽሐፏን ያገኘውን እቃዋን እየወሰደ ያስቸግራት የነበረው-- እሷን ብሎ ትምህርቱን አቋርጦ ደብረታቦር ድረስ የመጣው--- ለፍቅሯ ሲል ሽንት ቤት እስከ ማጠብ ድረስ የከፈለው መስዋእትነት--- አዲስ ዘመን መጥቶ ከፀሐይ ቤት ያሳለፉት ጊዜ ሳይቀር ወለል ብሎ በሀሳቧ ታያት:: በዚያም ሳያቆም አስመራ ድረስ መምጣቱ--- ለእሷ የነበረው ጥልቅ ፍቅር--- ከማሰብ በላይ ሆነባት::

አንድ ቅዳሜ ቀን ደግሞ ሐሸሽ አጭሷል ብላ ለመጀመሪያ ጊዜ የፈራችው ቀን ትውስ አላት:: በጣም ከፍቶት ነበር:: የእናቱንና የቤተሰቡን ከድህነት ወለል በታች የወረደ ችግራቸውን ሲነግራት አድሮበት የነበረው መሪር ሀዘን:: መጨረሻ ላይ--- አዎ! መጨረሻ ላይ ቃሏን የሰጠችው ቀን--- ያን እለት ፊቱ ላይ ያነበበችው ቃላት ሊገልጹት የማይችሉት ደስታው--- እግሯ ሥር የተንበረከከው--- ከዚያ የሆነውን ሁሉ አሰበችው--- መኖር አስጠላት:: መሪር ሀዘን አዘነች:: ጭንቅላቷ ባዶ ቅል የሆነ እስኪመስላት ድረስ ለፍቅሩ አለቀሰችለት:: ለዚች መከረኛ አገር እድገት--- ብልጽግና አስበው ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም ለተሰውት ጓዶች ሁሉ ልቧ ደማች:: እንጀቷ ተንሰፈሰፈ:: ከፍተኛ ሀዘን አዘነች:: እንባዋ ከውስጧ ተንጠፍጥፎ ያለቀ እስኪመስላት ድረስ ከፉኛ አነባች.....





አምባገነኑ የደርግ መንግሥት የተወሰኑትን ረሽኖ በጅምላ ከቀበረ በኋላ የተወሰኑትን ደግሞ መፍታቱ የታወቀ አሰራሩ ነው:: ባህር ዳር ከተማ ግማሽ ሀዘን ግማሽ ደስታ ተፈጥሮላታል ሰሞኑን:: ሕዝቡ በተረሸኑት ልጆቹ-- እህቶቹ--ወንድሞቹ... ማቅ ለብሶ አዝኗል:: የዚያኑ ያህል ደግሞ በተፈቱት ተደስቷል:: ሀዘን--ተፍስሃ.....

******

«እኔ ከእንቺ ጋር ነው የምተኛው» አለ ቴዎድሮስ ከእናቱ አንገት ላይ እጁን ጥምጥም አድርጎ:: ወደ ኋላው ተጠምዞ ዞሮ እንግዳውን ሰውየ እየተመለከተ::

«አዲስ አንሶላና አዲስ ብርድ ልብስ ውስጥ መተኛት አትፈልግም ቴድዬ? እስኪ ሂድና እንዴት ቆንጆ እንደ ሆነ ተመልከት» አለች ትሩፋት እየሳቀች፤ ከሳሎኑ አንድ ጥግ ላይ ወደ ተዘረጋው አልጋ በእጇ እያመለከተችው::

«አንቺ አብለሽኝ ከተኛሽ ነዋ!» አለ ዐይኑን እንግዳው ሰውዬ ላይ ሳይነቅል:: እንግዳው ሰው ሳቀና

«ና እስቲ ቴድዬ ና! እንደውም ዛሬ ከእኔ ጋር ነው የምታድረው:: እየው ይህን እሰጥሃለሁ» አለው በጨሌ እምሮ የተሰራ ብዕር እያሳየው:: ቴዎድሮስ ወደ ሰውየው በመሄድና ባለመሄድ አመነታ:: ሰውየው ብዕር የያዘ እጁን እንደዘረጋ ማባበሉን ቀጠለ:: ልጁ ቀስ እያለ ቀረበው:: አባትና ልጅ ተቃቀፉ:: ጉያው ውስጥ አስገብቶ በናፍቆት እቅፍ አድርጎ ሳመው::

ይነበብ ተፈትቶ የመጣ እለት ትሩፋት ቤቷ በሰው ጢም ብሎ ነበር:: ገንቦ ጥላ፣ ጠርሙስ አረቄ፣ ጠጅ በደንበጃንና በማንቆርቆሪያ እየያዘ ያልመጣ አብሮ አደግ ጓደኛና ወዳጅ ዘመድ አልነበረም:: እንደ ሰርጓ እለት ደስታዋ ደስታቸው ሆኖ ነበር::

«ይህንን ፍቅር አዋቂ ደግ ሕዝብ ምን ይውሉለታል? ከቶ ምን ቢደረግለት ውለታው ተከፍሎ ይዘለቃል?» አለች ትሩፋት ደስታዋ ደስታቸው ሆኖ ያመሹትን ሰዎች ተመልከታ::

******

«ስንት እልፍ አእላፍ ጓዶች ሕይወታቸውን የሰውለትና--ሊሰውለት የተዘጋጁለትን ዓላማ የትም በትነው በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዲህ ፍርክስከሳቸው ይወጣል ብዬ እንኳን በውኔ በህልሜም አስቤው አላውቅም ነበር:: በኢሕአፓ ላይ የነበረኝ የእምነት ጽናት ከብረት የጠነከረ ነበር» አለ ይነበብ:: በጀርባው ተኝቶ በግራ እጁ የትሩፋትን ፀጉር እየደባበሰ:: በጨለማው ምክንያት ከማይታየው የላስቲከ ኮርኒስ ላይ ዐይኑን አፍጦ:: ታየው ይመስል

በጨለማው ውስጥ ራሷን ጣል አድርጋበት ከነበረው ሰፊ ደረቱ ላይ ከአንገቷ ወደ ላይ ቀና ብላ

«ምን እንደሚሰማኝ ታውቃለህ ይነበብ?» አለች ትሩፋት:: «ይቺ አገር እንደ ቴዎድሮስ ለአድገቷ፣ ለብልጽግናዋና ለዳር ደንበሯ ቀናኢ የሆነ ቆራጥ መሪ-- እንደ ምኒልክ ብልህና አስተዋይ ዲፕሎማት መሪ እንዳይወጣባት የተረገመች ነው የሚመስለኝ::»

«እርግማን ነው ብለን ምክንያት ካልሰጠነውና ለጥፋታችን ማመካኛ ሰበብ ካልፈለግንለት በስተቀር ስህተቱ የእኛው ነው:: አጉል እወቅን ባይ ትውልዶች ነን:: ተመካክሮና ተቻችሎ መሥራት አናውቅም:: የራሳችንን ሐሳብ ማኾጎድጎድ እንጂ የሌላውን ሐሳብ በጥሞና አናዳምጥም:: ብናዳምጥ እንኳ በቀናነት ላለመቀበል ምክንያታችን ብዙ ነው:: ከመከባበርና ከመተሳሰብ ይልቅ መወነጃጀልና መነቃቀፍ ይቀናናል:: ለየግል እምነታችንና ሀሳባችን እንጂ ለቆምንለት ዓላማ ተገዥዎች አልሆንም:: ቂመኞች ነን:: በይቅርታ መማማር አናውቅም:: ይኸ ሁኔታ ደግሞ በተለይ ከላይ አመራሩ ላይ ያሉ ሰዎችን በእጅጉ ተጠናውቷቸዋል:: በዚህ ምክንያት ጠባቧን ቀዳዳችንን መድፈን ተስኖን አስፍተን አስፍተን ለጠላት ተመቻችተን ውድቀታችንን አፋጠን::»

«አባከህ ተወኝ ይነበብ:: እርግማን ባይሆን ኖሮ ሰፊ የሕዝብ መሰረት ያገኘች--- ለውጥ ሲያመጣ የሚችል ትኩስ የወጣት ኃይል በብዛት ያቀፈች— በመላ ኢትዮጵያ ሰፊ ድጋፍ የነበራት ሕብረ-ብሄር ድርጅት እንዲህ በአንድ ጊዜ ከዐይናችን ሥር የእንቧይ ካብ ሆና ባልተናደችም ነበር:: አባቶቻችን ድንገት ተሰባሰበው የውጭ ጠላትን ያህል አሳፍረው የመመከት ኃይል ነበራቸው:: እኛ እንዴት እጅ ላይ የደረሰ ድል ያመልጠናል? እንዴት ምንም የሕዝብ ድጋፍ በሌለው አምባገነን መንግሥት መዳፍ ስር እንዳይሆኑ ሆነን እንወድቃለን? እውነትም እንደሚወራው ይች አገር እንዳታድግ--- እንዳትበለጽግና እንዳትሻሻል የነበላይ ዘለቀ እርግማን ሳይኖርባት አይቀርም» ብላ መልሳ ደረቱ ላይ ኃደም አለች::

«አባቶቻችን ለቆሙለት ዓላማ ጽናት ነበራችው:: በዚያ ላይ ይተማመናሉ:: ቃላቸውን አያጥፉም:: እንዲት ቃል ከምትጠፋ አይሞቱ ምት ቢሞቱ ይሻላቸዋል:: ከነተረቱ እንኳ 'የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ' አይደል የሚሉት:: ለአባቶቻችን ቃል ከባድ ነገር ነው:: በተለይ በመሳሪያ ከተማማሉማ እስከወዲያኛው አይከዳዱም:: የገንዘብና የስልጣን ነገር አያጓጓቸውም:: ለዚህ ነው እንደ ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ለቅኝ ገዥዎች ያልተንበረከኩት:: አገራቸውንና ነፃነታቸውን ጠብቀው ለትውልድ ያስተላለፉት እርስ በርሰ ተማምነው በመነሳታቸው ነበር:: እኛ ግን እምነትና ጽናት ይጎለናል:: በቁንጽል እውቀታችን አጉል እንመጻደቃለን:: 'እኔ ይበልጥ አውቃለሁ:: እኔ ያልኩት ካልሆነ' የሚል ከፉ ትዕቢት የተጠናወተን ትውልዶች ነን:: የማዝነው ሳልተገኘ ነጻነት የተከፈለውን ከንቱ መስዋዕትነት ሳሰብ ነው:: የኢሕአፓ መፈረካከስ ብዙዎቻችን ላይ ደርግ ከደረሰብን





ቶርቸር የበለጠ ጎድቶናል:: በቀላሉ ለማይጠገን የመንፋስ ስብራት ዳርጎናል:: በባህርዳር ወህኒ ቤት እንኳ በጓዶቻችን ላይ የተፈጸመውን ግፍ ሳስታውስ ሰው መሆኔ ያስጠላኛል» ብሎ በረጅሙ ተነፈሰና ዝም አለ::

«እንደምታውቂው» ይነበብ ቀጠለ ጸጉሯን መደባበሱንም አልተወም:: «እንደምታውቂው እሰረኛ ምንጊዜም ቢሆን የውጭውን አየር ይናፍቃል:: ለሽንት የሚወጣበትን ሰዓት በጉጉት ሲቆጥር ይውላል:: አንድ ቀን ከሽንት ሰዓት ቀደም ብሎ አንድ ወታደር መጥቶ ለሥራ ውጭ እንደምንፈለግ ሲነግረን የተፈታን ያህል ነበር ደስ ያለን:: ሥራው እዚያው ግቢ ውሰጥ ጉድጓድ መቆፈር ነበር:: በሳምንት ጊዜ ውስጥ አምሰት በአምስት ሜትር ጥልቀትና ሰፋት ያለው ትልቅ ጉድጓድ ቆፍረን ጨረስን፤ ለተጨማሪ ሽንት ቤት እንደ ሆነ እየገመትን» ብሎ ዝም አለ:: ትሩፋት ደረቱ ላይ ኃደም እንዳለች ማዳመጧን ቀጥላለች::

«የቁፋሮው ሰራ ሲያልቅ ከዚያች ነፍስን ከምታሰጨንቅ ጠባብ ከፍል ውስጥ መዘጋት ሊመጣ መሆኑን ስናውቅ ተከፋን:: በባህርዳር ሙቀት በዚያች ጠባብ ከፍል ውስጥ ከመዘጋት የማይሻል ነገር የለም:: በሚቀጥለው ሳምንት ደግሞ ሌላ ተጨማሪ ሥራ ተገኘልን:: ደስ አለን:: ከግቢው አንድ ጥግ ላይ አዲስ የተቆረጠ ግንድ ተከምሯል:: ሥራው የግንዱን ልጥ መላጥና ገመድ መፍተል ነበር:: አሁንም ገመዱ ለማገር ማሰርያ እንደሚሆን ገመትን:: ከተከመረው ግንድ ላይ ግማሹ እስረኛ ልጡን እየላጠ ሲያቀብል ግማሹ ገመድ መፍተሉን ተያያዝነው:: ይኸኛው ሥራ እንደ ተጠናቀቀ የፈራነው አልቀረም እዚያችው ትንፋሽ ከምታሳጥር ከፍላችን ውስጥ ገብተን ተዘጋን:: ሕይወት እንደ በፊቱ በጠባብ ከፍል ውስጥ ቀጠለች:: መኖር ወይም አለመኖርን እየጠበቀች::

አንድ ቀን ከሌሊቱ አራት ሰዓት ገደማ ይመስለኛል የከባድ ጫማ ኮቴ ግቢያችን ውስጥ በረከተ:: የመኪና ፓውዛ መብራት ይበራል—-ይጠፋል:: ለሰላም እንዳልሆነ ሁሉም እስረኛ ገብቶታል:: ሁላችንም የተጨነቀች ነፍሳችንን ከውስጥ እያዳመጥን ተቀመጥን:: የሁላችንም ጆሮ ደግሞ ውጭ የሚሆነውን ሁሉ በንቃት ይከታተላል:: የከባድ ጫማ ኮቴ ከከፍላችን ይቀርባል ይርቃል:: በዚህ ሁኔታ ላይ እያለን በዛ ያለ ሰው ኮቴ ሲሰማንና የከፍላችን በር ቁልፍ ሲከፈት አንድ ሆነ:: ወታደሮች ተከታትለው ገቡ:: ሁላችንም ባለንበት ደንግጠን የጨው አመድ መሰልን:: ከመካከላችን ጓዶቻችን ስማቸው እየተጠራ ሲወጡ ጠብደል ጠብደል ወታደር ከውጭ እየቀለበ እጃቸውን ለኋሊት እየሰበረ በፈተልነው ገመድ ያስራቸው ጀመር:: ዐይናችን እያየ ጓዶቻችን ከየከፍሉ እየተወሰዱ ሌላ ከፍል ውስጥ ሰበሰቧቸው:: መሞታቸው ቁርጥ መሆኑን ሲያውቁ እስረኞቹ መጮህ ጀመሩ:: መዝሙሩ መፈክሩ ያን የወህኒ ቤት ግቢ ቀውጢ አደረገው:: ከወህኒ ቤቱ ውጭ ያሉ ኗሪዎችም ይጮሁ ነበር::

በኋላ ወሬው እንደ ተሰማው ከሆነ እርስ በእርስ ተረዳትተው እስራቸውን ይፈታሉ:: ከእስር ነጻ ሲሆኑ ሁሉም ለማምለጥ ይሞክራሉ:: ያመለጡት አመለጡ:: የያዟቸዉን

እስረኞች ግን በፈተልነው ገመድ እያነቁ ከቆፈርነው ጉድጓድ ውስጥ በጅምላ አፈር መለሱባቸው:: ከእነዚህ እስረኞች ውስጥ አንዱ ፍቅሩ ነበር» አለ ሀዘን ባደከመው ድምጽ:: ለጥቂት ጊዜ ከባድ ጸጥታ ሆነ፡

«ሊመታ ስሙ ሲጠራ 'ለሰዉ ልጅ ያለህን እዛኝ ልብና አከብሮት አደንቃለሁ:: ትሩፋት አፍቃሪና ታማኝ ባል ማግኘቷን ሳልነግርህ አልሞትም:: ምንም ያህል ጊዜ ቢረዝም እምባገነኑ የደርግ መንግሥት መውደቁ አይቀርም:: የተሰዋንለት ዓላማ የብርሀን ጮራውን በኢትዮጵያ ምድር ሁሉ መፈንጠቁ አይቀርም:: ያኔ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ኑሯችሁ የሰላምና የፍቅር እንዲሆን ከልቤ እመኝላችኋለሁ:: ለትሩፋት መቃብር ውስጥ ሆኜ እንኳ ሁሌም እንደ ማስባት ንገርልኝ:: ያን ያሳለፍነውን የልጅነት ጊዜ አትርሽው አደራ ብሎሻል በልልኝ» ብሎ ለስንብት አቅፎ ሰሞኝ ሊወጣ ዐይኑ ውስጥ ያየሁት ቆራጥነት መቼም ቢሆን አይረሳኝም:: እስከ መጨረሻው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ፍትህ ነፃነትና እኩልነት እንድታገል መሪር መልዕክት ነበረው» አላት::

እንቧዋ ደረቱ ላይ ወርዶ ሞቅ ሲለው ተሰማው:: ከአንገቱ ቀና ብሎ በጨለማው ውስጥ ግንባሯን--ዐይኗን --አፍንጫዋን--ጉንጯን --ከንፈሯን ሳመ:: እንቧዋ አፉ ውስጥ ጨው--ጨው አለው:: እጣጥሞ ወደ ውስጥ ዋጠው:: እሳት ስሜቱን ረመጥ ሆና የምትቀበለው ትሩፋት ዛሬ አልቻለችም:: እንደ በረዶ ቀዝቅዛ ዝም አለችው:: ሁለ ነገሯን እየደባበሰ ያገኘውን የሰውነት ከፍሏን ሁሉ ሳመ:: መታገስ እንዳለበት ግን ወዲያው ነው የገባው::

«እስከ መጨረሻዉ በጽናት የቆመ እሱ ጻድቅ ነው» የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ትዝ አለው:: «እስከመጨረሻው በጽናት የቆመ-- እሱ ድል አድራጊ ነው» አለ በለሆሳስ ለራሱ:: ኢሕአፓ ከላይ እመራሩ ፈራርሶ የቀረበ ድል ከእጅ ላይ ሲያመልጥ ከታች ያለው አባል ተስፋው እንደ ጉም በነነ:: በቀበሌ እመራሮች ተሰብስቦ መድረክ ላይ እርስ በርሱ ተጠቋቆመ:: ይነበብ ያደራጃቸው እንደነ መናለ ጀንበር--እንደነ ወሰንና ጌታሁን የመሳሰሉ ገበሬዎች በጠቋሚ ታስረው እሳር መከራቸውን እዩ:: ከኑር መሬታቸው ላይ ተነቀሉ::

«ከእንግዲህ እነዚህን ተስፋቸውን ሙጥጥ አድርገው ከጨረሱ ገበሬዎች ልብ ውስጥ መልሶ መታመንን እንዴት ማግኘት ይቻል ይሆን? የትግል መንፈስ እንደ ገና በልባቸው ውስጥ ማሳደር የሚቻለው እንዴት ተደርጎ ቢሠራ ይሆን? ደርግ ለጊዜው የበላይነቱን ተቀዳጅቷል:: ድሉን ያገኘው ግን በራሱ ጥንካሬ ሳይሆን ኢሕአፓ በገጠማት የውስጥ ችግር ተዳክማ በመገኘቷ ነው:: ይህን የተዳከመ ኃይል መልሶ ማጠናከር የሚቻለው እንዴት ነው? ዳግም ለሕዝብ ልዕልና የሚያስቡ ጠንካራ የገበሬ ጓዶችን ከእንግዲህ እንዴት ማግኘትና ማሰባሰብ ይቻል ይሆን?» በውስጡ ለተደረድሩት ለእነዚህ ጥያቄዎች ምንም መልስ አላገኘላቸውም:: ቢያነሳ ቢጥል ምንም ጠብ ያለለት መፍትሄ አልነበረም:: ለጊዜው የታየው ወደ ስራው ተመልሶ እስካሁን የተጎዳውን ቤተሰቡን ማደራጀት ነበር:: ሴትም ወንድም--- እናትም አባትም ሆና ድርብ ድርብርብ ትግል የታገለችውን





የደከመችውን ትሩፋትን ማገዝና ማሳረፍ ይኖርበታል:: ፊቱን ሙሉ ለሙሉ ወደ እሷ ዞሮ ሁለመናዋን ወደ ራሱ ልጥፍ አድርጎ አቀፋት:: ገላዋ ሙቀት ሲረጭ ተሰማው---

******

ኢትዮጵያ የወዛደሩን ፓርቲ ትመሰርታለች:: በወዛደሩ ፓርቲ ትመራለች:: ጆሮ ስልችት እስኪለው ራዲዮኑ ቀኑን ሙሉ የሚያወራው ስለ ኢሰፓ ምስረታ ብቻ ነው:: ድርቅ ደግሞ ኢትዮጵያን በተለይ ሰሜናዊ ከፍሏን ከፋኛ እየመታ ይገኛል:: ሰውና ከብት እንደ ቅጠል እየረገፈ:: በ1966 ዓ.ም ንጉሱ የልደት በአላቸውን ከፈረንሳይ በመጣ ኬክና ሻንፓኝ ሲያከብሩ ወሎ ውስጥ ሰው በጠኔ ሲረግፍ ነበር:: የደርግ መንግሥት ደግሞ በተራው የሰውን በችጋር ማለቅ ቸል ብሎ ለኢሰፓ ምስረታ ሽር ጉድ ማለቱን ተያይዞታል:: አዲስ አበባ ለሠራተኛው ፓርቲ ምስረታ ልትሞሸር ነው:: ልትዋብ፣ ልትኳኳል:: በዓለም ፊት አሸብርቃ- ደምቃ ልትታይ:: የደርግ ባለስልጣናት መብራቶችንና ርችቶችን እንዲሁም የዲኮሬሽን ባለሙያዎችን ከሰሜን ኮርያና ከቻይና በማስመጣት ከፍተኛ ሥራ ላይ ተጠምደዋል:: የርሀብ ቸነፈር ደግሞ ትግራይን፤ ወሎንና የጎንድር ቆላማ ቦታዎችን እንደ እውሎ ነፋስ በፍጥነት እያዳረሰ ይገኛል:: ገበሬው ቀዬውን እየለቀቀ ሲሰደድ የባለስልጣናቱ ዐይንና ጆሮ እያይም አይሰማም:: ቀልባቸው ሁሉ ከሠራተኛው ፓርቲ ምስረታ ላይ እርፏል:: ልክ እንደ ጃንሆይ 80ኛ ዓመት ልደት በዓል ጊዜ:: አስረኛው የአብዮት በዓል ሊከበር-- ኢሰፓ ሊወለድ 1977 ዓ.ም::

«ትሩፌ ይህ የድርቅ መባባስ ምን ያመጣ ይመስልሻል? ሰው እኮ በሚያሳዝን ሁኔታ እያለቀ ነው:: የደርግ መንግሥትን ግን ያሳሰበው አይመስልም::

«የ1966ቱን ዓይነት አብዮት እንድልህ አሰበህ ከሆነ ተሳስተሃል ይነበብ:: ይህ ለውጥ ናፋቂ ትውልድ አንድ ባላወቀው ስህተት ሊያገኝ የነበረውን ድል ተነጥቋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ከራሱ ጨዳኝ ገዥዎች ተላቆ ሊጎናጸፈው የነበረው ነፃነት እጁ ላይ አምልጦታል:: በእኔ ይሁንብህ ይህ ድርቅ በዚህ እምባገነን መንግሥት ላይ የሚፈጥረው አንዳች ለውጥ አይኖርም:: የሚያመጣው ለውጥ ቢኖር የኢትዮጵያን ምስኪን ሕዝብ እልቂት ብቻ ነው» አለች ትሩፋት ፍርጥም ብላ::

«እንኳን አንድ እምባገነን መንግሥት ይቅርና ማንኛውም ከስተት ቢሆን የራሱው ልደትና ሞት አለው:: ወታደራዊ መንግሥት ለዘለዓለም ይኖራል ከሚል ድምዳሜ ላይማ አንደርስም:: ደርግ መውደቁ--ለውጥም መምጣቱ አይቀርም:: እንዲህማ ተስፋ አትቁረጭ:: አይዞን!»

«እርግጠኛ ነኝ እንዲህ በአጭር ጊዜ ውስጥ በዚህ ድርቅ ምክንያት ግን አይሆንም:: ይነበብ አይታይህም? ደርግ እኮ በኢትዮጵያ ምድር ላይ ጀግና እንዳይበቅል አድርጎታል::

ዳግም ቆራጥ ታጋይ እንዳይፈጠር ቀጥቅጦ ቀጥቅጦ የፍርሃት ቆፈን ለቆበታል:: በፍርሀት ተሸብቦ ሁለመናው እርዶ እየተንቀጠቀጠ የሚገኝ ሕዝብና ትውልድ አድርጎታል:: ፈሪ---ወላዋይ---አድብርባይ ትውልድ እየተቀፈቀፈ ነው:: በቀበሌ የማጋለጥ ዘመቻ ጊዜ ታዝቤዋለሁ:: እንዲህ ዓይነት ትውልድ ደግሞ ለውጥ ያመጣል ብዬ ማመን ይከብደኛል:: ከገባበት የፍርሃት--የወላዋይነትና የአድርባይነት ቀፎ ውስጥ መውጣት ይኖርበታል:: ለነፃነቱ ቀናዒ የሆነ አዲስ ትውልድ ካልተፈጠረ በስተቀር ይች አገር ምንም ተስፋ አይኖራትም:: ቆራጥ ትውልድ ለማግኘት ደግሞ ከባድ ትግል ይጠይቃል:: እንደ ገና ሌሎች የትግል ዓመቶች-- እንደ ገና ሌላ መስዋዕትነት.......»

«ትክክል ነሽ ትሩፌ ከባድ ትግልና መሰዋዕትነት ይጠይቃል:: ይህ እንዲሆን ደግሞ እያንዳንዳችን ለዳግም መሰዋዕትነት ቢያንስ ውስጣችንን ማዘጋጀት ይጠበቅብናል:: በታሪክ እንደ ተረጋገጠው ምንጊዜም ቢሆን ሕዝብ አሸናፊ ነው:: ይህንን መቼም አትጠራጠሪም::»

«እንጃ! እኔስ አልመሰለኝም:: ሕዝብ አሸናፊ ነው የሚለው ጽንሰ-- ሐሳብ እንደ ገና ጥናት የሚያስፈልገው ሳይሆን አይቀርም:: በተግባር ሲታይ አሸናፊው ሕዝብ ሳይሆን መሳሪያ የያዘ-- የመሳሪያ የበላይነት እየሆነ እያየሁት ነው:: ከአዛውንት እስከ ወጣት ሰፊ የሕዝብ ድጋፍ የነበራት ኢሕአፓ መች ለድል በቃች»

«ሕዝብ ጠንካራ ድርጅትና መሪ ይፈልጋል:: ኢሕአፓ ሰፊ የሕዝብ ድጋፍ ቢኖራትም ነገሮችን አቻችሎ የሚይዝ ብልህና አስተዋይ መሪ አልነበራትም ማለት ነው:: የሕንድ ሕዝብ ማህተማጋንዲን የመሰለ ብልህ መሪ በማግኘቱ ነፃነቱን ሊቀዳጅ ችሏል:: የደቡብ አፍሪካ ሕዝብ ማንዴላን የመሰለ አስተዋይ መሪ ባያገኝ ኖሮ ይሄኔ ከአፓርታይድ ነፃ ባልወጣም ነበር:: ከነፃነትም በኋላ እንኳ ቢሆን እልቂት በተፈጠረ ነበር:: ያለፈውን ከፉ የታሪክ ጠባሳ በይቅርታ አወራርዶ ነጩንና ጥቁሩን ሕዝብ እንዲህ አቻችሎ በአንድ ላይ ማኖር የተቻለው ማንዴላ ብልህና አርቆ ተመልካች መሪ በመሆኑ ነበር:: ዓለም ዘመናትን ተሻግረው አርቀው ለተተኪው ትውልድ የሚያስቡና የሚጨነቁ ብልህነትን---አስተዋይነትን---ትዕግስትን--ቆራጥነትን--ለሕዝብና ለአገር ተቆርቋሪነትን--የተላበሱ መሪዎችን የምትፈጠረው ምናልባት በምዕተ ዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል:: ኢትዮጵያ እነዚህን ፀጋዎች የተላበሰ መሪ አትወልድም ብለን ተስፋ አንቆርጥም:: መውደቅ መነሳት ደግሞ አንዱ የትግል ገፅታ ነው» አለ ይነበብ ተስፋዋ ጨርሶ እንዳይጨልም እየሰጋ::

«ደርግ 'ያደማችሁትን አብዮት ካሱ' በሚል ፈሊጥ እረፍት ነሰቶናል:: እያየህ ነው አይደል? ከመደበኛ ስራችን ውጭ በየገጠሩና በየመንደሩ እየዞርን የእርዳታ እህል እንድንሰበስብ በትኖናል:: እንደ ሰንበት ዱቄት ለማኝ መነኩሲት አቅማዳ ይዘን ቤት ለቤት ስንከራተት እንውላለን:: የማታ ማታ ቤታችን የምንገባው ደክሞን ነው:: ለተራበው ሕዝብ አዝኖ እንዳይመስልህ:: ከአልተረፈው ሕዝብ የተረፈ ነገር አይገኝም:: ከዚህ ኑሮው ከእጅ ወደ





አፍ ከሆነ ሕዝብ የሚገኝ እርዳታ ቋት እንደማይሞላ አጥቶት አይደለም:: በየቤታችን እንዳናርፍ ውከበት መፍጠሩ ነው:: ፋታ እንዳናገኝ የሰነልቦና ወረራ ማካሄዱ ነው:: በዚህ ሁኔታ ተጠፍንጎ የተያዘ ትውልድ እንደ ገና ለለውጥ ማነሳሳት እንዴት እንደሚቻል ዘዴው አልታይሽ ብሎኛል» አለች ትሩፋት::

«ዘዴው ቀላል ነው:: ለውጥን ከራስ መጀመር:: ያለማወላወል ለለውጥ ራስን ዝግጁ ማድረግ:: ተስፋ ሳይቆርጡ በቆራጥነት እንደ ገና መደራጀት:: ራስ ያመኑበትን ጉዳይ ለሌሎች ማስረዳትና ማሳመን አይቸግርም:: ከዚያ በኋላ በችኮላና በአንድ ሰሞን ሆይ ሆይታ ሳይሆን በርጋታና በብልሃት ሕዝብን አስተባብረው የሚመሩ መሪዎችን ፈልፍሎ ማግኘት:: ለግል ዝናና ጥቅም ሳይሆን ለሰው ልጅ በሙሉ የሚያስቡና የሚጨነቁ ነገን አሻግረው የሚመለከቱ ባለራዕይ መሪዎችን ማግኘት ከተቻለ እንኳን የሕዝብ መሰረት የሌለውን አምባገነን መንግሥት መገርሰስ ይቅርና መንግሥተ ሰማያትን መውረስ ይቻላል» አላት:: ጠንክሮ ሊያጠነክራት እየሞከረ::

«ይነበብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጁንና ሕይወቱን ገብሮ ሊጎናፀፈው የነበረውን ድል በአንዱ ወይ በሌላው ስህተት ከዓይኑ ሥር መሳሪያ በያዙ ወታደሮች ተነጥቋል:: ያን የተነጠቀ ድል ለማስመለስ በተለይ ወጣቱ በቆራጥነት አይከፍሉ መስዋእትነት እየከፈለ ባለበት ወቅት ከህደት ደርሶበት አንጀቱ እየተቃጠለ በጠላቱ ፊት እንዲንበረከክ ተፈርዶበታል:: ተስፋውን ሁሉ አጨልመውበት ተዋርደው በየቀበሌው መድረክ እንዲዋረድ አድርገውታል:: ይህንን ለመልካም ዓላማ ሕይወቱን ሊገብር ተነሳስቶ በከንቱ እንዲባክን የተደረገን ትውልድ መልሶ ለትግል ማነሳሳትና ማሰባሰብ የሚቻል አልመሰለኝም:: ታውቃለህ ተስፋ መቁረጥ ከሁሉም በላይ የከፋ ነው:: ሕዝቡ-- ወጣቱ ተስፋ ቆርጧል» ብላ ዝም አለች::

«ለምን ተስፋ እንቆርጣለን? እንዲህ ያለ ውድቀት በእኛ አገር ብቻ አልተጀመረም እኮ ትሩፌ:: በዓለም ላይ የተነሱ ለውጥ ፈላጊ ታጋዮች መንገዱ ሁሉ አልጋ በአልጋ ሆኖላቸው አይደለም ለድል የበቁት:: እየወደቁ-- እየተነሱ በቆራጥነት እስከ መጨረሻው ስለታገሉ ነው» አለ ይነበብ::

ይነበብ ጅግና ኪዳነምህረት የአምራቾች የኅብረት ሥራ ማህበር ውስጥ እንደነምናለና ጌታሁንን የመሳሰሉ፣ አርባተንሳ ቀበሌ ገበሬ ማኅበር ውስጥ ደግሞ እንደነወሰንና ዋሰይሁንን የመሳሰሉ እሳት የላሱ ንቁ ገበሬዎችን መልምሎ ለትግሉ ሙሉ ድጋፍ እንዲሰጡ አድርጎ ነበር:: በእርግጥ ቀላል ተግባር አልነበረም:: በቀላሉ ተጠራጣሪ የሆኑ ገበሬዎችን አሳምኖ የትግሉ አጋር ማድረግ ፈታኝ የሆነ ተከታታይ ሥራና ትዕግስትን ይጠይቃል:: እነዚህ የገበሬ ጓዶች በስራቸው ብዙ ገበሬዎችን የመለመሉ ደፋሮች ነበሩ:: ኋላ ላይ ያተረፉት ነገር ቢኖር እስርና መሬት አልባ መሆንን ነበር:: «ልጅ አምነን ልጅ ሆነ» ብለው ተስፋቸው እንደ ጉም በኗል:: አሁንስ በሚሄድባቸውና በሚያደራጃቸው

ቀበሌ ገበሬ ማኅበራት ውስጥ ጠንካራ የገበሬ ታጋዮችን ማግኘት ይችል ይሆን? በሚያገኛቸው ገበሬዎች ልብ ውስጥ እንደ ገና የትግል ወኔን ማሰረጽ ይቻል ይሆን? ድርቅ ፤ ርሀብና ስደት የሚከሰተው መልካም አስተዳደር ካማጣት መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው:: ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ድሀ ሆና አይደለም:: ከርሰ ምድሯ የሦስት ሜትር ጥልቀት ያህል ሳይቆፈር ውሃ የሚገኝባት አገር ናት:: በድርቅ ምክንያት በዓለም ፊት እጇን ለልመና መዘርጋቷ ውርደት ነው---ውርደት! ገበሬው ውሃ ማቆርን--የመስኖ ውሃ መጠቀምን ቢማርና ቢያውቅ ኖሮ የዝናብ እጥረት ባጋጠመ ቁጥር ለርሀብ ባልተጋለጠም ነበር:: የተወለደበትንና የኖረበትን ቀዬ ትቶ ባልተሰደደም ነበር:: በይነበብ አዕምሮ ውስጥ እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ሀሳቦች ይነሳሉ ይወድቃሉ:: ለዚች አገር ሁለንተናዊ እድገት መምጣት የደርግ አምባገነን መንግሥት መወገድ አለበት ብሎ በጽኑ ያምናል:: የወሰደውን ያህል የትግል ጊዜ ይውሰድ እንጂ ለሕዝብ እድገትና ብልጽግና ሕዝባዊ መንግሥት መመስረቱ ወሳኝ ነው ብሎ ደምድሟል:: ግን እንዴት? መቼ? ገና መልስ ያላገኘላቸው የተንጠለጠሉ ጥያቄዎቹ ሆኑ ::

«ነገ ጧት ነው ወደ እብናት የምሄደው» አለ ይነበብ:: ዝም ዝም ብለው ከቆዩ በኋላ:: ሁለቱም በየራሳቸው ሐሳብ ተጠምደው ነበር::

«ይዘኸው የምትሄደው ምን ይዘጋጅልህ?» አለችው::

«ብዙ ነገር አልይዝም:: ከሳምንት በላይ የምቆይ አይመስለኝም::»

******

ይነበብ እብናት ከተማ ሲደርስ ሰማዩ አመዳማ ጭጋግ ለብሶ ሰማያዊ ውበቱን አጥቷል:: ትንሿ የገጠር ከተማ እብናት ቅዝዝ ያለው አመዳማ አየር ተጋብቶባት በቁሟ ታንቀላፋለች:: ከከተማው ትንሽ ወጣ ብሎ ከሚገኘው ሜዳ ላይ የርሀብ ሰለባዎቹ ጠጠር መስለው-- ጠጠር አክለው ፈሰዋል:: ሕይወት ከመኖር ተሰፋ ጫፍ ላይ አንጠልጥላ መጠለያ በሌለው ሜዳ ላይ እከት አድርጋ ይዛቻዋለች:: የረጉ ዐይኖቻቸውን ከጊዜያዊው የእርዳታ ማሰተባበሪያ ጣቢያ ድንኳን ላይ ሰክተው--ተረኛ ሟች ማን ሊሆን እንደሚችል እንኳ ሳያውቁ ---ሩሀዋቸው ህቅ እስከትል ድረስ እጃቸውን ለእርዳታ ዘርግተዋል::

ይነበብ ከቦታው ሲደርስ ይህን ያህል ለቁጥር ያታከተ በድርቅ የተጎዳ ሕዝብ ይኖራል ብሎ አልጠበቀም ነበር:: እንዴት አድርጎ ሥራውን መጀመር እንዳለበትና እንዴትስ በትክክል መወጣት እንደሚችል ማሰላሰል ያዘ:: እብናት ከተማ የገቡት ርሀብተኞች አብዛኞቹ ከትግራይና ከወሎ የመጡ ናቸው:: ቁጥራቸው ይነስ እንጂ ከጎንደር ቆላማ ቦታዎችም የመጡ ይገኙበታል::





ይነበብ ከመስሪያ ቤቱ የተላከበት ዋና ሥራ እብናት ከተማ በጊዜያዊ የእርዳታ ጣቢያው የሚገኙትን ተረጅዎች መመዝገብ ነው:: የመጡበትን አካባቢ በቀበሌ ገበሬ ማኅበር --በጢሰ፤ በአባውራና በቤተሰብ ብዛት ለይቶ ለዋናው ግብርና መስሪያ ቤት ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል:: «በሳምንት ጊዜ ውስጥ እመለሳለሁ» ያለው ሰውዬ የሕዝቡን ብዛት ሲያየው በወር እንኳ የሚጨርሰው አልመሰለውም:: ስደተኞቹ ከሰፈሩበት ሜዳ ከመግባቱ በፊት ወደ ከተማዋ ሄዶ ማደሪያ የሚሆን አልቤርጎ በአንድ ትንሽ ልጅ ጠቋሚነት የተሻለ ነው ከተባለለት ቡና ቤት ውስጥ አንድ ክፍል ያዘ:: ክፍሉ ጠባብ ነው:: እንደ ክፍሉ ሁሉ ባለ እግሩ የሽቦ አልጋም ጠባብ ነው:: ብርሀን በደንብ አይገባውም:: ጭንቅ ይላል:: ይነበብ ምርጫ አልነበረውም:: የልብስ ቦርሳውን አልጋው ላይ ጣል አድርጎ ዘወር ሲል ይዞት የመጣው ልጅና የቡና ቤቱ አስተናጋጅ በር ላይ ቆመዋል::

«ጋሼ ቁልፉ ይኸው» ብላ እጇን ዘረጋች አስተናጋጇ:: እሰስላ የሞቀው እጇ ጠቁሮ ጥላሸት የተቀባች አስመስሏታል:: ቁልፉን ተቀበላት:: «ከፍያ ቅድሚያ ነው ጋሼ» አለች በማስከተል:: አስር ብር አውጥቶ ሰጣት:: መልሱን ሳይቆጥር ተቀበላትና ለልጁ ሁለት ብር ሰጥቶ አሰናበተው:: ልጁ አመሰግኖት በደስታ እየዘለለ ከግቢው ወጥቶ ሄደ:: ይነበብ የሚጠጣ ነበር ፈልጎ ወደ ቡና ቤቱ ማስተናገጃ ክፍል ገባ:: ስው የተለያየ መጠጥ ይዞ በቡድን በቡድን ያወራል:: ጥግ ላይ ቦታ አግኝቶ ተቀመጠ:: ከሱ ጎን የተቀመጡት አራት ሰዎች ሞቅ ያለ ጨዋታ ይዘዋል:: ጨዋታው ድርቁን የሚመለከት በመሆኑ ይነበብ ሳይጋበዝ የነሱ አድማጭ ሆነ::

«የወረዳ አስተዳዳሪውና የእርዳታ አሰተባባሪዉ ተጠሪ ተባብረው የተጫነውን ሰንዴና ዱቄት በቁሙ እዚያው አዲስ አበባ ለነጋዴ ሸጡት እኮ እነዚህ ሆዳሞች!» አለ ከአራቱ ሰዎች አንደኛው በቁጭት::

«በዘርና በቀለም የማይዘመደነ---- በዐይኑ ያላየነ ፈረንጅ አዝኖ ሲረዳነ የእኛዎቹ ጅቦች በየቀኑ የሚረግፈውን ርሀብተኛ ከመጤፍ አልቆጠሩትም:: ይገርማቸኋል! ወረዳ አስተዳዳሪው አዲስ አበባ ላይ የገዛው ቤትና ገልባጭ መኪና ይላሉ:: በድሀ ሞት እሱ ከብሯል:: ይኸ ድርቅ ለእሱ ከሰማይ የወረደ በረከት ሆኖለታል::»

«ከዚህ በርሀብ አለንጋ ከሚገረፍ ሕዝብ መንጋጋ ፈልቅቆ የበላው እንጀራ እንጀራ እንዳይመስልህ:: ደም ነው--የሰው ደም:: የሰው ደም ደሞ አዙሪት አለው:: ዞሮ ዞሮ ግፉ አይለቅም:: ቆይ ታያለህ! የዚህ ድሀ ሕዝብ እንባ መሬት ጠብ አይልም:: ግፍና በደል ቆይቶም ቢሆን መድረሱ አይቀርም:: ፈጣሪ እንደ ሰው ለበቀል አይቸኩልም:: ሲቀጣም ዱላ አያነሳም:: የቆየ ሰው ያያል:: በራሳቸው ወይ በልጅ ልጆቻቸው ላይ እዳቸውን መክፈላቸው አይቀርም:: ምናለ በሉኝ::»

«ኧረ ወዲያ ተወኝ እባከህ አያ! በችጋር እየተቀጣ ያለው ይኸው መከረኛ ሕዝብ ነው:: እነሱ ጮማ እየቆረጡ በውስኪ ሲራጩ እሱ በሾርታቴ እያለቀ ነው:: ፈረንጅ በረዳው ሰንዴና ዱቄት እነሱ አዲሳባ ላይ ሰማይጠቀስ ቤት ሰርተዋል:: ከመኪና መኪና እያማረጡ እየተንፋላሰሱ ነው:: ይብላኝ ቀን ለጎደሰበት ለአገሬ ድሀ ገበሬ! ምንም ሳይደርሰው በስሙ እየተነገደ ለሚላገጥበት!»

የአብናት ኗሪ የእርዳታ እህሉ በወረዳ አስተዳዳሪውና በእርዳታ አስተባባሪው ተጠሪ መዘረፉን በምሬት ያወራል:: እውነትም በየእለቱ በራድዮ የሚነገረው የእርዳታ እህል መጠን የትየለሌ ነው:: ለተረጅው ደርሶ ነፍስ ሲያተርፍ ግን እንብዛም አይታይም:: ሀሩርና ቁር እየተፈራረቀበት ባዶ ሜዳ ላይ የፈሰሰውን ርሀብተኛ በየለቱ ሞት ይቀጥፈዋል:: ከእርዳታ ማስተባበርያው ጣቢያ ደርሶ ያለው ሰው ጠግቦ ሳይበላ በየቀኑ ቀየውን እየለቀቀ የሚመጣው ሰው ቁጥር ህልቆ መሳፍርት የለውም:: የተሰባሰበው ርሀብተኛ የረባ እርዳታ ሳያገኝ በየቀኑ እየመጣ ይጨመራል---ይጨመራል... ሰሞኑን ደግሞ አንድ አስደንጋጭ ወሬ ተሰምቷል:: አብናት በታች ከቆላው በአንድ ቤተሰብ ላይ የደረሰ አሳዛኝ ታሪክ ነው:: መቼም ይሄ የ1977 ድርቅ ያላፈረሰው ጎጆ--ያልበተነው ቤተሰብ የለም::

«አባከሽ አዝግመሽም ቢሆን አብረን እንሂድ አለሜ:: ተይሀ ባዶ ባድማ እጣ ነፍስሽን እነዚህን ጨቅላ ሕጣናት አሳቅፌሽ መሄዱ ጨነቀኝ እኮ! ሰጅብ ሰጥቻችሁ እንዴት ብዬ ልሂድ?» አለ ዋሰልኝ ቤተሰቡ በሙሉ ቀስ እያለ አዝግሞ የእርዳታ እህል ይገኝበታል ወደ ተባለው አብናት ከተማ እንዲደርስለት እሰቦ:: ሚስቱ ደግሞ መንገዱን ፈራች::

«ኧረገኝ አንተወይ ምን ሆንከብኛ! ከአንተ ጋር ብኸድ ጠልቼ ይመስልሃል? ባነሳ ብጥለው የማይሆንልኝ ሆኖ እግኝቸው ነውይ» አለች የሻረግ ባለቤቷን ዋሰልኝን ሰረቅ አድርጋ የጎንዮሽ እያየችው:: አዬ ጉድ! እንደ ዱሮው ቢሆን ኖሮ ይኸ አስተያየቷ ስንት ጊዜ ቀበቶ አስፈትቶ--- ስንት ጊዜ ሱሪ አስወልቆት ነበር::

«ከቀየው ለምልከት የቀረ ሰው እኮ የለም የሸዬ!»

«ከንቱ ሳልደርስልህ ለምን እጀምረዋለሁ እንተወይ? ተመንገድ ነው የምቀርብህ:: ሆዴም ባዶ አይደለም፤ ቅሪት ነኝ» ስትለው አመድ መስሎ አጥንቱ እንደ አለት ያገጠጠው ፊቱ ጭራሽኑ ጨው መሰለ:: መናገር አቃተው::

«ቶሎ ቶሎ ሰመኸዱ ሌጣህን መሆኑ ይሻላል:: ችግሩ ውሃ መጥፋቱ ነውይ ለጊዜው ጭቃም ቢሆን እኮ ርሀብ ያስታግስ ነበር:: ዛዲያ ውሃው ከዜት ይምጣ?» አለች የሻረግ የውሃው ነገር እያስጨነቃት:: ባለቤቷ ቶሎ ሄዶ ለነብሳቸው እንዲደርስ ገፋፍታ ሰደደችው:: ዋሰልኝ ተነስቶ መንገድ ሲጀምር ሁሉ ልቡ የኋሊት እየቀረበት ነበር::





ድርቁ ከአባቢውን እንድዶታል:: በአቅራቢያ የሚገኝ ወንዝና ምንጭ ሁሉ ነጥፏል:: የሻረግ ውሃ ፍለጋ በጧት የወጣች ናት:: ልጆቿ ጠብታ ውሃ አጥተው በጥም ከማለቃቸው በፊት የትም ፈልጋ ቢሆን ይዛላቸው መድረስ ይኖርባታል:: ጉዞዋን በየት አቅጣጫ እንደምታደርግ አሰበች:: ፊት ለፊቷ ወደምታየው ተራራ መሄዱ እንደሚሻል ገምታ ወደ ዚያው አዘገመች:: ሲደከማት እየተቀመጠች--- ደግሞ እየተነሳች--- እንደ ገና ደግሞ እረፍ እያለች-- ትንፋሽ እየወሰደች ትንሽ ለምለም ቅጠል ባየችበት ቦታ ሁሉ ተንከራተተች:: እሷም ምላሷ ደርቆ ከጉሮሮዋ ሊወተፍ ምንም ያህል አልቀረውም:: ጉልብቷ ዝሎ ተስፋዋ ሁሉ ተሟጠጠ:: ባለችበት ቆማ ወደ ቤቷ በመሄድና ባለመሄድ መካከል ስትዋልል ከአንድ ተራራ ግርጌ አጅብ ብሰው የበቀሉ ለምለም ቅጠሎች ተመለከተች:: እንደ ምንም ያለ የሌለ ኃይሏን አሰባሰባ ወደ ዚያው እዘገመች:: ከተራራው ስር ስትደርስ ጀንበር ልትጠልቅ ወደ ምሽጓ እያቆለቆለች ነበር:: ርጥብ አፈር አገኘት:: በእጇ ቧጥጣ አንድ ሁለት ጊዜ ጎረሰችለት:: አዲስ ጉልበት ያገኘች መሰላት:: እጠገቧ ባገኘችው ሹል ድንጋይና እንጨት በዛለ ክንዷ የራሰውን መሬት ማስ ማስ አደረገችው:: የቆፈራቻት ትንሽ ጉድጓድ ቀስ እያለች ውሃ መያዝ ጀመረች:: የረጋ ዐይኗን ሳታራግብ በጉጉት ተመለከተቻት:: ትንሽ ውሃ መያዝ ጀመረች:: በያዘችው ፋጋ ጨልፋ ተጎነጨች:: የደረቀ ጉሮሮዋ ቻስ–ስስ ብሎ ሲረጥብ ታወቃት:: በርካታ ተነፈሰች:: ውሃዋ ትንሽ ትንሽ እያለች እየተጠራቀመችላት ነው:: ከላይ ከላይ በፋጋዋ እየጨለፈች እንስራዋን ሞላች:: ማንገቻ ጠፍሩን እንገቷ ላይ አጥልቃ እንስራዋን አነሳች:: ቀስስ አድርጋ ከሚያረገርግ ጉልበቷ ላይ አሳረፈችው:: ትንሽ ቆም ብላ ትንፋሽ ወሰደች:: እየተንቀጠቀጠች አሁንም ቀስስ አድርጋ ወደ ጀርባዋ አዙራ ተሸከመች:: ልትወድቅ ተንገዳገደች:: እንደ ምንም ሚዛኗን ጠብቃ ቆም አለች:: ትንፋሿ መለስ ሲልላት ጉዞ ወደ ቤቷ ጀመረች::

ምሽቱ ገፍቶ ለዐይን ያዝ ሲያደርግ ወደ ቤቷ ተቃረበች:: ልጆቿ ቀኑን ሙሉ በር በሩን ሲያዩ ነው የዋሉት:: ከሩቁ ብቅ ስትል ተመለከቷት:: እንደ ድሮው ቢሆን ኖሮ ሩጠው ጉልበቷ ላይ በተጠመጠሙባት ነበር:: እዚያው እንደ ቆሙ በደስታ ፈገግ ለማለት ሞከሩ:: ፈገግታቸው ግን አጥንቱ ካገጠጠ ፊታቸው ላይ ተጣብቆ ቀረ:: እሷም በእናትነት ፍቅር ፈገግ ለማለት ሞከራ ነበር:: አልሆነላትም:: ፈገግታዋ እንደ ጣሰ ከተጣመመ ፊቷ ላይ ከሰመ::

«ግድ የለም ይኸ ከፉ ቀን እስኪያልፍ ያለፋል:: እንኳን ውሃውን አግኝቼ በጥም ለተንገበገቡ ለልጆቼ ደረስኩላቸው:: ተመስገን! ከርሀብ የከፋውና ጊዜ የማይሰጠው ውሃ ጥም ነው:: አባታቸው ደሞ እህሉን ይዞ ሲሮጥ አሁን ይደርስልናል» አለች:: ውስጧ በመኖር ተስፋ ተሞልቶ:: ከራሷ ጋር እየተነጋገረች ወደ ቤቷ ቀረበች:: ልጆቿን ከጥም ለመታደግ እየቸኮለች:: የቤቷን ደፍ ለመርገጥ ጥቂት ሲቀራት አንድ ያላስተዋለችው የቆመ ድንጋይ አደናቀፋትና ባፍ ጢሟ ተደፋች:: ጀርባዋ ላይ የነበረው እንስራ ወደ ፊቷ ተወርውሮ ተከሰከሰ:: ርሀብ ባደከመው ጉልበቷ--- በሌለ አቅሟ--- ቀኑን ሙሉ ስትንከራተት ውላ የቀዳችው ውሃ ጠጥቶ የማይጠግበውን መሬት አለበሰው:: ልጆቿ

የተደፋው ውሃ ባራሰው መሬት ላይ ተረባረቡ:: በምላሳቸው ላሱ:: ተስገብግበው በጥፍራቸው እየቧጠጡ ጭቃውን በሉ::

የሻረግ እንደ ወደቀች ናት:: እዚያው እንዳለች በሰመመን እልም ብላለች:: ነገር ዓለሙ ሁሉ ዙሮባት አዕምሮዋን ስታለች:: ምን እንደ ተፈጸመ--የት እንዳለች--እሷ ራሷ ምን እንደ ሆነች ረሳች:: ድንገት ቀና ብላ ባለችበት ፍዝዝ--ድንዝዝ ብላ ቁጭ አለች:: ፊት ለፊቷ ወድቆ ከተከለከለሰው እንስራ ጀሮ ላይ እይኗ አረፈ:: በደመነፍስ ሄዳ ቶሎ ጠፍሩን ፈታች:: በዚያው ፍጥነት ወደ ጓሮ ዞረች:: ቅጠሎቹ ረግፈው መለመላውን ወደ ቆመው ግንድ እነጣጠረች:: ባለ በሌለ ኃይሏ ግንዱ ላይ ወጣች:: ከተንጨፈረሩ ቅርንጫፎቹ ወፈር ባለው ላይ ጠፍሩን ጠለፈች:: ባዶ ባድማ ውስጥ ብቻቸውን የቀሩትን ልጆቿን የሚያስታውስ ሕሊና አልነበራትም:: እንገቷን ሸምቀቅው ውስጥ አስገባች:: ኮሰማና ሰውነቷ አየር ላይ ተወዛወዘ::

በቃ!! የሻረግ ከእንግዲህ በርሀብ አለንጋ እየተገርፉ የሚንገላቱ ልጆችን ሰቆቃ አታይም:: ከእንግዲህ በውሃ ጥም እየተቃጠሉ የሚንጠራወዙ ከሲታ ልጆቿን እያየች በሀዘን ፍላፃ አትወጋም:: የእርዳታ እህል ለማግኘት የወጣ ባሏ እንኳ ሳይመለስ እሷም ላትመለስ እስከ ወድያኛው ነጉዳለች:: ልጆቿም ይከተሏት ይሆናል:: በእሁኑ ይዞታቸው ምን የሚያቆይ ተስፋ ይኖራቸዋል? እግዜሩ ሲያዳላባቸዉ ጧቱን በዚች ጎስቋላ አገር ፈጥሯቸዋል:: እነሱ ከጥጋብ በላይ በልተው እያገሱ ፍርፋሪያቸውን እንኳን ከማይጥሉ ጭካኝ ገዥዎች እጅ ላይ ጥሏቸዋል::

ይነበብ እብናት ደርሶ በድርቁ የተጎዱትን ሰዎች ሲያይ ሀዘኑ ከባድ ነበር:: እዚያ ቡና ቤት ውስጥ የሰማው ወሬም ትክክል ሳይሆን አይቀርም:: በውጭ አገሮች ለእርዳታ ተሰጠ የሚባለዉ በቶን የሚቆጠር እህል እዚህ እብናት ደርሶ ነፍስ ሲየተርፍ ብዙም አላስተዋለም:: አሰራሩ ሁሉ የይስሙላ ነበር:: በድርቅ የተጎዳው ሕዝብ በሚያሳዝን ሁኔታ ውስጥ ይገኛል:: በየቀኑ በሞት የሚቀሰፈው ሰው ለቀብር ያታከታል:: በእብናት የእርዳታ ማስተባበሪያ ጣቢያ ውስጥ ሞት ተራ የተለመደ ነገር ሆኗል:: ለካ ሞትም ይለመዳል:: እንዱ አፈር ሳይለብስ ሌላው ይከተላል:: በጸጥታ እየተንጠራወዙ በከሳ ጉልበት ልጅን---እናትን--አባትን--ወይ እህት ወንድምን..... አፈር ጫር ጫር አድርጎ አልብሶ መለስ ይባላል:: ዋይታ የለም! ደረት መጣል የለም! ጀርባ ላይ የተጣፈ እንጀት እየተንሰፈሰፈ በዝምታ ጸጥ--- ረጭ እንዳሉ ስርዐተ ቀብር ይፈጸማል:: «እዬዬም ሲደላ ነው» ማለት ለካ ይሄ ኑሯል::

የየሻረግ እሟሟት ደግሞ ከመቼው ወሬው በሁሉም ጆሮ መድረሱ ፍጥነቱ ይገርማል:: ድፍን የእብናት ሰው እንደ ጉድ ያወራዋል:: አንድ ከነየሻረግ መንደር ወረድ ብሎ የሚኖር ገበሬ ነው አሉ ወሬውን ያመጣው:: ያለ እናት አባት የቀሩትን የየሻረግን ልጆች «እንዴት ዓይኔ እያየ ለጅብ ጥያቸው እሄዳለሁ» ብሎ ከልጆቹ ጋር አብሮ ይዟቸው እብናት ይደርሳል:: እሱ ራሱ ሚስቱን አፈር አልብሶ ልጆቹን ይዞ ቀዬውን ለቆ መሰደዱ ነበር::





ሁለቱ የየሻረግ ልጆች እብናት ደርሰውለታል:: እንደኛው ግን አልቻለም:: መንገድ ላይ እናቱን ተከትሏል::

አንዲት የውጭ ጋዜጠኛ «የውሃው መዘዝ» በሚል ርእስ የየሻረግን አሳዛኝ እሟሟት በዜና በመጽሔት ላይ አወጣችው:: ለታዋቂ የዜና ማሰራጫዎች ሁሉ አስተላልፋው ዓለም ሁሉ እንዲሰማው አደረገች:: ኢትዮጵያና መታወቂያዋ የሆኑት እነዚያ አጥንታቸው ያገጠጠ፤ ሆዳቸው የተቆዘረ፤ ዝንብ የወረራቸው ሕጻናት ጭምር እስከ ዓለም ጫፍ ተናኝተዋል:: እንደ ቢቢሲ የመሳሰሉ ታዋቂ የዓለም አቀፍ የዜና አውታሮች ውሃ ፍለጋ ሄዳ-- ውሃ ሆና ለቀረችው የሻረግ ትልቅ ሽፋን ሰጥተዋት ከአጥናፍ አጥናፍ ስሟ ናኘ:: በዚች መከረኛ አገር የተፈጠረችው የሻረግ ሕሊናዋን ሲታ አንገቷን ለገመድ ሰጥታ ጉም ላይ ተንሳፋ ቀርታለች:: ተወልዳ አድጋ-- ተድራ ተኩላ ወግ ማዕረግ ያየችባትን መንደሯን ዞራ ላታያት ነጉዳለች:: ዓለም በሌለችበት የአዞ እንባ አነባችላት::

ኢትዮጵያ ልጆቿን በሰበብ አስባቡ ትነጠቃለች:: የሰው ሰራሹ ጦስ ሳያንሳት ተፈጥሮም ፊቷን አዙራባታለች:: ጋራና ሸንተረር-- ሜዳና ተራራ---ወንዝና ባሕሩ---ጫካውና ድሩ.... ያለሰው ብቻውን አገር ሳይሆን ሰዎቿን ትጨርሳለች:: ይች ኢትዮጵያ የሚሏት ስመ ገናና አገር ሰው ሆኖ ለሰው የሚያስብ ከላይ የተቀባ መሪ ፈጣሪ ገና አልሰጣትም:: እጆቿን ወደ ሰማይ እንደ ዘረጋች ይኸው ስንትና ስንት ዘመኗ! እንደ አለመታደል ሆኖ በመልካም አስተዳደር እጦት እድገቷ አንድ እርምጃ ወደ ፊት ሁለት እርምጃ ወደ ኋላ ሆኖ ብዙዎች የዕለት ጉርስ የማያገኙባት አገር ሆና አርፋዋለች:: የሚጠጣ ውሃ ከእቅሙ ጠፍቶ እሱኑ ፍለጋ ሲንከራተቱ ብዙዎች የሚቀጠፉባት ለዓለም ትዝብት የተዳረገች አገር ሆና ቀርታለች:: «የመጀመሪያው መጨረሻ» ከዓለም ኃያላን አገሮች ተርታ ተቆጥራ የስልጣኔ ቁንጮ እንደ አልነበረች ሁሉ ዛሬ በዓለም ፊት ኢትዮጵያና አጥንታቸው ያገጠጠ ርሀብተኞች የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሆነው አብረው ዘልቀዋል:: በሃያ እንደኛው ክፍለ ዘመን እንኳ ያልተለወጠ ታሪክ::

የዚያን ቆለኛ አድሜ ያስንብተው ዋለልኝ ሁለቱን ልጆችን አግኝቷል:: በዚህ ደስ ብሎታል:: መንገድ ላይ ሞት የነጠቀው አንዱ ልጁና የሻረግ ደግሞ ከሆዱ አልወጣለት ብለው ይብሰለሰላል:: የሻረግንና እሟሟቷን ባሰበ ቁጥር እሱም መኖር ያስጠላዋል:: አንዳንድ ጊዜ እንደ እሷ በብጣሽ ገመድ «ሀቅ» ብለህ ሙት!--ሀቅ ብለህ ሙት!» የሚል ሳይጣናዊ ሐሳብ ይፈታተነዋል:: ዘለዓለማዊ የሰማይ ቤቱ መፍረሱና የልጆቹ ነገር እያስጨነቀው ነው እንጂ የሚሰቱን እጣ ፈንታ ለመጎንጨት ብዙ ጊዜ ብልጭ ብሎበት ያውቃል::

ትሩፋትን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲንዲቋቋም፣ የተሻለ አስተዳደርና እድገት እንዲመጣ የተሰው ጓዶቻቸው ምንጊዜም በእሷነቷ ውስጥ ተቀብረው ልቧ ውስጥ ሀዘንና ፀፀት ተከለውባት አልፈዋል:: አብሮ አደግ የልጅነት እፍቃሪዋ ከርታታው

ፍቅሩ---- እነያዩ--- እነአገሬ----- እነለተብርሀን-- እነንጹሀ----- እነኛ ምስኪን ሴት ገበሬዎች---- እኒያ በራቸው ላይ በደም ከተነከረ ልጃቸው አስከሬን ላይ ድፍት ሲሉ በጥይት የተመቱት እናት--- እብዱ ዋጋ--ኧረ ስንቱ!!... አሁን ደግሞ ድርቅ ሕዝብ እየፈጀ ነው:: «እግዚአብሔር ፊቱን ያዞረባት አገር» አለች:: የየሻረግን አሟሟት የሰማችው በቢቢሲ ዜና ነው:: ለየሻረግና ለልጆቿ ልቧ ቁስል እስከትል አዘነች---በየቀኑ ሞት ለሚቀጥፈው ርሀብተኛ ወገኗ አዘነች--- ለዚች ጎስቋላ አገር አዘነች:: «መቼ ይሆን ከሀዘን የሚወጣው? ለስንቱስ አዝኖ ይዘለቅ ይሆን?» አለች ከፍት ብሏት::

በዚህ በተባባሰ የድርቅ እልቂት ሰዓት የደርግ መግሥት ደግሞ ለኢትዮጵያ «የዳቦ ቅርጫት» የሚለውን የቆየ ቅጽል ስሟን በዓለም ፊት ለማስመለስ ብቸኛው አማራጭ ሰፈራ ነው ብሎ ቆርጦ ተነስቷል:: እብናት ጊዜያዊ የድርቅ ማስተባበሪያ ጣቢያ ከተሰባሰበው የድርቅ ተጎጂ ጉልበታቸው ጠና ጠና ያሉትና በእድሜ ያልገፉት ሰዎች በውድም ይሁን በግድ በአገሪቱ ድንግል መሬት ላይ ጉልበታቸው መዋል አለበት ብሎ ደምድሟል:: ወደ ደቡብ የኢትዮጵያ ክፍል ሄደው መስፈርና መሥራት አለባቸው ብሎ ወስኗል:: ለዚህ የሰፈራ ፕሮግራም ግብ መምታት ደግሞ የግብርና መሥሪያ ቤት ሰራተኞች ኃላፊነት ተጥሎባቸዋል:: አምርቂ የቅስቀሳ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል:: ይነበብ እብናት ከሄደ በኋላ ይህ ተጨማሪ የሥራ ትዕዛዝ ደርሶታል:: ይህንን ድንገት ከላይ የወረደ የመንግሥት እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ ግራ ገብቶታል:: በጥናት ያልተደገፈ ሥራ እንዴት ሊሰምር እንደሚችል አያውጠነጠነ እያለ ድንገት ፍዝዝ ብሎ ማዶ ማዶውን እያየ የሚቆዝመው ሰው ቀልቡን ሳበው:: በአካል እንጂ በመንፈስ እዚያ የለም:: እልም ጭልጥ ብሎ በሐሳብ ነጉዷል:: ይነበብ ወደ ሰውየው አመራና ትከሻውን ጎንተል ሲያደርገው

«የጠቅል አሽከር!» ብሎ ፎከሮ በፍጥነት ዞር አለ ዋሰልኝ:: ፉከራው ደግሞ ይግረም:: ለካ ልብና ወኔ አይሞትም::

«ይቅርታ ወንድም ሳታስበው ነከቼህ አስደነገጥኩህ መሰል?»

«ኧረ የለም ጌታው አላስደነገጡኝም:: የማልገፋው ሐሳብ ይዞ እየወዘወዘኝ ፈዝዤ ነበር እንጂ እርሰዎማ ከምኔ ደርሰው» አለ ዋሰልኝ:: በእድሜ ከእሱ ቢያንስም የመንግሥት ሠራተኛ በመሆኑ በአክብሮት አንቱ አያለው::

«ግድ የለም አንተ በለኝ:: ለመሆኑ ስምህ ማን ይባላል?» አለ ይነበብ::

«አገር የለሰው ሰው ምን ስም አለው ብለው ጌታው? ባገሬ--በቀዬየ ሳይማ ዋሰልኝ አባል ነበር:: ዋሰልኝ ሀብቴ:: እዬ ወድያ! ተለው እጅ ወድቆ የተዋረደ ሰው ምን ስም ይኖረዋል? አገር ላይ ኑሮ ካልተጠሩበት» አለ በትካዜ መሬት መሬት እያና በእግሩ እየቆረቆረ::





«አይዞህ! ይኸ በአገር የመጣ ነው:: ለአንተ ብቻ ለይቶ የመጣ ችግር አይደለም» አለ ይነበብ ሊያጽናናው::

«ኧረ የኔ መከራ ደም ከማን ይገጥማል ጌታዬ!? በማንስ ደርሶ ያውቃል!? በኔ ነው እንጂ ለጉዱ በፈጠረኝ! ድርቁማ መቼም የአገር ሁሉ እርግማን ነው:: ከሞቱ አማማቱ የልጅነት ምሽቴ እንዳልሆነ ሆና ሙታብኝ ነው እንጂ ማዘኔ:: የምድሩ ሲቃይ ሳያንሳት በገዛ እጇ ሁለት ነፍሷን እጥፍታ የሰማይ ቤቷን ዘጋች:: አግዜርን አሳዝና እኔንም እንጀቴን በጥፉ ቆርጣኝ ሄደች:: እንዳልሰሰን አድርጋ በቁሜ ገላኝ ሞተች» አለ ዋሰልኝ:: ከአንገቱ ላይ በጠመጠማት እርጌ አደፋ ነጠላ ፀይኑን እየጠራረገ:: ይነበብ የየሻረግ ባለቤት መሆኑ ገባው:: አዘነለት::

«ከማን ጋር ትጋፋለህ እንግዲህ? በርታ ብሎ መጽናናት ነው የሚሻለው:: ለመሆኑ ድርቁ በጣም ጎድቷችኋል ማለት ነው?»

«ኧረገኝ! ይኸማ ምኑ ይጠየቃል ጌታው? ችግሩ ከፍቶ ጥሪታችን አሟጠን ብንጨርስ እንጂ መንደራችን የለቀቅነ:: ቤታችን እየዘጋን ተመንግሥት እጅ የወደቅነ:: ለሉቱ ቢረዳኝ ብለን ነበር እኛማ:: የተባለውን የርዳታ እህል አግኝቼ ይገፍሳት ሳልደርስ ቀደመችኝ እንጂ» አለ አሁንም በሀዘን እየተብከነከነ::

«ዋሰልኝ አካባቢያችሁ ከፉኛ በድርቅ መጎዳቱን አጫውተሽኛል:: ከተወሰኑ ዓመታት ወዲህ ዝናቡ ወቅቱን ጠብቆ እየዘነበ አይደለም:: ድርቅ ባማያጠቃው አካባቢ መንግስት ቢያሰፍራችሁ ምን ይመስልሃል?» አለው ይነበብ ሁኔታውን እያጠና::

«እትብቴ የተቀበረበትን ቀዬ ለቅቄ !?» አለ ዋሰልኝ ቀና ብሎ በመገረም እያስተዋለው:: «ተሰደድ የሚሉኝ ነፍስ አላጠፋሁ! መንግሥት ይኸነን ከፉ ቀን ያወጣነ መስሎኝ ነው እንጂ! ተሰደድ!? ወይ ፈጣሪ! ጆሮ አይሰማው ነገር የለ!» አለ ዋሰልኝ ቅይም ብሎ:: የይነበብ ግምት ትክክል አልነበረም:: በሚሰቱ ሞት ምክንያት አካባቢውን ይጠላዋል መስሎት ነበር::

«የምትሄደው እኮ በሌላው የአገርህ ክፍል ኢትዮጵያ ውስጥ ነው:: ሁልጊዜ በድርቅ ከምትሰቃዩ መንግሥት ለአንተም ለልጆችህም የተሻለ ኑሮ እንድትኖሩ አስበላችሁ ነው:: አንተ ብቻ እኮ አይደለህም:: ለም ቦታ ተሰጥቷቸው ሰርተው ለመብላት የሚፈልጉ ሁሉ ይሄዳሉ» አለ ይነበብ:: በሌላ በኩል ደግሞ ደርግ የቀየሰው ያልተጠና የሰፈራ ፕሮግራም የዚህ በድርቅ የተጎዳ ሕዝብ ፍላጎት ካልሆነ መሰረታዊ ለውጥ ሊያመጣ አለመቻሉን ከዋሰልኝ ሁኔታ እያስተዋለ::

«ኧረ በሰማም ይበሉ ጌታው! ድህ ባገሩ አይኑር ነው!? ምነው ምን አደረኩዎ! ምን በደልኩዎ! የማይሆነውን! የማልሞከረውን! እሱን አንድዬን አንድ ልብ ሆነን በጠሎት

ብንግጠነው ኧረ ፊቱን ይመልለልናል! ይብላኝ ለአናንተ እንጂ እኛስ ዘንድሮ ዝናቡን ቢለጠን ከጢሳችን ገብተን እናርሳለን፡፡» አለ ዋለልኝ ወደ ቀዬው አሻግሮ እየተመለከተ፡፡

«በል ለዛሬ አንተወው፡፡ አሰቲ አንተም በደንብ አለበህበት እደር፡፡ ነገ እንነጋገርበታለን፡፡» ብሎት ሊሄድ ሲል

«አጉል አይድከሙ ጌታው! አግሬንም አልነቀል! ወቅት ጥሎነ ተመንግሥት እጅ ብንወድቅ በደል አልፈጠምነ፡፡ ደም የተቃባነ ይመለል አገር ሰቃችሁ ተሰደዱ ትሉነ! ማጣት ለካ እሰተዚህን ሰው ያስንቃል! ከችግራችን ሌላ ምን ከፋት ተገኘብነ ኧረ!? ተይሁ ያገሬ መሬት ይብላኝ ጌታው አልለደድም!» አለ ዋለልኝ ድምጹን ዘለግ አድርጎ ይነበብን በትዝብት እየተመለከተ፡፡

ደርግ በግብታዊነት ባወጣው ያልተጠና የሰፈራ ፕሮግራም ማንም ደስተኛ አልነበረም፡፡ እንደ ለመደው በማንአለብኝነት በግዳጅ ተግባራዊ ማድረግ ጀመረ፡፡ እናት የሌላቸው ሕጻናት የያዘው ዋለልኝም እንደ ፎከረው አልቀረም፡፡ የመጀመሪያው የሰፈራ ፕሮግራም ለለባ ሆነ፡፡ ጉልበት አለው የተባለ ርሀብተኛ ሁሉ በግዳጅ ወደ ሰፈራ ጣቢያ ተጫነ፡፡ ቤተ ዘመድ ተነጣጠለ፡፡ ወንድም፣ እህቱ የሄደበት ቀሪው ገበሬ በደርግ መንግሥት ላይ ቂም ቋጠረ፡፡ በወጣው የሰፈራ ፕሮግራም ያላመኑበት እንደ ይነበብ የመሳሰሉ የግብርና ባለሙያዎች ደግሞ በስራቸው ተማረሩ፡፡ ለእንዲህ ዓይነቱ አለከፊ አሰራር ተሳታፊ ላለመሆንና ግፉን ላለማየት ከመንግሥት ሥራ ለመገላገል መንገድ ማፈላለግ ግድ ነው ብለው አመኑ፡፡

ትሩፋትና ይነበብ ሌላው የገጠማቸው አለጊው ነገር ደግሞ ጎንደር ከፍለ ሀገር መደበኛ ሥራን ሰርቶ በሰላም የሚኖሩባት አገር አልሆነችላቸውም፡፡ በፀረ አብዮት ካምፕ ተሰልፈው ደርግን ሲያደሙ የነበሩ ተብለው በምድረ የኢሰፓ ካድሬ ሁሉ በጥርጣሬ ዐይን የሚታዩ ሆኑ፡፡ የሚሠሩት ሥራ ሁሉ እምነት የማይጣልበትና በበጎ የማይተረጎም እየሆነባቸው ተቸገሩ፡፡ አበራሽ እንኳ ሁልጊዜ የተለያየ ጥቆማ እንደሚደርሳት ሳትደብቅ ነግራቸዋለች፡፡ ያደሙትን አብዮት ለመካለና ታማኝነታቸውን ለማሳየት የኢሰፓ አባል መሆን የውዴታ ግዴታ መሆኑን ገልጻላቸዋለች፡፡ ሌላው አማራጭ ደግሞ በኢሰፓ ካድሬዎች ጥርለ ውስጥ ከገቡበት ከጎንደር ከፍለ ሀገር ዘወር ማለቱ እንደሚሻል ደጋግማ አሳስባቸዋለች፡፡ ትሩፋትና ይነበብ ደግሞ ምንም የከፋ ነገር ቢገጥማቸው አበራሽ ያቀረበችውን የመጀመሪያውን ምርጫ መቼም ቢሆን የሚቀበሉት አይሆንም፡፡ ከጎንደር ከፍለ ሀገር በዝውውር ወደ ሌላ ከፍለሀገር ለመሄድ ደግሞ በቀላሉ የሚሳካ አልሆነም፡፡ በዚያ ላይ ቤተሰቡ ለፍቷል፡፡ ይነበብ ከተፈታ በኋላ ሁለት ልጆችን ጨምረዋል፡፡ ምኒልከንና ሀናን፡፡ ሕይወት ቀላል አልሆነላቸውም፡፡ ይበልጥ ሥጋት የሆናቸው ደግሞ ጎንደር ከፍለ ሀገር የያዙትን ሥራ ይዘው እየሰሩ በሰላም ለመኖር ዋለትና ማጣታቸው ነበር፡፡ «ነገ ምን ይደርስብን ይሆን» የሚለው የዘወትር ሥጋታቸው ሆኖ ያባንናቸዋል፡፡





ለጊዜውም ቢሆን መፍትሄ ይሆናል ብለው ያሰቡት አንዳቸው እንኳን ወደ ከፍተኛ ትምህርት ቢገቡ የሚሻል መሆኑን አምነው ተቀብለውታል፡፡ ለዚህም ጥርለን ነከሶ ማጥናት አማራጭ የሌለው መንገድ ነው ብለው ቆርጠው ተነስተዋል፡፡

የግብርናው መስሪያ ቤት ተጠሪ ቀናና ሥራ ወዳድ ሰው ነበር፡፡ ይነበብ ትጉ ሠራተኛ በመሆኑ ተግባብተዋል፡፡ ሥራውን በአግባቡ ከተወጣ በቀኑ የትምህርት ከፍለ ጊዜ እንዲመዘገብና በሳምንት የተወሰኑ ቀኖች እንዲማር ፈቅዶለታል፡፡ ይነበብም ቢሆን ስሙ መመዝገቡ እንጂ ትምህርት ቤት ሄዶ ከሚማርበት ቀን ይልቅ የማይሄድበት ይበልጣል፡፡ ጠንክሮ ሥራውን እየሰራ ጥናቱን ከትሩፋት ጋር ቢጋራ ተያይዘውታል፡፡

መቼም በዓለም ላይ አንዳንድ ምቀኛ ሰው አይጠፋም፡፡ የሌላው እድገትና መለወጥ እንቅልፍ የሚነሳው በሽተኛ፡፡ ከይነበብ ጋር አብሮ የሚሰራውና እንደውም ከከፍሉ ሰራተኞች ሁሉ ጥብቅ ወዳጅ መስሎ የሚቀርበው ባይከዳኝ የይነበብ የቀን ትምህርት ውስጥ ውስጡን በቅናት ያሳርረው ኑሯል፡፡ ጎንደር ከተማ በተመላለሰ ቁጥር ለበላይ አለቆቹ ሥራ እየተበደለ መሆኑን ሳያሳብቅና ሳያመለከት አይመለስም ነበር፡፡

አንድ እርብ ቀን አለቃውና ይነበብ ፖሊስ ጣቢያ ለጥያቄ ይፈለጋሉ፡፡ ፖሊስ ጣቢያ ሲደርሱ ጉዳዩ ይነበብ በቀኑ የትምህርት ከፍለ ጊዜ መማሩ ነበር ወንጀላቸው፡፡ የከፍለ ሀገሩ የግብርና መስሪያ ቤት ጥቆማ ደርሶት የምርመራና የማጣራት ሥራ እንዲሰራ ደብዳቤ መላኩን ይገልጽላቸዋል የአውራጃው መርማሪ ፖሊስ፡፡ የመንግሥትን መመሪያና ደንብ እንዲያለፈጽም የተቀመጠ አለቃ እንድ የከፍሉን ሰራተኛ በምን ምክንያት በቀኑ የትምህርት ከፍለ ጊዜ እንዲማር ሊፈቅድ እንደ ቻለ በጥያቄ ያጣድፈው ጀመር የግብርናውን ኃላፊ፡፡ ይነበብ ጠንካራ ሰራተኛ መሆኑንና ስራ እንዳልተበደለ በአጽንኦት ገለጸ፡፡ በቀኑ የትምህርት ከፍለ ጊዜ ስሙ መመዝገቡ እንጂ የቱንም ያህል ቀን ሥራው ላይ እንዳልቀረ ሊያስረዳውና ሊያሳምነው ጣረ፡፡ መርማሪ ፖሊሱ ግን ሊቀበለው አልቻለም፡፡ የመንግሥትን መመሪያ መጣለ መሆኑን አንቀጽ ጠቅሶ እየገለጸ ወንጀሉን አከበደው፡፡ ሁለቱንም ፖሊስ ጣቢያ እንዲታሰሩ አደረጋቸው፡፡ ከአውራጃው ኢሰፓ ጽህፈት ቤት በመጣ ቀጭን ትዕዛዝ አለቃው ወዲያውኑ እንዲፈታ ሆነ፡፡ ይነበብ ግን የግል ጥቅምን በማለቀደም የመንግሥትን መመሪያ በመጣስና ሥራን በመበደል ወንጀል ተከሶ እንዲያድር ተወሰነ፡፡ አወደድ ባይ የኢሰፓ ካድሬ ሁሉ ጉዳዩን ከአለፈ ታሪኩ ጋር እያይዘው ወንጀሉን አሳድገው አሳድገው ሰማይ ጥግ አደረሱት፡፡ በአጃቢ ወታደር ተነድቶ ለዳግም እስራት ወደ ጎንደር ተላከ፡፡ የአስራ ሁለተኛ ከፍል መልቀቂያ ፈተናውን ከወሰደ በኋላ መሆኑ እንደ አንድ ድል ቆጠረችው ትሩፋት፡፡ ከስድት ወር እስራት በኋላ ተፈቶ ሲመጣ የማትሪክ ጥሩ ውጤቱም አብሮ መጣለት፡፡ ምድቡ ደግሞ ስድስት ኪሎ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሆነለት፡፡ ትሩፋት ሊመረቅ አንድ ዓመት ሲቀረው ዝውውሯን ሞልታ ቤተሰቧን ጠቅልላ አዲስ አበባ ገባች፡፡

## አዲስ አበባ

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ ልደት አዳራሽ በተማሪዎችና ቤተሰቦታቸው እንዲሁም ጥሪ በተደረገላቸው እንግዶች ግጥም ብሏል፡፡ የሚጠበቁት የኢሰፓው ፕሬዝዳንት ናቸው፡፡ ድንገት «መጡ-- መጡ--» የሚል ሹከ ሹከታ አዳራሹን ሞላው፡፡ ዐይኖች ሁሉ ወደ በሩ ተወረወሩ፡፡ አጭር ናቸው--- አፍሪካዊ መልከ ያላቸው፡፡ በደማቅ ሰማያዊ ካኪ ልብሰ ሽከ ብለዋል፡፡ ቆፍጥን ባለ አረማመድ ወደ መድረኩ አመሩ፡፡ በአዳራሹ ውሰጥ ያለው ሰው በሙሉ በፍርሀት ይሁን በአከብሮት ብድግ ብሎ በጭብጨባ ተቀበላቸው፡፡ ትሩፋትም አጨብጭባለች፡፡ የእሷ አቀባበል የለየት የፍርሀት ነው፡፡ መድረኩ ላይ እንደ ወጡ ሕዝቡን እንዲቀመጥ ጋበዙ፡፡ ጭብጨባውም ቆመ፤ ደደራሹም ፀጥ ረጭ አለ፡፡ ፍርሀት የነገሰበት ድባብ አዳራሹን ሞላው፡፡

«ሕዝብ በፍርሀት ሳይሸቆጠቆጥ ወዶና ፈልጎ የሚያከብረው የአገር መሪ መቼ ይኖረን ይሆን?» አለች ትሩፋት በውሰጧ፡፡ የኢሰፓው ፕሬዘዳንት በፕሮግራሙ መሪ ብዙ ተወደሱ፡፡ በብዙ አከብሮት ተጋብዘው ወደ መድረከ ሲያመሩ አሁንም ከፍተኛ ጭብጨባ አጅቧቸው ነበር፡፡ ቆሞ በጭብጨባ የአሞገሳቸውን ታዳሚ እንዲቀመጥ ጋብዘው ረዘም ያለ ንግግር አደረጉ፡፡ ትምህርት የአንዲት አገር የእድገት መሰረት መሆኑን በአጽንኦት ተናገሩ፡፡ አብዮቱ ሰለ አሰገኛቸው ድሎች--- የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ሰለ ተጎናጸፈው ዲሞከራሲያዊ መብቶች--- ሰለ ተሻሻለው ኢኮኖሚያችን--- ሰላደገውና ሰለ ተሰፋፋው የትምህርት ደረጃችን.... በፕሬዘዳንቱ ንግግር ያልተጠቀሰ ነገር የለም፡፡ ሁሉም ነገር እድጎ--እድጎ ሰማይ ጥግ ደርሷል፡፡ ከኢሰፓው ፕሬዘዳንት ንግግር ቀጥለው ሌሎች የሚመለከታቸው ባለሰልጣናት በየተራ ንግግር አደረጉ፡፡ ሁሉም እየተነሱ የኢትዮጵያ ፕሬዘዳንት፣ የኢሰፓ ዋና ጸሐፊ፣ የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ፣ የኢህድሪ ሊቀመንበር.... በሰልጣን ላይ ሰልጣን የደራረቡትን የአገሪቱን ገዢ ብልሕነትና አሰተዋይነት የተሞላበት ቆራጥ አመራር አደነቁ! አሞገሱ! የሳቸው ብልህነትና አሰተዋይነት የተሞላበት አመራር ባይኖር ኖሮ ዛሬ እብዮታችን በፀረ አብዮተኞች ሊቀለበስ እንደሚችል በአጽንኦት ገለጹ፡፡

የእሳቸው ጥበብ የተሞላበት አመራር ባይኖር ኖሮ አገሪቱ በዘረኞችና በጎጠኞች ብትንትኗ ሊወጣ ይችል እንደ ነበር እንባ እየተናነቃቸው ምስከርነታቸውን ሰጡ፡፡ ነገ በሰልጣን ሊያላድጋቸው ወይም ከሰልጣናቸው ሊያቆያቸው የሚያሰችላቸውን ንግግር ታሳቢ በማድረግ ሰውየውን ከሚሸከሙት በላይ ከንቱ ውዳሴ ጫኗቸው፡፡

ወደ አምሰት ሰዓት ገደማ የተለመደው የተማሪዎች የምረቃ ስነ-ሰርዓት አበቃ፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች በተለይ ገና በአፍላ ወጣትነት እድሜ ላይ የሚገኙ ተመራቂዎች ከፕሬዝዳንቱ ጋር ፎቶ ለመነሳት ሲሽቀዳደሙ ተመለከተች ትሩፋት፡፡ ይነበብን እጁን ያዝ አድርጋ ወደ ኋላ ጎተት አደረገችው፡፡ ዐይን ለዓይን ተጋጩ፡፡ ተግባቡ፡፡ ከፕሬዝዳንቱ ጋር ፎቶ





አይነሳም፡፡ ለየትኛው መልካም አሰተዳደራቸው መታሰቢያ ሊሆንቸው ነው የላቸዉ ፎቶ? የኢሰፓው ፕሬዝዳንት በመጡበት አኳሃን ግቢውን ለቀው ሄዱ፡፡ ትሩፋት እንዳች ሸከም ትከሻዋ ላይ የወረደላት ይመሰል ቅልል አላት፡፡ ተመራቂ ሁሉ ከወዳጅ ዘመድ ጋር ፎቶግራፍ ለመነሳት የሰድሰት ኪሎ ግቢ በሰው ተጥለቀለቀ፡፡ ከዚህም ከዚያም ፎቶ የሚነሳው ተመራቂና ቤተሰብ ይርገረጋል፡፡

«ከጓደኞችህ ጋር የምትነሳው ፎቶ ካለህ ተነሳና እንውጣ፡፡ ራሔል ልጆቹን ይዛ ውጭ እየጠበቀችን ነው» አለች ትሩፋት፡፡

«ለፎቶግራፍ ግቢው ውሰጥ መግባት ይቻል ነበር እኮ ለምን እንዲገቡ አናደርግም፡፡ አለ ይነበብ፡፡

«እንጠፋፋለን ብዬ ውጭ ግቢው በር ላይ ነው ጠብቁኝ ያልኳቸው» አለች ትሩፋት፡፡ ይነበብ ከጓደኞቹ ጋር ፎቶ ተነሰቶ ከጨረሰ በኋላ እጅ ለእጅ ተያይዘው ግቢውን ለቀው ሊወጡ ሲሉ

«ቆይ ጋዎኑን ላውልቀው» አለ ይነበብ ቆቡን ከጭንቅላቱ ላይ እያነሳ፡፡

«እንዴ ለምን ታወልቀዋለህ? ለብሰኸው ትንሽ ተንጎራደድ እንጂ ትምህርት እኮ እንደ ገና እንድትታሰር ምከንያት ሆኖ ያልተጠበቀ ሌላ መሰዋዕትነት አሰከፍሎናል፡፡ ከእውቀቱ ባሻገር ለከፈልነሰት መሰዋዕት ከብር ሊባል የምትለብሰው እንደውም ለሁለት ቀን ነው፡፡ አለች ትሩፋት ጋዎኑን እየነካካች፡፡ ደሰ ብሏታል፡፡

«የባታ ወህኒ ቤት የሰድሰት ወር ቆይታዬን ሁለት ቀን ሙሉ ይህን የከብር ጋዎን ለብሼ እንዳወራርደው ነው ፍላጎትሽ?» አለ እየላቀና ወደ ራሱ ጥግት አድርጎ እያቀፋት፡፡

«አሁን ላይ ሆኜ ሳሰበው መታሰርህ ለበጎ ኖሯል ይነበብ፡፡ በቀኑ የትምህርት ከፍለ ጊዜ መማርህ ለበብ ሆኖ ለዳግም እሰራት ባትዳረግ ኖሮ ይህን ሁሉ ቤተሰብ ይዘን ቀርጠን አዲሰ አበባ መግባት ይቸግረን ነበር፡፡ አለች ትሩፋት ከላይ እሰከታች እየተመለከተችው፡፡ ጥቁሩ የመመረቂያ ጋዋኑ ከረጅም ቁመቱ ጋር ግርማ ሞገሰ አጎናጽፎታል፡፡

«እውነት ለመናገር ለሁለተኛ ጊዜ መታሰሬ ጎንደር ከፍለ ሀገርን የመልቀቂያ ጊዜውን ሳያፋጥነው አልቀረም፡፡ የአበራሽ ማሰፈራሪያና ምከር ለበሰ ማሰጠንቀቂያ ደግሞ ተጨማሪ ግፊት ፈጥሯል፡፡ ጊዜው ይረዝም እንደሆን እንጂ እኔም አንቺም ለመማር ካለን ፍላጎት የተነሳ አዲሰ አበባ መግባታችን ግን አይቀርም ነበር» አላት፡፡ በግራ እጁ የ(ዘበችውን የእንኳን ደሰ አለህ አበባ ይዞ በቀኝ እጁ ወደ ራሱ ጥግት አድርጎ እያቀፋት፡፡ ወደ ጉያው ሽጉጥ አለች፡፡ ለሚያያቸው አዲሰ የተዋወቁ ፍቅረኛሞች ይመስላሉ፡፡ ይነበብ በመመረቁ በጣም ደሰ ብሏታል ትሩፋት፡፡ እሷም ነገ እንደምትማር እርግጠኛ ናት፡፡ ታናናሾቿን

እስተምራሰች:: ድልነሳ ከኢሕአፓ መበታተን በኋላ በሱዳን በኩል አድርጎ አሜሪካ ገብቷል:: ልጆቿ ሰትምህርት ደርሰዋል:: ከእንግዲህ እንዳትማር የሚያግዳትት ብዙ እንቅፋት ከፊቷ የለባትም:: አዲስ አበባ መግባቷ ደግሞ ነገሮችን አቅልሎላታል:: ነጋ ጠባ በሆነ ባልሆነው ከመታሰር እሷም ይነበብም እርፋዋል:: በማታው ከፍሰ ጊዜ ሰመማር አድሉ ይኖራታል:: የደርግን መንግሥት ሰመጣል የሚያደርጉት ትግል የተገታ መሆኑ ውስጥ ውስጡን ቁጭት ቢኖርባቸውም ምንም ማድረግ ግን አልቻሉም:: ሁለቱም ፊታቸውን ወደ ቤተሰባቸው መልሰዋል:: ሕይወት ትግሏን ቀጥላለች:: በአዲስ አበባ ከተማ መሰረቷን ሰመጣል እየተውተረተረች ትገኛለች::

******





## ማነህ ባለተራ

ሰሞኑን የሚወራው ወሬ ሁሉ ደግሞ ያስፈራል:: ወያኔዎች ይህን ቦታ ተቆጣጠሩ--- ሻብያ እስመራ ከተማን ሊቆጣጠር በቅርብ ርቀት ላይ ይገኛል.... የሚነፍሰው ነፋስ ሁሉ የደርግ መንግሥት ሊወድቅ ገደል ጫፍ ላይ የተንጠሰጠሰ መሆኑን ያመላከታል:: አዲስ አበባ ተጨንቃለች:: የሰውጥ ነፋስ ዳግም ስቅዝ አድርጎ ይዟታል:: ከየከፍለ ሀገሩ እየሸሸ የሚመጣው ሕዝብ ብዛት ከተማዋ ውስጥ እንደ ጉንዳን ይርመሰመሳል:: በተሰይ ከኤርትራ፣ ከትግራይ፣ ከጎንደር፣ ከጎጃምና ከወሎ እየተነሳ የሚመጣው የመንግሥት ሠራተኛ ቁጥር ለደመወዝ አከፋፈል እስኪያስቸግር ድረስ በየእለቱ ይጨምራል:: ከሕዝቡ ፊት ላይ የሚነበበው ጭንቀትና ስጋት ብቻ ነው:: ሰው ሁሉ ሰጊዜው የሚሆን ቀለብ ለመግዛት በየገብያው ይሯሯጣል:: ያገኘውን የእለት ምግብ ሁሉ በተባሰው ዋጋ እየገዛ በቤቱ ጓዳ ይደብቃል::

ትሩፋት እሷም እንደ ሕዝቡ ለቤተሰቧ ፈጣን የእሰት ምግብ የሚሆን እንዳንድ ነገር መግዛት እንደሚገባት እምናለች:: ፈጣን ምግቦችና ጋዝ ከቤቷ ቢኖሩ አይከፋም:: ይህንን እያሰበች ከስራዋ ወጥታ ወደ ቤቷ ስትሄድ የግንቦት እናት የምትበሳ ፀሐይ ፊት ሰፊት አገኘቻት:: ጃንጥላዋን ከቦርዋ አውጥታ ከመዘርጋ ድንገት ኃይለኛ አውሎ ንፋስ ተነስቶ ጃንጥላዋን ወደ ላይ ገሰበጠው:: ቀሚሷንም ከላይዋ ላይ ሊያነሳው ደረሰ:: በአንድ እጇ ቀሚሷን ወደ ታች እየጎተተች ስትታገል ጃንጥላዋ ከእጇ ላይ አምልጦ አየር ላይ ተንሳፈፈ:: ቀሚሷን ጭምድድ አድርጋ እንደ ያዘች እንጋጣ ተመለከተችው:: ቀስ እያሰ ንፋሱ መብረድ ሲጀምር ጃንጥላዋም ቁልቁል ወርዶ መሬት ሰመሬት ተሽከረከረ:: አንድ ተማሪዋ የሆነ ልጅ ደርሶ እንደ ምንም ተሯሩጦ ያዘውና አምጥቶ ሰጣት:: አመሰግና ስትቀበለው:: ጃንጥላው ግን እንዳይሆኑ ሁኖ ተሰባብሯል:: ተጠግኖ እንኳን ጥቅም ላይ የሚውል አይደሰም:: እቤት ስትደርስ ቆርቆሮ እጥሩ ላይ ሸጎጥ አድርጋው ገባች:: የከፉ ቀን ቀለቧን ሰመግዛዛት ዘንቢሏን እንጠልጥላ ተመልሳ ወጣች:: ገበያ ውስጥ ስትገባ ሁሉም ነገር ከገመተችው በላይ ውድ ሆኗል:: ሕዝቡ ገንዘቡን ከየት አመጣው? እስኪያሰኝ ድረስ ነጋዴው የጠራውን ዋጋ ከፍሎ ይገዛል:: ትሩፋት ሰጊዜው በጣም የሚያስፈልጉ የመስሳትን ብቻ ገዛች:: ከገበያ መልስ ይነበብ ልጆቹን ሊያስጠና አገኘችው:: ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ገበያ የሄደችበትን ምክንያት ስትነግረው

«ከፉ ቀን አይምጣ እንጂ ከመጣ እኮ የገዙትንም መብላት የማይቻልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ትሩፊ--- ዝም ብሰሽ ነው የደከምሽው» አላት:: ወሬው እገር ሊፈታ ደርሷል:: አዲስ አበባ ሰውጥ ያረገዘው ሰማይ ተደፍቶባት በወሬና በስው ብዛት ልትፈነዳ ደርሳለች::

የደርግ እምባገነን መንግሥት ኢሕአፓን የመስለች ግዙፍ አገር አቀፍ ሕብረ-ብሔር ድርጅት በራሷ የውስጥ ችግር ጭምር ብትወድቅሰትም እንቅልፍ የሚነሳው የውስጥ ጠላት

አላጣም፡፡ ኢሕአፓን እንዲወጉለትና እንዲያዳክሙለት ራሱ ውስጥ ውለጡን ያለታጠቃቸውና ያጠናከራቸው «አንገንጠል» ባይ የጎጥ ድርጅቶች እንቅልፍ ነስተውታል፡፡ በተለይ በአገሪቱ ለሜናዊ ክፍል የተነሱት የጎጥ ድርጅቶች የጎን ውጋት ሆነውበታል፡፡ እንደ ተራ ሽፍታ «ወንበዴ--ተገንጣይ-- ጠባብ ብሔርተኛ...» እያለ ይንቃቸው የነበሩ ድርጅቶች ጉያው ውስጥ ደርጅተው አፍንጫው ስር ጎልብተው ሰንገው ይዘውታል፡፡ እያደር እየተባባለ የሄደው ብልሹ አመራሩ የሕዝቡን ልብ እያሻከረው መጥቷል፡፡ ገበሬው በሞፈር ዘመት የመሬት ድልድል መድሎ ምክንያት በመንግሥት ላይ አኩርፎ ፊቱን አዙሯል፡፡ ሕዝበ-- ኢትዮጵያ ቀይ ኮከብ ዘመቻ---- አረንጓዴው ዘመቻ--- የእናት አገር ጥሪ ዘመቻ:.. እየተባለ አፈር ግጦ ያሳደገው ልጁን ከጉያው በመነጠቁ አዝኖ ቂም ቋጥሮ ቀን እየጠበቀ ተቀምጧል፡፡

በለፈራ፣ በመንደር ምስረታ ምክንያት ከኖረበት ቀዬ የቤቱ ጣራ አላዩ ላይ ፈርሶ በመፈናቀሉ የደርግ መንግሥት እንዲወድቅ ጧት ማታ ጸሎት ላይ ያለው አርሶ አደር የሚጠብቀው ትንሽ ሰበብ ነበር፡፡ ሽፍታ እያሏ የናቃቸው የሕወሀትና የሻቢያ ታጣቅዎች ጉሮሮው ላይ ሲቆሙ ወደ ፊት እየገሰገሱ አገሩን ሁሉ ሲቆጣጠሩት ይህ የተከፋ ባላገር ውሻው እንዳይጮህ ከጎተራ የአከተተ ኮሽታ ሳያሰማ መንገድ እየመራ ተባበራቸው፡፡ ወታደሩ በማያባራ ጦርነት በመሰላቸቱ--- በበላይ አለቆች የተዛባ አመራር በመበሳጨቱ መዋጋቱን ትቶ መሳሪውያን ዘቅዝቆ እንደ ሞኝ ዝም ብሎ ተማረከላቸው፡፡ ማንም ሳያቆማቸው እየጎሰገሱ ምህል.አገር ገቡ፡፡ አዲስ አበባን ተቆጣጠሩ፡፡ በአነሱ ብርታት ሳይሆን በደርግ ብልሹ አስተዳደር ሳይጠበቁ በአቋራጭ መንግሥት ሆነው ቁጭ አሉ፡፡ ለቁራሽ መሬት ሲታገሉ እነሱም ሳያሰቡት ሕዝብም ሳይጠብቀው የታላቋ አገር የኢትዮጵያ ባለቤት ተረኛ ገዥ ሆነው ሚኒሊክ ቤተመንግሥት ዘው ብለው ገቡ፡፡

«በአናትህ እነዚህ ጭባዎች ናቸው ግዙፉን የደርግ ወታደር ያንበረከኩት? የሚታመን ነገር እኮ አይደለም» አለ አንድ ወጣት የተንጨበረ ጸጉሩን በግራ እጁ እየገመደ፡፡ እድሜው ወደ ሃያዎቹ አጋማሽ ይሆናል፡፡

«ሲያስጠሉ! ምን ይመስላሉ!? የጸጉራቸው መንጨብረር--ልክ ያንተን ይመስላል» አለ ሌላው ወጣት፡፡ አጠገቡ የተቀመጠ ጓደኛውን ቀና ብሎ ወደ ጸጉሩ እየተመለከተ፡፡ አራት ኪሎ ክፎቶ ፒው ፊት ለፊት ባሉት ድድ ማስጫ ደረጃዎች ላይ ምንጊዜም ሰው አይጠፋም፡፡ ብዙዎቹ ሊስትሮዎች ያን አካባቢ አይለቁም፡፡ ከገጠር የመጡ ልጅ አግር ሎቶሪ አዟሪዎች አንዱ ሲሄድ ሌላው እየተተካ መደዳውን የተቀመጠውን ሰው ሎተሪ ግዙ እያሉ መወትወታቸው የተለመደ ነው፡፡ ደከተማ አውቶብሶች እዚሁ ሰው ያወርዳሉ-- ሰው ያሳፍራሉ፡፡ ታክሲዎች ይርመሰመሳሉ፡፡ የሰው ብዛት ምንጊዜም ገበያ እንደ መሰለ ነው፡፡ በተለያየ የእድሜ ክልል የሚገኙ ሰዎች ከደረጃው ላይ መደዳውን ተቀምጠው አዲስ መጤ ገዥዎቻችን ይተቻሉ፡፡ አብዛኛው የአዲስ አበባ ኗሪ ከጅምሩ አልወደዳቸውም፡፡ ለጥላቻው





ምክንያት የሚጠይቅ ቢኖር ኖሮ ያኔ በቂ ምክንያት አልነበረውም፡፡ አሁን ቢሆን እንኳ ግብራቸውንም አይቷል፡፡ አንድ ሚሊዮን ምክንያት መስጠት ይቻላል፡፡

«እናቴ ትሙት ወንድ ናቸው! አላየህም ያንን ሁሉ ክርፋፋ ወታደር እንደ ከብት ሲነዱት» አለ የመጀመሪያው ተናጋሪ ባለ ጨብራራ ጸጉሩ ወጣት፡፡

«ያኔ ለብሔራዊ ውትድርና በቀበሌያችን የተመለመልን ጊዜ ቁም ሳጥን ውስጥ ተደብቀን ባናመልጥ ኖሮ ይህን ጊዜ ከነዚህ እንደ ከብት ከሚነዱት ወታደሮች መሀከል አኛም ነበርንበት» አለ ሁለተኛው ልጅ፡፡

«የማትሪክ ውጤት መጥቶልኝ ኮሌጅ አልገባሁ---ወይ ሥራ ይዤ ከእናቴ ትከሻ ላይ አልወረድኩ---ያኔ ቁም ሳጥን ውስጥ ተደብቄ ከምቀር በሄድኩና በሞትኩ ይሻለኝ ነበር፡፡ እናቴ እንዲህ በቁሜ እያለሁ ከምታለቅሰልኝ ለናት አገሬ ሰዋደቅ ብሞት ኖሮ ሌላው ቢቀር ቡናና አድር ላይ በጓደኞቿ ፊት "የጀግናው እናት' እያለች ትፎክር ነበር» አለ፡፡ ኑሮ ያንገሸገሸው ይመስላል፡፡

«ሳትሞት ቀርተህ-- እንዲህ እንደምናያቸው ምርኮኛ ወታደሮች እየተንገላጀጅህ ብትመጣስ? በቁምህ የምታንቀሳፋ መሰለህ በአንድ ጨበሪያም ሕወሀት ወያኔ እንደ በግ ለትንዳ ቢያዩህስ? ካልክስ የሞት ሞት ይሉሀል ይኸ ነው፡፡ እናት እንደ ልጇ ሽንፈት የሚያሳዝናት ነገር የለም፡፡»

«በእነዚህ ጭባዎች ከምማረክ ደግሞ-- እናቴ ትሙት! ሺህ ጊዜ ብሞት እመርጣለሁ!» አለ ያው ባለ ጨብራራ ጸጉሩ፡፡

«ፓ! ጉርኛ ነህ እባክህ! አላወቅኸውም እንጂ አሁንም እኮ ያው ምርኮኛ ነህ፡፡ ማን ሊገዛህ ምኒልክ ቤተመንግሥት የገባ መሰለህ? እነዚሁ ክርፋፋ ጨበሪያም ወያኔዎች እኮ ናቸው፡፡ ግን እውነትህን ነው፡፡ የተማረከው ጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው፡፡ ለዚህ ነው ያልተሰማህ፡፡»

«ቆይ ቷያሏህ ምንም ያህል ጊዜ አይቆዩም፡፡ በምንም መመዘኛ አገር የሚያስተዳድሩ አይደሉም፡፡ አልቻሉበትም፡፡»

«እነዚህ የጫካ ተራ ሽፍቶች ጊዜ ለጣቸው! ምን ይደረግ!»

«ደግሞ እኮ አልም ያሉ ጀዝባዎች ናቸው፡፡ ልብለ ታጥቦ የት ቦታ መድረቅ እዳለበት እንኳ አያውቁም፡፡ አታይም የተከበረው ፓርላማ የእነሱ የውስጥ ሱሪ ማሰጫ ገመድ ሆኖ ክብሩን አጥቷል እኮ፡፡ በፎቁ በረንዳ ላይ እንደ ቋንጣ አንጠልጥለው -አንጠልጥለው መጫወቻ

አደረጉት፡፡ ሞገሱን አሳጡት» አለ በቁጭት ያንኑ ጩብራራ ጸጉሩን እየገመደና ወደ ፓርላማው እየተመለከተ፡፡

«አትፍረድባቸው የሚያውቁት ቃታ መሳብ ብቻ ነው፡፡»

«ተዋርደው አዋረዱን፡፡ ከተማ ሲገቡ ሊያጋጥማቸው ስለሚችለው ደንብና ሰርዓት አንድም ነገር ያላገናዘቡ ተራ ሽፍቶች መሆናቸውን እኮ ነው ያጋለጡት፡፡»

«አርግጠኛ ነኝ የደርግ መንግሥትን ጥለው አዲስ አበባን የሚቆጣጥሩ አልመሰላቸውም ነበር፡፡ ትግራይን ለመገንጠል ብቻ ሲሙኙ እድል ፊቷን መለሰችላቸውና እያንከበከበች አምጥታ ሳያስቡት ምኒልክ ቤተመንግሥት ዶለቻቸው፡፡ ያልጠበቁት ሲሳይ ሲያጋጥማቸው ድንብርብራቸው ወጣ፡፡ የሚይዙትና የሚጨብጡት ጠፋባቸው፡፡ በጠባቡ የለኩት ጥብቆ ለፋባቸውና ተቸገሩ፡፡»

«እውነት ብለሀል፡፡ ድንገት የተገኘ የመቶ ሺህ ብር ሎተሪ እንኳን ያስደነግጣል፡፡ አንኳን ኢትዮጵያን የምታክል ትልቅ አገር! የሚገርመው ደግሞ የመጀመርያው ሰሞን መሰሳለላቸውና ያሳዩት የነበረው ፀባይ ለጉድ ነበር፡፡ በየመንገዱ ሕዝቡ ሲሰድባቸው፣ ሲያንቋሽሻቸውና ጢቅ ሲልባቸው አንኳ ትንፍሽ አይሉም ነበር፡፡»

«እሱ እንኳን ጅብ እስኪይዝ ያነከሰ ነው ነገሩ፡፡ አንገቱን የሚደፋና የሚቅለሰለስ ሰው ውስጠ አጥፊ ነው ወዳጄ 'ጠርጥር ከገንፎም አለ ስንጥር' ተብሏል፡፡»

«የሆኑ ድግምታሞች ናቸው፡፡ ሲመጡ አንዲት ነጭ አህያና አንድ ጥቁር ፍየል ነው እሉ ይዘው የገቡት፡፡ ያፍዝ ያደንግዝ አስደግመው ነው እሉ የደርግን ወታደር እንዲህ በጅምላ የነዱት፡፡ እውነትም የሆነ ድግምት ነገር ሳይኖራቸው አይቀርም፡፡ በወታደሩ ላይ ብቻ አይደልም በእኛም ላይ ደግመውብናል፡፡ በምናምን አደንዝዘውናል፡፡ እንዲህ እየጠላናቸው ከተማችንን ሲወሩ የሌላ ሕዝብ አገር እንደሚወሩ ሁሉ እጅ አግራችን አጣጥፈን አፋችንን ከፍተን ባልተቀበልናቸውም ነበር» አለ ያው ባለ ጩበሬ ጸጉር በቁጭት፡፡

«ድግምትና አስማት እንኳ የውድቀት መሸፋፈኛ-- የጥፋት ማላከኪያ ምከንያቶች ናቸው፡፡ እውነታው ግን ወታደሩ በወያኔዎች ተሸንፎም አይደለም፡፡ ማብቂያ በሌለው ጦርነት ውስጥ መሆኑ ሰልችቶት ነበር፡፡ መሳሪያ ይዞ ሳይተኩስበት ዝም ብሎ የተነዳላቸው፡፡ ለደርግ መንግስት ያለውን ጥላቻና ተቃውሞ ማሳየቱ ነበር፡፡ ግን ቢዋጋ ይሻለው ነበር፡፡ ከዚህ ሁሉ ውርደት አይብሰበትም ነበር፡፡»





«ወታደሩን እንኳ ይበለው! ሽንጡን ገትሮ መዋጋት ሲችል አይወርዱ ውርደት ተከናነበ፡፡ የሚያሳዝነው አገሪቱም ተዋርዳ ከማይሆን ቅርቃር ውሰጥ መግባቷና በዘረኞችና በጎጠኞች እጅ መውደቋ ነው ትልቁ ጦስ፡፡»

የደርግ መንግሥት ባልጠበቀውና ባላሰበው ጊዜ «ጎጠኛ-- ወንበዴ ሽፍታ» እያለ በናቃቸው ቡድኖች ተሸንፎ ወያኔ አገሪቱን የተቆጣጠረ ሰሞን በየድድ ማስጫው ብቻ ሳይሆን በየትም ቦታ ወሬው ሁሉ ይኸው ሆኖ ነበር፡፡

ቀንን ቀን እየወለደው ሁኔታዎች ሁሉ እየተለዋወጡ መጡ፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የተለወጠለት ነገር አልነበረም፡፡ የጥንት የጥዋቱ አኗኗር መልኩን ሳይለውጥ ያው እንደ ነበረ አለ፡፡ መታሰር መፈታትም አልቀረለትም፡፡ የደርግ ባለስልጣናትና የኢሰፓ አባላት ሁሉ በያሉበት እየተለቀሙ ታሰሩ፡፡ ጎንደር ውስጥ ከታሰሩት የደርግ ባላስልጣናት አበራሽ አንደኛዋ ነበረች፡፡ ቆይቶም እድሜ ልክ ከተፈረደባቸው መካከል አንዷ እሷ ሆነች፡፡ ትሩፋትና ይነበብ ከአዲስ አበባ ተጉዘው ጠይቀዋታል፡፡ ትሩፋት ታሰራበት ከነበረበት ባታ ወህኒ ቤት አስጠርተዋት ስትወጣ የባሕር አሳ የሚመስለው ገጽታዋ ገርጥቶ ከስታ ሞራሏ ሁሉ ወድቆ ነበር፡፡ ያ እንደ ፓውዛ ያበራ የነበረው ዓይኗ ፈዞ ትካዜ ይነበብበታል፡፡ ሁለቱም በቻሉት መጠን ሊያጽናኗት ሞከረዋል፡፡ እሷ ግን ተስፋዋ ሁሉ ከውስጧ መከኗል፡፡ በእነሱ አቅም ማድረግ የሚገባቸውን ሁሉ እንደሚያደርጉላት ቃል ሲገቡላት እንባዋን መቆጣጠር አልቻለችም፡፡ የመለያያ ሰዓቱ ደርሶ ተሰነባብተው ሲለያዩ ሁሉ ጥልቅ ሀዘንና ትካዜ ውስጥ ነበረች፡፡ ትሩፋት በተለይ ብቸኛ በመሆኗ ከልቧ አዘነችላት፡፡

ትሩፋትና ይነበብ ጎንደር ከተማን ያገኟት ልክ እንደ ደርግ ጊዜው ዛሬም ጭንቀት ውስጥ ሆና ነው፡፡ አሳሪ የነበሩት ታስረው የእነሱም ቤተሰቦች ሰንቅ በማመላለስ እየተንገላቱ ይገኛሉ፡፡ ዋጋ እንኳ አብደቷ ብሶባት ልብሷን ጥላለች፡፡ ትሩፋት ቆም ብላ በሀዘን ተውጣ ተመለከተቻት፡፡ ያልሰበሰበችው ቆሻሻና ቅራቅንቦ ነገር የለም፡፡ ቁርና ሀሩር የሚፈራረቅበት ከሲታ አርቃን ገላዋ አይሆኑ ሆኖ ጠቁሯል፡፡ ለማንም ያላዘነችውን ያህል አዘነችላት፡፡ «ምነው መከብብን የበላ ቀይ ሽብር በልቷት በነበር» ስትል ሞቷ ይሻላት እንደ ነበር ደጋግማ አሰበች፡፡ ከሀሳቧ ስትመለስ ይነበብ እየጠበቃት ነው፡፡ የመልስ ጉዞ ትኬት መቁረጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ጎንደር ከተማ የጥንት ለዛዋ ጠፍቷል፡፡ በደስታና በፍቅር የሚውሉባትና የሚያድሩባት ከተማ አልነበረችም፡፡ የሚያውቋቸውን ወዳጅ ዘመዶቻቸውን እንኳ ሳይጠይቁ ቶሎ ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ፡፡

******

እንደ ሁልጊዜው ሁሉ ዛሬም ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንደ አቅሙ የአገሩ ጉዳይ የማያስጨንቀው አለ ለማለት አያስደፍርም፡፡ ሁሉም ሰው ያለውን ችግር ያነሳል--

ይጥላል፡፡ በተለይ የኢሕአፓ አባል የነበሩትማ በተገናኙ ቁጥር ወሬያቸው ሁሉ ስለ ዚችው መከረኛ አገር ብቻ ነው የሚሆነው፡፡

ተሰፋዬ ከጎንደር አዲስ አበባ ተዛውሮ በግብርና መስሪያ ቤት ውስጥ ይሰራል፡፡ ታፈሰ የሥራ ባልደረባውና ጓደኛው ነው፡፡ ከስራ ውጭ ሲሆኑ አልፎ አልፎ አብረው ጊዜ የሚያሳልፉባት ቡና ቤት አለች፡፡ ዛሬም እዚያችው ቤት ተገናኝተው የልብ የልባቸውን እየተጫወቱ ነው፡፡

«እየሃቸው! እነዚያ እነማን ይመስሉሃል?» አለው ታሰፈ በአገጩ ጥግ ላይ ወደ ተቀመጡት ሰዎች እያመለከተው፡፡

«በአሁኑ ጊዜ ሙሉ ጅንስ በሰኒከር ጫማ ግጥም አድርጎ የሚለብሰ ማን ሊሆን እንደሚችል እንኳን እኔ አዲስ አበባ የምኖረው ከአገር ቤት የመጣው እንቴም አይስተው፡፡» አለ ተሰፋዬ ወደ ጅንስ ለባሾቹ እየተመለከተ፡፡ ጥግ ላይ ውስኪ ይዘው ተቀምጠዋል፡፡

«የሚገርመው ዓለም ታልፋለች የተባሉ ይመስል ሌሊቱን ሙሉ በየጭፈራ ቤቱ ዳንኪራ ሲረግጡ ማደራቸው ነው፡፡» አለ ታፈሰ እየተገረመ ፡፡

«ዳንኪራው ብቻ በበቃቸው፡፡ የከተማው ሴት ሁሉ አይቅራችሁ --ሄዋን ሁሉ አትለፉችሁ ሳይባሉ አይቀሩም፡፡ መጀመርያ ሲገቡ የነበረው መለሳለሳቸው የት ገባና እንዲህ እንዳበደ ውሻ እከለፈለፉቸው አባከህ? እንዲህ እንደ ቅጠል የሚረጩት ገንዘብስ ከደደቢት የባንክ ካዝና ይሆን ተዝቆ የመጣው?» አለ ተሰፋዬ፡፡

«ዴሞክራሲን--ፍትህን -ንጽነትን ለኢትዮጵያ አህዝብ ለማምጣት-- ደርግን ለመጣል ያባከኑትን የልጅነት ጊዜያቸውን ለማካካስ አይመሰልህም፡፡ አንተ ያን ጊዜ ከተማ ከተማውን እያካለልክ ዓለምህን ተቀጭ ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ እነሱ በተራቸው እየጠጡ ይደንሱ፡፡»

«ድንቄም ዲሞክራሲ! የኢትዮጵያ ሕዝብ የተረፈው ወሬ ብቻ ነው አባከህ! ጆሮው እስኪደነቁርና ሰልችት እስኪለው የፕሮፖጋንዳ ጋጋታ ብቻ!»

«ተው! ተው ተሰፋዬ! እንዲህ ድራፍትህን በነጻነት እየጠጣህ እስከ ፈለከው ሰዓት ድረስ በንጻነት የምታመሽው ማን በከፈለው መስዋዕትነት መሰለህ? የስዓት ገደብ ተነስቶልሃል፡፡ ሌሊቱን በሙሉ አዲስ እበባን ስታሰሳት ማደር መብትህ ነው፡፡ ከዚህ በላይ ዴሞክራሲ ምን ትፈልጋለህ?» አለ ታፈሰ የሰላቅ ሳቅ እየሳቀ፡፡

«ሲጠጡና ሲደንሱ ለማደር ለራሳቸው እንዲያመቻቸው ብለው እንደ ሆን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ያውቃል፡፡ ቡና ቤቱ ሁሉ በሰዓት አላፊ ሰም እንዳይዘጋባቸው፡፡ አሁን





አሁንማ እነሱ ከገቡበት ቡና ቤት ገብቶ መዝናናትም እያሰፈራ መጥቷል፡፡ በሆነ ባልሆነው ጠብ ይፈጥራሉ፡፡ ስትናገራቸው ቶሎ ብለው ሽጉጥ ላጥ-- ግንባርህ ላይ ድግን ያደርጋሉ፡፡ ሊገድሉህ ሁሉ ይችላሉ፡፡ ማን ይጠይቃቸዋል? በዘመነ ወያኔ ሥራዓት ብሎ ነገር የለ-- ሕግ ብሎ ነገር አይከበር» አለ ተሰፋዬ ሌላ ድራፍት እንድታመጣላቸው ለአስተናጋጇ የእጅ ምልክት እየሰጠ፡፡

«በጎጥህ፣ በዘርህና በቋንቋህ በንፃነት እንድትደራጅ ተፈቅዶልሃል ከዚህ በላይ ምን ትፈልጋለህ?»

«ይልቅስ በቀደምለት የሆንኩትን ልንገርህ፡፡ አዲስ መታወቂያ ለማውጣት ወደ ቀበሌ ጽሕፈት ቤት ሄድኩ፡፡ ቅጽ የምትሞላዋ ሹርቤ ሴት ብሔሬን ጠየቀችኝ፡፡ ምን ብዬ ልንገራት? አባቴ ባባቱ የጎንደር ሰው ሲሆን---- እናቱ የትግራይ ተወላጅ ናት፡፡ እናቴ የአርባምንጭ ሰው መሆኑዋን አውቃለሁ፡፡ እሷም ብትሆን ከአንድ ዘር የወጣች አይደለችም፡፡ ራሴን ከኢትዮጵያዊነት ውጭ እስቤው አላውቅም ነበር፡፡ ማን ነኝ ልበላት? መታወቂያውን ሳላወጣ ወደ ቤቴ ተመለስኩ፡፡ ማንነቴን ያስጠፉኝ ከፉ እፉኞች ናቸው፡፡ ኢትዮጵያን በዘርና በቋንቋ ከፋፍለው ከማፈራረስ የሚመለሱ አይመስለኝም» አለ ተሰፍዬ ስጋት ዐይኑ ላይ እየተነበበ፡፡

«በል---በል ወዳጄ! ከዚህ በላይ ከጠጣህና 'እህ' ብሎ ጆሮ የሚሰጥህ ካገኘህ ገና ብዙ ሳትዘባርቅ አትቀርም፡፡ ሰዓት እላፊው የተነሳ ቢሆንም የሚሆነው አይታወቅም፡፡ ከዚህ በላይ ማምሸቱም ለኛም አይበጀንም፡፡ የዚች የመከራ ጉዞዋ ገና ያላለቀላትን አገር ጉዳይ እንዲህ ባጭር ጊዜ ውስጥ አውርተን የምንጨርሰው አይሆንም፡፡ ተነስ እንሂድ» አለ ታፈሰ፡፡ የያዙትን ድራፍት ጨርሰው ሒሳብ ከፍለው ሊወጡ አካባቢውን ጨለማ ውጦታል፡፡ የመንገድ ላይ መብራት ባይኖር ኖሮ እስከ ታክሲ መያዣው ያለው መንገድ ባልታያቸውም ነበር፡፡

«ከምኔው እንዲህ ጭልምልም አለ አባከህ!» አለ ታፈሰ፡፡

«ሲነጋ ሲል ይጨልማል፡፡ ምናልባት ለዚያ ይሆን?» አለ ተሰፋዬ፡፡ እየተደነቃቀፉ ታክሲ ተራ ሲደርሱ ትራንስፖርት ችግር ሆኖ ሰው ሁሉ ከወዲያ ወዲህ ይራወጣል፡፡ እንዱ ታክሲ ውስጥ እንደ ምንም ተጋፍተው ገብተው ወደ የሰፈራቸው አመሩ፡፡ የደርግ መንግሥት ወድቆ አዲስ መንግሥት ቢተካም ሕዝቡ የተመኘውን ዓይነት አመራር ያገኘ አይመሰልም፡፡ የአገሪቱ አብዛኛው ሕዝብ የሚያሰማው ቅሬታና ብሶት ብቻ ነው፡፡

******

ሂያጂውን በሚሸኝና መጭውን በሚቀበል ቦሌ ዓለም አቀፍ አይሮፕላን ማረፊያ በሰው ተሞልቷል:: ከአሜሪካ የሚመጣውን ድልነሳን ለመቀበል ትሩፋትና ቤተሰቧ ከተቀባይ ወገን ናቸው::

«ሻይ ቡና እያልን ብንቆይ አይሻልም ትሩፋት? አንቺም ወገብሽን አሳርፊ» አለ ይነበብ ትካዜ የሚነበብበትን ፊቷን መልከት አድርጎ::

«እ--እ--» አለች ትሩፋት:: ሐሳብ ውስጥ ነበረች:: ከልቧ አላዳመጠችውም::

ትሩፋት ቦሌ ዓለማቀፍ አይሮፕላን ማረፊያ ስትመጣ ሁሌም ደስ አይላትም:: ምንም ከማይጠቅማትና ልትመልሰው ከማትችለው ከፉ ትዝታ ውስጥ እየወሰደ ይዶላታል:: «ጩሂ-- ጩሂ--አልቅሽ-- አልቅሽ« የሚል ስሜት ይተናነቃታል:: ዛሬም በሀዘንና በትካዜ ተውጣ ነበር:: እንዲህ ስትሆን ደግሞ ለማጽናናትም ሆነ ለማረሳሳት አትሞከርም:: የምትመርጠው ከገባችበት የሐሳብ ባሕር በራሷ ጊዜ እንድትወጣ ብቻዋን እንዲተዋት ነው:: ዝ--ም! እንዲሏት::

ግማሹ ሰው አበባ ይዞ በደስታ ይፍለቀለቃል:: እንግዳውን ለመቀበል ከአጥሩ ቀድሞ ለመጠጋት ይጋፋል:: እንግዳውን ለማየት እየተንጠራራ አንገቱን ያሰጋል:: በሌላ ወገን ደግሞ መለያየት ሞት ሆኖበት እንገት ላንገት ተቃቅፎ የሚላቀሰው የዚያኑ ያህል ነው:: ትሩፋት ይህ ሁሉ የቦሌ ትዕይንት አልሳባትም:: የጉዞ ጣጣ የማያውከውን የሀሳብ ፈረሷን ጭና ጭልጥ ብላ ሄዳለች---ነጉዳለች፤ ወረታ እያቷ ጋ---

ጊዜው ሐምሌ በመሆኑ ይዘንባል:: የአባቷ እናት እማዎይ ፊንታዬ በጠና ታመው ልትጠይቃቸው ወረታ የሄደችው ከእናትና ከአባቷ የመጨረሻ ልጅ የሆነችውን እያልን ለትምህርት ወደ አሜሪካ ከሸኘቻት በኋላ ነበር::

«እማማ ምን ታይቷት ይሆን? እጄን ጭብጥ አድርጋ ይዛ እያልን አሜሪካ የሚባል አገር እንዳልሰዳት እጥብቃ ያስጠነቀቀችኝ ወደ ፊት የሚያጋጥማት ሞት ታይቷት ይሆን? ሰውነቷ ነግሯት ይሆን? ሕልም አልማ ይሆን? ምነው ከመሄዷ በፊት አግኝቻት ነግራኝ በነበር» የአያቷን ማስጠንቀቂያ አሁንም አሁንም ደግማ--- ደጋግማ እያሰበች ተብሰለሰለች:: የአንድ ወንድሟ የድልነሳ ነገር ሆኖባት ነው እንጂ ቦሌ አይሮፕላን ማረፊያ ስትመጣ ትከፋለች:: ሆዷ ውስጥ አዳፍና የያዘችውን የሀዘን ረመጥ እየቆሰቆሰ ያርመጠምጣታል::

«ምነው ባልሰደድኳት ኖሮ! --ምነው ሳትማር በቀረች!» አለች አሁንም ለራሷ:: ፀፀት እንጀት ጉበቷን በላው:: የመሸኛ ድግስ ደግሳ በጭፈራ የላከቻት ታናሽ እህቷ እያል-- ተምራ ከራሷ አልፋ ለአገር ለወገን ትጠቅማለች የሚል ሕልም ነበራት:: በሰው አገር-- ያውም በሰው እጅ ተገድላ አስከሬኗን ቦሌ አለማቀፍ አይሮፕላን ማረፊያ እቀበላለሁ ብላ





ማሰብ ቀርቶ አላለመችውም:: የእያልን ሞት ገና እምና ያልተቀበለችው ነገር ሆኖባት እንደ ቀን ቅዠት ያባንናታል:: የእግር እሳት ሆኖ ይኸው ያንገበግባታል፤ ከንቱ ላታገኛት::

ከትሩፋት እናትና እባት የመጨረሻ ልጅ የሆነችው እያል ከሌሎች እህቶቿ የተሻለ የትምህርት ችሎታ ነበራት:: እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል የዘለቀችው የክፍሏ የማእረግ ተማሪ እየሆነች ነው:: የአጋጣሚ ነገር ሆኖ የአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ብሔራዊ ፈተና በጣም ጥሩ የሚባል ውጤት ሳይመጣላት ይቀራል:: ትሩፋትና ይነበብ ድልነሳ አሜሪካ የትምህርት እድል የምታገኝበትን መንገድ እንዲያመቻችላት ሳያሳልሱ ጣሩ ወተወቱ:: ከአንድ ዓመት ውጣ ውረድ በኋላ ተሳካና አሜሪካ ገባች:: እስካሁን ጉዳዩ ግልጽ ሆኖ ባልታወቀ ምክንያት በሰው እጅ ሕይወቷ ያልፋል:: እስከሬኗ ወደ እናት እገሯ ይላካል:: በቃ!! የእያል ነገር በዚሁ ያከትማል!! ለቤተሰቦቿ ግን ሁልጊዜ አዲስ ትዝታ ናት:: የማትረሳ! ልባቸው ውስጥ የበቀለች ያማታብብ አበባ::

ትሩፋት ፀፀት ከሞላበት ከፉ ትዝታዋ ስትመለስ ቦሌ ዓለም እቀፍ አይሮፕላን ማረፊያ ውስጥ ናት:: በዓለም ዙሪያ እንደ ጨው ከተበተነው ኢትዮጵያዊ ስደተኛ አንዱ የሆነው ድልነሳ ከአስራ አምስት ዓመት መለያየት በኋላ ዛሬ የእገሩን መሬት ይረግጣል:: ትሩፋት የደርግ መንግሥት ውድቀት ያስገኘላት ነገር ቢኖር የታናሽ ወንድሟን ወደ አገር ቤት መመለስን ብቻ ነበር:: እንኳንም ሳይገናኙ እስከ ወዲያኛው አልቀሩ:: ያልተቋጨው ራዕይ ሰለባ የሆነው ወርቁንና ብቸኛ ልጅ አሳዳጊዋ እልፍነሽ ታወሷት:: ከሁልጊዜው ይበልጥ ለእልፍነሽ ዛሬ በጣም አዘነችላት....

ሌሊቱ ገፍቶ ሊገባደድ ሲል ከአሜሪካ የተነሳው የኢትዮጵያ አየር መንገድ አይሮፕላን መግባቱ በተለያዩ ቋንቋዎች ተነገረ:: እንግዳ ተቀባይ ወዳጅ ዘመድ መንቀሳቀስ ጀመረ:: ትርምስ ሆነ:: ትሩፋት ድልነሳን ገና ብቅ ሲል ነበር የለየችው:: ቀጠን ብሎ መካከለኛ ቁመት ይኖረዋል ብላ የጠበቀችው ድልነሳ እጠር ብሎ ደልደል ያለ ሰው ሆኖ አገኘችው:: እንደ ልጅነቱ ዛሬም ኮፍያ ደፍቷል:: ድሮም ከርከም ያሉት ከናፍሮቹ ይብልጥ ከርከም ብለው አፉን ያጠበቡት መሰላት:: እየተላቀሱ ተቃቀፉ:: በሁለቱም ልብ ውስጥ እያል ነብስ ዘርታ ተንቀሳቀሰች:: አዲስ ለቅሶ--አዲስ ሙሾ---

«ከእንግዲህ እያልን በለቅሶ እናገኛትም:: በቃ! ይበቃችኋል:: ለድሌም አስቢለት እንጂ:: ሰንት ሰዓት ሙሉ አይሮፕላን ውስጥ ተቀምጦ ተጉዞ የመጣ ሰው ነው፤ ይደከመዋል:: ወደ ቤት ሄደን ትንሽ እረፍ ቢል ይሻላል» አለ ይነበብ:: ጉዞ ወደ ቤት ሆነ:: ቤት ሲደረሱ ድሌም መተኛት አልቻለም:: ሰዓቱ ከእኩለ ሌሊት ቢያልፍም «እንኳን ደህና መጣህ» ለማለት በሚጠብቀው ጎረቤትና ወዳጅ ዘመድ ቤቱ ተሞልቷል:: የተዘጋጀው ድግስ ተበላ ተጠጣ:: ሰው ወደ የቤቱ የሄደው ሌሊቱ ገፍቶ ሊነጋጋ ሲል ነበር:: እነ ትሩፋትም መኝታን ገና አላሰቡትም:: ድልነሳን ዐይን ዐይኑን እያዩ ሁሉም የናፍቆታቸውን በያፋቸው ያወራሉ:: የአስራ አምስት ዓመት ናፍቆት እንዴት ብሎ በአንዲት ምሽት ያልቃል?

የአያል ሞት ድንገት ነበር የተነሳው:: በዚህ ሰዓት የእህታቸውን ሞት አንስተው እንግዳ ወንድማቸውን ማሳቀቅ አልፈለጉም ነበር:: ግን ሆን ብሎ ሳይሆን ከወሬ መሀል ራሱ ድልነሳ ነበር ያነሳት::

«አያል ሞት ቀደማት እንጂ ለቤተሰብ የነበራት ፍቅር ከሁላችንም በላቀ ሁኔታ ትሩፋትን ትተካት ነበር:: በተለይ ለእናቷና ለአገር ቤት ወንድሞቿ የነበራት ልብ ከቅጠል የሳሳ ነበር» አለ ድልነሳ ዐይኑን ቡዝዝ አድርጎ:: ራሔል መነፋረቅ ጀመረች፤ ይኸው ናት:: ሁሌም የአያል ስም በተነሳ ቁጥር ማልቀስ ልማድ አድርጋዋለች::

«ተሰሚያስሽ ራሔል በአያል ሞት ከእኔ የበሰጠ አንቺ አልተጎዳሽም:: ጧት ለሥራ ተሰናብታኝ ወጥታ ግማሽ ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከምትሰራበት ቦታ 'ሞታልሃለችና ና አስከሬን ውሰድ' ተብዬ ሲደወልልኝ የደረሰብኝ ሀዘንና የልብ ስብራት በጊዜውና በቦታው ሳልነበረ ሰው ቢነግሩት ከቶም ሊገባው አይችልም:: ድንገተኛ ሞቷ እውነት አልመስለኝ ብሎ ትነሳ እየመሰለኝ አስከሬኗ ላይ በግንባሬ ተድፍቼ ትንፋሿን አዳምጫለሁ:: ዐይኔን ሳልነቅል አሳይዋ ላይ አፍጥጫለሁ:: ግን ማንም ከሞት እንዳልተመለሰ ሁሉ እሷም አልተመለሰችም» አለ ድልነሳ መከፋቱ ፊቱ ላይ እየተነበበ:: ቤቱ በአንዳፍታ የሀዘን ድባብ ዋጠው::

«ይልቅ ሁላችንም የሚጠበቅብንን ነው ማድረግ ያለብን:: ይዘገያኛል እንጂ ገዳይዋ ይገኛል:: እኔም እንደ እሷ እስከ ሞት ድረስ መከታተሌን አላቆምም:: ጉዳዩን የፍሎሪዳ ፖሊስ ዲፓርትመንት በጥብቅ እንዲከታተለው አድርጊያለሁ:: ከዚህ በመለስ እህታችንን ከልብ የምንወዳት ከሆነ በሕይወት እያለች ትመኝ የነበረውን ተግባራዊ ማድረግ ነው ከእኛ የሚጠበቀው እያል የቤተሰቡን፣ ፍቅር እድገትና ብልጽግና አጥብቃ ትፈልግ ነበር:: በቂ ገንዘብ ሲኖራት በቤተሰቡ ስም አንድ ሆስፒታል በገጠራቱ ኢትዮጵያ የመገንባት ትልቅ ምኞት ነበራት:: ለዚህ ነው የሕክምና ትምህርት ለማጥናት የመጀመርያውን ፈተና የወሰደችው:: ለጊዜው ትመኝ የነበረውን ተግባራዊ ለማድረግ አቅም ባይኖረንም-- በሕይወት በነበረችበት ጊዜ አብራን ያሳለፈችውን መልካም ጊዜ እያስታወስን በመንፈስ አብራን እንደምትኖር ማሰብ ይጠበቅብናል:: ሳቋን--ጨዋታዋን--ቀልዷን እያነሳን በመንፈስ ሁሌም አብራን እየኖረች አድርገን ልንቆጥረው ይገባል:: ከሁሉም በላይ ደግሞ የቤተሰቡን የእርስ በርስ መዋደድና መፋቀር አጥብቃ ትፈልግ ነበር:: አያል በዓለም ብትኖር ልታደርግ የምትመኘውን ቀሪዎቹ እኛ በሕይወት ያለው ሞት ሳይቀድመን ተግባራዊ እናድርገው:: እርስ በእርሳችን እንፋቀር---- እንተሳሰብ---- እንከባበር--- ማልቀስ እስከዛሬ ማንንም ከመቃብር አልመለሰም:: በቁም ያሉትን ማፍቀርና በደስታ ቀሪ ሕይወትን ማሳለፍ እያለ--- ሙት ናፋቂ መሆን ሞኝነትም አስሙሳይኝትም ነው:: የሞተ አይገኝማ!» አለ ድልነሳ መረር አድርጎ::





«በቃ! አሁን አሱን ተውት:: አያል ላትመለስ ሄዳለች:: ሕይወት ደግሞ ይቀጥላል:: አንዱ ሲሞት ሌላው እየተወለደ:: ይልቅስ አዳምጡ:: ከአስራ አምስት ዓመት የስደት ኑሮ በኋላ በዛሬው እለት ድሌ ለአገሩ መሬት በመብቃቱና ከቤተሰቡ ጋር በሰላም በመገናኘቱ ሁላችንም የእንኳን ደህና መጣህ ጽዋችንን አንደ ገና አናንሳ!» አለች ትሩፋት የራሷን ወይን ብርጭቆ ወደ ላይ ከፍ አድርጋ:: ሁሉም ብርጭቆቻቸውን አጋጩ፡

******

ድልነሳ አገሩን ከመናፈቁ የተነሳ አዲስ አበባ አልበቃው ብላለች:: ትናንት እንደወጣ አድሮ ትሩፋትን አስጨንቋት ነበር::

«ድሌ ምን ማለትህ ነው? ከውጭ የመጣ ሰው እኮ ዐይነ ውሃው ያስታውቃል:: የአዲስ አበባ ዱርዬ ማጅራትህን ብሎ ገሎህ ይሆናል ብዬ ስጨነቅ እንቅልፍ ባይኔ ሳይዞር ነው ያደርኩት---- ግን በጤናህ ነው?

«ትሩፋት ደግሞ ሁሌ ልጅ ታደርጊኛለሽ:: አሁን እኮ ለራሴ የማስብ ትልቅ ሰው ሆኛለሁ:: ዛሬም እንደ ልጅነቴ መጨነቅ አይገባሽም» ይህን እየተነጋገሩ ይነበብ ከውጭ ገባ::

«እንደ ምን ዋላችሁ» ብሎ ትሩፋትን ግንባሯ ላይ ስሞ ድሌን የእጅ ሰላምታ ሰጥቶት ተቀመጠ::

«ድሌ ትናንት የት ጠፍተህ አደርክ?» አለ ይነበብ ወደ ድልነሳ እየተመለከተ::

«ምን አባክህ አንዲት የአዲስ አበባ ቆንጆ ልጅ አግታኝ ነበር:: አሁንም በስንት መከራ እግረሙቅ ሰብሬ አምልጬ መምጣቴ ነው» አለ እየሳቀ::

«ብትጠለፍ ምን ይገርማል? የሸኒን ውሃ ጠጥተህ— ዶቅማዋን በልተህ ያደክ የውሃ ፈለፈል የመሰልክ ልጅ ነህ !» አለች ትሩፋት እሷም እየሳቀች::

«ወንድሟ ስሆን ጊዜ የሌለኝን ውበት ታላብሰኛለች:: ይልቅ አንተ ሰላም ዋልክ ይነበብ? ሥራ እንዴት ነው?» አለ ድልነሳ::

«ምን ሰላም አለ ብለህ ነው? እነዚህ ሰዎች የሚያሰሩን ዓይነት አይደሉም:: አውቀው አይሰሩ-- እውቀቱ የላቸው:: ችሎታውና ሙያው ያለው ሰው እንዳይሰራ ደግሞ እንቅፋት እየሆኑ አስቸገሩ:: አይሠሩ— አያሠሩ:: መላ ቅጡ የጠፋባቸው ሰዎች ናቸው:: በዚህ አካሄድ የዚች አገር እጣ ፈንታ መልካም ይሆናል ብሎ መገመት ይከብዳል» አለ ይነበብ::

«ሕወሓት ብሎ የአገር መሪ! ውጭ ኗሪ በሆነው ኢትዮጵያዊም ብዙ ድጋፍ አልነበራቸውም:: አነሳሳቸው ጎጠኝነትን መሰረት ያደረገ በመሆኑ አገሪቱን ብትንትኗን ያወጧታል ብለው የሚሰጉ ብዙዎች ነበሩ:: ይኸው የተፈራው አልቀረም ገና ከጅምሩ ኤርትራን አስገነጠሉ:: ይባስ ብለው ያለባሕር በር አስቀሩን:: አንድ መንግስት ነኝ የሚል ተቋም ቢችል የአገሩን የግዛት ደንበር ያሰፋል እንጂ መሬት እየቆረሰ ሌላ አሳልፎ የሰጠ ከነዚህ ገዥዎቻችን በስተቀር በዓለም ላይ ቢፈለግ አይገኝም:: መጀመሪያውንም ኢትዮጲያዊ አጀንዳ ሳይዙ እንዴት ኢትዮጵያን ያስተዳድራሉ ተብሎ ይታሰባል? በአገር ሉአላዊነት ደርግ ይሻላል የሚለውን ሐሳብ ብዙዎች ይጋሩታል» አለ ድልነሳ::

«ፍርድ ለመስጠት የቸኮልን አይመስላችሁም:: ስልጣን ላይ ከወጡ ብዙ አልቆዩም:: በዚያ ላይ አገርና ሕዝብ የማስተዳደር ልምድ ገና አላዳበሩም:: በደፈጣ ሲዋጉ የኖሩ የጫካ ሰዎች መሆናቸውን አትርሱ» አለች ትሩፋት::

«ከነደፉት ፕሮግራም ውጭ የት ይሄዳሉ? የህወሓት አነሳስ የትግራይን ሕዝብ ገንጥሎ ነፃ ማውጣት ነው:: ለመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነት ብለው አልታገሉም:: ቀን ሰጥቷቸው አራት ኪሎ ቤተመንግሥት ስለገቡ ብቻ ኢትዮጵያዊ ራዕይ ይኖራቸዋል ማለት ሞኝነት ነው:: መላሪያን ሁሉ ከሕዝብ ላይ ገፈው ባለ ትጥቅ እነሱ ብቻ መሆናቸውን ስላረጋገጡ ሕዝብ ንቀዋል:: ያ ባይሆን ኖሮ ያለ ሕዝበ ውሳኔ ኤርትራን ባላስገነጠሉም ነበር:: እጅግ አስደናቂው ነገር ደግሞ ከሚያስተዳድሯት አገር ይልቅ ለኤርትራ ሉዓላዊነት የቆሙ መሆናቸው ነው:: ኢትዮጵያ የባህር በር አያስፈልጋትም ብለው የአሰብን ወደብ ለኤርትራ አሳልፈው ሲሰጡ መጭው ትውልድ አላሳሰባቸውም:: ለታሪክ ፍርድ አልተጨነቁም:: ዓለም ጉድ እስኪል ተሯሩጠው ለኤርትራ ሉዓላዊነት እውቅና ሲሰጡ ማንም አገር አልቀደማቸውም:: በአጠቃላይ አካሄዳቸውን ስመለከተው እነዚህ ሰዎች ለኢትዮጵያና ሕዝቧ የሚበጅ ጤነኛ አጀንዳ ይኖራቸዋል ብዬ አላስብም» አለ ይነበብ ስጋት ፊቱ ላይ እየተነበበ::

«በእድልም ይሁን በአጋጣሚ ስልጣን እጃቸው ውስጥ ገብታለች:: የኢትዮጵያ ሕዝብም መዳፋቸው ስር ወድቋል:: አጋጣሚውን ተጠቅመው ፕሮግራማቸውን ይለውጡት ይሆናል:: ኢትዮጵያዊ አጀንዳ ያደርጉታል ብዬ አስባለሁ:: ይህን ድንገት የተገኘ እድል ከፈለጉ ታሪክ ሰርተው ከመቃብር በላይ የሚውል ስም ይተከላሉ የሚል ተስፋ አለኝ» አለች ትሩፋት:: ተስፋዋ ሙሉ ለሙሉ ተሟጦ ገና አልተጨረሰም::

«ወያኔዎች ከመጭው ትውልድ ጋር የሚቀላቀሉ ልጆች አሏቸው:: አንድ ቀን ከያዛቸው ክፉ ቅዠት ሲባንኑ ትክክለኛውን ነገር ይረዱታል:: ለትውልድ፣ ለአገርና ለወገን ቅድሚያ ሰጥተው ታሪክ የሚዘከረው ሥራ ይሰራሉ ብዬ አስባለሁ ስለዚህ ጊዜ ይሰጣቸውና እንያቸው» አለች ደገመችና::





«እስከ መቼ ነው የሚጠበቁት? ስልጣን ላይ ከወጡ ይኸው ድፍን ሦስት ዓመት አስቆጠሩ:: ለፖለቲካ እድሜ ሶስት ዓመት ብዙ ነው:: በጣ--ም ብዙ:: ነገር ግን የለምም ሆነ የፕሮግራም ለውጥ አላደረጉም:: ከእንግዲህ ዲሞክራሲን--ፍትህና እኩልነትን ከእነዚህ ሰዎች መጠበቅ የዋህነት ነው:: እንደውም በቴዎድሮስ ተጀምሮ በምኒልክ ተጠናከሮ የነበረው የአገር አንድነት እንዳይፈራርስ ያሰጋል:: በየቋንቋው እንደ ጫጩት የሚቀፈቅፏቸው ድርጅቶች ለጠባብነታቸውና ለጎጠኝነታቸው ዋቢ ምስክሮች ናቸው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋ በመሆኑ እንጂ እንደ እነሱ ቅስቀሳና ውትወታ ቢሆን ኖሮ እስከ አሁን እርስ በእርስ እሚጋረሰውን ነበር:: የውጭ ጠላት እንኳ ሕዝብ እርስ በርሱ እንዲባላ የሕወሀትን ያህል ተንኮል ሲጠነስስ ውሎ ሲጠነስስ አያድርም:: ምክንያታቸው ምን እንደ ሆነ ባላውቅም ሥራቸውና አካሄዳቸውን ላስተውለው ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ጥላቻና በቀል ያላቸው ነው የሚመስለኝ» አለ ይነበብ መጭው ጊዜ እያስጨነቀው::

«እናንተ ሰዎች ሳያችሁ የፖለቲካ ትኩሳታችሁ ዛሬም ገና አልበረደላችሁም:: እርፋችሁ ልጆቻችሁን ብታሳድጉ ይሻላችኋል:: በደርግ መንግስት ስትታሰሩ ስትፈቱ የኖራችሁት ከበቂ በላይ ነው:: አለመሞታችሁ የአግዜር ምህረትና ጥበቃ ታክሎበት ላይሆን አይቀርም:: ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለውጥ እንዲመጣ የዜግነታችሁን ተወጥታችኋል:: ኢሕአፓ የሚሏት ድርጅት የነካካችው ሰው ያለፖለቲካ ሕይወት ያለ አይመስለውም:: አባካችሁ ከእንግዲህ እድሜያችሁም ቀላል አይደለም:: ልጆቻችሁን እሳድጉ፣ ቤተክርስቲያናችሁን እየሳማችሁ፣ የተጣላ እያስታረቃችሁ አርፋችሁ ተቀመጡ» አለ ድልነሳ ከልቡ::

«እኛ ነን የምናውቅላችሁ:: እኛ ካልናችሁና ከምንነግራችሁ ውጭ ማድረግ አትችሉም እያሉ በእነሱ መልካም ፈቃድ ብቻ የምንኖር ከሆነ ምኑን እንደ ሰው አገር ላይ ኖርነው? ደርግን የታገልነው ለነፃነት ነበር:: እነዚህም ነፃነታችንን አልሰጡንም:: ይባስ ብለው የሕዝብ ውክልና ሳይኖራቸው ሕዝበ ውሳኔ የሚሹ ትላልቅ የአገር ጉዳዮችን እየወሰኑ አገሪቱንና ሕዝቡን ችግር ውስጥ እየከተቱት ይገኛሉ:: ለልጆቻችንስ እንዴት ያለች አገር ነው የምናወርሰው? አንተማ የምዕራቡን ዓለም ነፃነት አይተህ የለም እንዴ ድሴ!?» አለ ይነበብ::

«አዎ አይቻለሁ! እነሱ የሰው አይደለም የእንስሳት መብት ይከበር ከሚባልበት የዲሞክራሲ የእድገት መሰላል ላይ ደርሰዋል:: እኛ እንደ እነሱ ለመሆን ገ--ና ብዙ ይቀረናል ይነበብ» አለ ድልነሳ::

«እዚያ የነፃነት የእድገት መሰላል ላይ ለመድረስ እኛ ዝም ብለን ትተነው ቁጭ ካልን ማን መጥቶ እንዲያወጣን ነው የምንጠብቀው? እኛው ካልታገልን ነፃነትን እንደ ሸቀጥ ዕቃ ከውጭ አይገዛ ነገር! ወይም እንደምንገዳው እህል ስለ እማምላክ ብለን በምጽዋት

እናገኘው ነገር! የነፃነት ዋጋው ውድ ነው! በጣም ውድ! የሚያስከፍለው ወርቅ ሳይሆን ደም ነው፡፡ ይህ ለምን የሆነ ይመስላችኋል? ሰው ያለነፃነት ሕይወት አልባ ነው፡፡ ለነፃነት ሲል በአንዲት ነብሱ ይታገላል፡፡ አንገትን ደፍቶ ዝም ብሎ ስለተኖረ ብቻ ተኖረ ማለት አይደለም፡፡» አለ ይነበብ አዲስ የትግል ጥንስስ ልቡ ውስጥ እየተብላላ፡፡

«ያን ውድ ዋጋ ለመከፈል ዝግጁ የነበረው ወጣት ሁነኛ ድርጅት አጥቶ ተመቷል፡፡ ተስፋው ሞቶ ተቀብሯል፡፡ በዚያም ላይ ደርግ ቀጥቅጦ ቀጥቅጦ ፈሪ አድርጎናል፡፡ በዚያ ሰሞን ፍርሀትን የሚመለከቱ እንደ ቀልድ የተወሩ ሁለት ወሬዎች ላውራላችሁ» አለች ትሩፋት፡፡ ሁሉም ለማዳመጥ ዝግጁ ሆኑ፡፡

«ሁለት የአዲስ አበባ ወጣቶች ናቸው አሉ በኤርትራ መገንጠል ጉዳይ ይከራከራሉ፡፡ አንደኛው ወጣት 'ኤርትራን ከእናት አገሯ ሲገነጥሏት እንዴት ዝም ብለን እናያለን' እያለ በንዴት ይንጨረጨራል፡፡ የጓደኛውን መበሳጨት ያስተዋለው ሌላው ጓደኛ ምን ብሎ መለሰለት መሰላችሁ? 'እንኳን ኤርትራን የቤቴን የጣሪያ ቆርቆሮ መጥተው ቢገነጥሉት ላስቲክ አልብሼ እኖራለሁ አንተ ዝም ብለህ ነው ያዙኝ ልቀቁኝ የምትለው፡፡ ከእንግዲህ ጦር ማን ይማዘዛል?' ብሎ ከጋለ የጓደኛው ስሜት ላይ ቀዝቀዛ ውሀ ቸልሶበት እርፍ! ታድያ እንዲህ ወኔው የሞተን ወጣት እንዴት ነው ዳግም ለትግል ማነሳሳት የሚቻለው?» አለች ወደ ይነበብ እየተመለከተች፡፡

«አይምሰልሽ ትሩፌ ግፍና በደል የበዛበት ሕዝብ-- ነጻነቱ የታፈነበት ሕዝብ አንድ ቀን ለአመጽ መገንፈሉ አይቀርም፡፡»

«ያ አንድ ቀን መቼ ነው?- ነው ጥያቄው» አለ ድልነሳ፡፡

«የዛሬ መቶ ዓመት!» አሾፈች ትሩፋት፡፡

«እናንተ ትቀልዳላችሁ፡፡ እኔ አልቀልድም፡፡ ያን አንድ ቀን ለማፍጠንና ለማቅረብ መድሀኒቱ ተደራጅቶ መታገል ነው፡፡ ያለዚያ ያ አንድ ቀን መቼም በራችንን አንኳኩቶ አይመጣም ወይም ከሰማይ እንደ መና አይወርድልንም- እንደ ምንጭ ከከርሰ ምድር አይፈልቅልንም» አለ ይነበብ፡፡

«ቆዩ አስጨርሉኝ እስቲ! የሰማሁትን ታሪክ መቼ ጨርሼ ነገርኳችሁ» አለች ትሩፋት፡፡

«አልጨረሽም እንዴ! ትረካዉ ያበቃ መስሎን እኮ ነው ሌላ ክርክር ውስጥ የገባነው፡፡ ይቅርታ ትሩፌ» አለ ድልነሳ፡፡





«ይቅርታ የኔ ቆንጆ! በይ ቀጥይ» ብሎ ጉንጯን ዳበስ አደረጋት ይነበብ፡፡ ቀጠለች ትሩፋት፡፡

«መቼም ለዚች መከረኛ አገር እንደ አቅሙ፣ እንደ ችሎታውና እንደ እውቀቱ የማይጨነቅና የማይጠበብ ሰው የለም፡፡ ሁለት ያገር ቤት ጓደኛሞች ደግሞ እንዲሁ የኤርትራን ጉዳይ አንስተው ሲጨዋወቱ፡፡ አንደኛው የአገር ቤት ልጅ በቁጭት 'አገራችን አንገቷን ቆረጧት፡፡ ጎራዳ ጀበና አስመሰሏት' እያለ ይበሳጫል አሉ፡፡ ሌላኛው ጓደኛው በማናናቅ 'ምን እስር ጊዜ ኤርትራ ተገነጠለች-- አገራችን ጎራዳ ጀበና መሰለች' እያልክ ትንጨረጨራለህ፡፡ ዛዲያ ምን ይሁን!? አሁን የዘመቻ ምልመላ ቢመጣብህ ጢሻ ውስጥ ገብተህ ለመደበቁ ነው' ብሎ ጓደኛውን አፉን አስያዘው አሉ፡፡ የአገር ጉዳይ ነውና መቆርቆሩ ቢኖርም በአሁኑ ጊዜ ደፍሮ ለትግል የሚነሳ ትውልድ ማግኘት ይከብዳል ባይ ነኝ፡፡ ስለዚህ ይነበብ ውዴ! ለጊዜው ድሌ እንደ መከረን አርፈን ልጆቻችንን ብናሳድግ ይሻላል እባክህ!» አለች ትሩፋት፡፡

«አሁን እልፎ አልፎ የምናየው በዘር የመከፋፈል--የመጠቃቀምና የመጎዳዳት ሁኔታ አድጎ የእያንዳንዳችን ቤት ማንኳኳት ሲጀምር ግን ማጣፊያው ያጥረናል» አለ ይነበብ ፡፡

«አሁንስ ይሄ ማለቂያ የሌለው የፖለቲካ ወሬ አጅ እጅ አለኝ፡፡ ውጭ አገር እንዲሁ ከአንድ አበሻ ጋር የተገናኘሁ እንደ ሆነ በተቀዋሚ ወይ በደጋፊ ጎራ ራሳችን እንመድብና ስንነታረክ ውለን ስልችት ብሎኝ አንድም መቋጫ ነገር ሳይገኝ እቤቴ እገባ ነበር፡፡ እዚህ ስመጣም የባሰ እንጂ የተሻለ ነገር አላጋጠመኝም፡፡ ምንም ወሬ ይጀመር --ምንም ዓይነት ጨዋታ ከማንም ኢትዮጵያዊ ጋር ይከፈት ዞሮ ዞሮ ማሳረጊያው የዚችው መከረኛ አገር ፖለቲካ ሆኖ ያርፈዋል፡፡ አንድም ጊዜ ግን ዘላቂና የተጨበጠ የመፍትሔ ሐሳብ አምጥተን እናውቅም፡፡ በዚህ በዚህ መንገድ እንታገል ብሎ ግልጽ ያለ አስተማማኝ የሆነ የመታገያ ስልት ነድፎ ያሳየን ድርጅትም ሆነ ግለ-ሰብ የለም፡፡ ከሕዝቡ ቁጥር በላይ ድርጅቶች ተፈልፍለዋል፡፡ ምን ጠቀሙን? ሁልጊዜ ማውራት-- መጯጯህ ብቻ! ችግራችን አንድ ሆኖ ሳለ ድርጅቶች ሺህ ናቸው፡፡ ለአንድ ችግር አንድ ላይ ቁሞ መታገል እስከ አልተቻለ ድረስ ትርፉ መጯጯህ ብቻ ነው፡፡ እስኪ ለዛሬ የፖለቲካው ሙግት ይብቃንና ወጣ እንበል፡፡ የናፈቅኋትን የአዲስ አበባን ነፋስ እንቀበል አባካችሁ!» አለ ድልነሳ፡፡

«እውነትህን እኮ ነው፡፡ ምንም ቢሆን የፈረንጅን ውሃ የጠጣ ይግደለኝ፡፡ በዓለም ላይ ሲኖሩ በጭንቀትም መሀል ሆኖ አንዳንዴ ነብስን ዘና ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ሁልግዜ ማልቀስ ሆነ እኮ ኑሯችን፡፡ ዛሬስ ለቅሶውን ስንለምደው ጊዜ ነው መሰል ዘፈን ሳይመስለን አልቀረም» አለች ትሩፋት፡፡

«ምንጊዜም የአስተዳደር ጭቆና ያለባቸው አገሮች ሕዝባቸው የሚተርፈው ምሬት ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ሁሉም ነገር ለቅሶ ነው፡፡ አድርባይ ካልሆኑ በስተቀር የኪነጥበብ ሥራዎች

ሁሉ በለቅሶና በሀዘን የተሞሉ ነው የሚሆኑት:: ልበለዱ፣ ግጥሙ፣ ትያትሩ፣ ሙዚቃው፣ ተውኔቱ ሁሉ ከችግርና ከስቃይ ያለፈ አይጻፍም:: አይተወንም:: የማኅበረሰቡ እውነተኛ ገፅታ ያ ስለሆነ:: እኛም የዚህ ያልታደለ ሕዝብ አካል ነንና የሌለ ነገር ከየት አምጥተን እንጫወታለን?» አለ ይነበብ::

«በእናታችሁ! ለዚህ ሁሉ ከርከራችን ማሳረጊያ የሚሆን ተረት ወይ ቀልድ በሉት ፈገግ ቢያሰኛችሁ አንድ ለመንገድ ልበላችሁና እንውጣ» አለች ትሩፋት ቀድማ እሷው እየሳቀች:: ሁለቱም ዐይኖቻቸውን ወደ ትሩፋት ላኩ፡

«ቀልዱን ሳንሰማው አንቺው ስቀሽ ጨረሰው እኮ» አለ ይነበብ አብሯት እየሳቀ::

«የማወራላችሁ ስለአንድ መምህር ነው:: መምህር አይደለሁ ወኔ ሁሉ ያው ከመምህር አይወጣም::»

«እባክሽ ወደ ፍሬ ነገሩ ግቢ:: ሳንወጣ እዚሁ ልታስመሽብን እኮ ነው» አለ ድልነሳ ለመውጣት ቸኩሏል::

«ምነው እንዲህ ተጣደፍክ? ያች የትናትናዋ ልጅ ቀጥራሃለች እንዴ?» አለች ትሩፋት እየሳቀች::

«እሷው እንዳገተችኝ ቀርቼ በነበር:: መቋጫ በሌለው ፖለቲካ ከምታደርቁኝ የእሷው እስር ይሻለኝ ነበር:: ይልቅ ያመጣሽውን ጨዋታ አሰሚንና ውቧን አዲስ አሳበባ በጊዜ እንዝናናባት:: እናንተ ምን አለባችሁ:: ደስታውንም፣ ሀዘኑንም፣ ድሎቱንም፣ ችግሩንም፣ ፖለቲካውንም እዚሁ ውስጡ አብራችሁ ትኖሩታላችሁ:: እኔ በሰው አገር ያለሁት ግን ናፍቆቱ አልወጣልህ ብሎኛል:: በይ ትሩፌ ቶሎ ትረካሽን ንገሪንና እንውጣ::»

«እንዲህ ሆነላችሁማ! አንድ የአማርኛ ቋንቋ አስተማሪ ለጊዜው ማስተማር ስልችት ይላቸዋል:: ከፍል እንደ ገቡ የከፍል ሥራ ሰጥተው ወንበራቸው ላይ ማረፍ ይፈልጋሉ:: 'ልጆች ዛሬ አራት ስንኞች ያሉት አንድ ግጥም ትጽፋላችሁ:: ርእሱ ደግሞ እናት ኢትዮጵያ የሚለው ይሆናል' ብለው ጥቁር ሰሌዳው ላይ በጉልህ ይጽፋሉ:: የከፍሉን ተማሪ በሙሉ አንድ ጊዜ ዳር እስከ ዳር መልከት አድርገው ሄደው ወንበራቸው ላይ ጉብ ይላሉ:: ገና ከመቀመጣቸው አንድ ተማሪ 'ጨርሻለሁ ቲቸር' ይላቸዋል:: ፍጥነቱ ገርሟቸው 'አሰቲ ወዲህ በለው' ይሉና ደብተሩን ተቀብለው ግጥሙን ሲያነቡት

እንኳን አራት መስመር መቶም አይበቃሽ፣

እንዴው በደፈናው የጉድ አገር ነሽ:: ይላል ተማሪው ጽፎ ያመጣት ሁለት ስንኝ ግጥም:: ከየት እንደ እመጣት ወይም እንደ ሰማት አልገለጸም:: ዘመዶቹ የዚችን





አገር በሽታ ብናነሳ ብንጥለው መድሀኒቱ ገና አልተገኘላትም:: ኢትዮጵያ ገና የመከራ ጉዞዋ ያላለቀ የጉድ አገር ሆናለች:: ይልቅዬ 'ሕይወት አጭር ናት' ብሏል በእሉ ግርማ:: ይቺን አጭር ህይወት በማያልቀው የፖለቲካ ወሬ አበጨንቀን ይበልጥ አንዳናሳጥራት:: ተነሱ እንሂድ! አዲስ አበባን በምሽት እናድምቃት:: እንቀሳቀስ!» አለች ትሩፋት ለሄመድ እየተነሳች

******

አዲስ አበባ እንደ ወትሮው ሁሉ በኤሌከትሪክ ብርሃን አሸብርቃለች:: የለውጡን ነፋስ ወደ ውስጥ እየማገች መልሳ ታስወጣዋለች:: በየዳንኪራ ቤቱ አስረሽ ምችው ደርቷል:: የሽገር ቆነጃጅቶች አዲስ መጤ የጫካ ሰዎችን እንደ አጥቢያ ኮከብ በሚንቦገቦጉ ዐይኖቻቸው እያሽኮረመሙ-- ይገረሙሟቸዋል::

አነትሩፋት ምሽቱን ማሳለፍ የፈለጉት ሞቅ ደመቅ ያለ ባህላዊ ጭፈራ ባለበት የምሽት ከበብ ውስጥ ነው:: ለዚህ ደግሞ ካዛንችስ ተመራጭ ናት:: ምሽቱ የሚነጋባት:: ሁሉም የሚገኝባት፤ ሁሉም የሚያብድባት-- ካዛንችስ:: ጥሩ የባህል ሙዚቃ ይገኝበታል ብለው ከአሰቡት ቡና ቤት ገብተው ቦታ ሲያማትሩ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሪቫን ራሷ ላይ ሽብ ያደረገች ቀንበጥ ልጅ መጥታ በሞቀ ፈገግታ ተቀበለቻቸው::

«እንደ ምን አመሻችሁ:: እንኳን ደህና መጣችሁ» አለች በላቀ ትህትና:: እነትሩፋት አጸፋውን መለሱ:: የለበሰችው ጥልፍ ቀሚስ እንደ ሪቫኗ ሁሉ በኢትዮጵያ ባንዲራ ያሸበረቀ ጥለት አለው:: ከጥልፉ ጋር ልዩ ውበት አጎናጽፏታል:: እሷም ውብ ናት:: እየመራች ወሰዳ ጥግ ላይ ሦስት ወንበር ያለበት ቦታ አስያዘቻቸው:: እግረ መንገዷንም የሚፈልጉት ታዛ ከሚያምረው የባሕል ቀሚሷ ጋር በውብ አረማመዷ እየተውረገረገች ሄደች::

መድረከ ላይ ባህላዊ የአማርኛ ዘፈን ይዘፈናል:: ተወዛዋዦች አንገታቸው በሮ የሄደ እስኪመስል ድረስ አሰከታውን ያስነኩታል:: አንዳንዱ እድምተኛ በጭብጨባ አጅቧቸው አብሮ ይወዛወዛል:: ሳይታሰብ ከቤቱ አንደኛው ጥግ ላይ ከፍተኛ ድምፅ ተሰማ::

«ስምኢ አንቺ ትግርኛ ሙዚቃ እንዲዞፍን አድርጊ--» አለ አስተናጋጇን በከፍተኛ ጭብጨባ ጭምር እየጠራ:: ውስኪ ይዘው ከተቀመጡት አራት ሰዎች አንደኛው ነው:: ጩኸቱ ከሙዚቃው በላይ ነበር:: ሰው ሁሉ የየግል ጨዋታውን ትቶ ወደ ሰውየው በግርምት ተመለከተ::

«እሺ! ለሙዚቃ አቀነባባሪው እነግረዋለሁ» አለች ያችው ውብ አስተናጋጅ በትህትና:: ምንም ያህል ሳይቆይ አሁንም

«ለምን ነው ትግርኛ ዘፎን እንዲዘፎን ለምኑፈልግ ሰዎችን ትግርኛ የማይዘፎነው?» አለ አንደ ገና በቁጣ።

«ለሙዚቃ አቀነባባሪው ነግሬዋለሁ። ከሁለት ዘፈኖች በኋላ ይቀጥላል።» አለች አሁንም አስተናጋጇ ትህትና።

«ለምናባትሽ ነው አሁን እንዲዘፎን የማቱነግሪው— አንቺ ወዲ ሸርሙጣ!» አስተናጋጇን ገፍትሮ ወደ ትንሿ መድረከ ተንደረደረ። አደራሹ ውስጥ ያለው እድምተኛ ሁሉ ሰውየው ያበደ ነበር የመሰለው።

«እኛ ትግርኛ ዘፈን አንፈልግም። አንተ ከፈለግህ ከቤትህ ሄደህ ቴፕ ከፍተህ ተዝናና!» አለ አንድ ሰው ጮከ ብሎ። ከቤቱ መሀል ላይ ያለውን ጠረጴዛ ከበው ከተቀመጡት ሦስት ሰዎች መሀከል። የለከረ ይመስላል። ሲናገር አፉን ያዝ--ያዝ ያደርገዋል።

«ወዳአይቴ!! አንተአ ወዲ ሸርሙጣ! ለማናባትከ ነው እንዲ ትናገርው ያሎህ!» እለ በንዴት አየተንተገተገ። ወደ መድረኩ መሄዱን ትቶ ተናጋሪው ሰውዬ ላይ አፍጥጦ።

«ምን ታመጣለህ! ወንድ ከሆንከ ውጣና ይለይልኝ! እዚህ ሰው መሀል አይደለም መደንፋት!» አለ ያው ሰው አሱም በንዴት እየተንተባተበ።

«እዚ ሕዝቡ ሙሀል እሸናሃሎህ አንተ ውሻ!» አለ ወገቡን በአንድ እጁ እየዳበሰ። ሰውየው ምንም አልፈራውም። ሞቅታና ንዴት ድፍረት ሰጥተውታል።

«ሂድ ወድያ ቆርቆሮ! መሳርያ አይደለም የጀግንነት መለኪያ! ሂድ ውጣ ከዚህ! እቤትህ ትግርኛ ዘፈንከን አዳምጥ ብየሀለሁ አንተ ዘ-ረ-ኛ!» ቃላቶቹን እየረገጠ እሱም በንዴትና በልህ ነበር የሚያወጣቸው። እጠገቡ አብረውት የሚጠጡት ሁለቱ ሰዎች ዝም እንዲል ቢያከላከሉትም አሺ ብሎ ዝም የሚል አልሆነም፤ እንደውም ብሰበት ከጣራ በላይ መጮህ ጀመረ።

«እኔ አዬ ዘረኛ? አንተ ጮሙላቃ... » መናገር አልቻለም። እጁ ተንቀጠቀጠ ትግርኛ ይዘፈን ባዩ።

«አዎ ዘረኛ ነህ! እኔ እናቴ የወለጋ ሰው ናት፤ አባቴ ደግሞ ጎጃሜ። እናትና አባቴ ዘር ወይም ቋንቋን ተጠያይቀው አልተጋቡም። ዘራቸውን ቢጠየቁ ደግሞ በእርግጠኝነትና በኩራት የሚነግሩህ የነሱ ወላጆች የትግራይ፣ የጉራጌ፣ የከንባታ፤ የአደሬ፣ የወላይታ፣ የሲዳማ፤ የሱማሌ፣ የሸናሻ፣ የአኝዋክ፣ የአፋር.... የሌላም የሌላም ቅልቅል መሆናቸውን ነበር። ግን በየትኛውም መንግሥት ዘራቸውን ተጠይቀው አያውቁም። ዘር—ጎሳ ብሎ ነገር አይገባቸውም። በየሚኖሩበት አካባቢ ከኗሪው ጋር ተሰማምተው በደግ በከፉ ሳይለያዩ





በሰላምና በፍቅር ደስ ብሏቸው እብረው ኖረዋል። እኔም የማውቀው የሁሉም ዘር ቅልቅል አንድ ኢትዮጵያዊ መሆኔን ነበር። አሁን ግን አማራ ነኝ። አማራ መሆኔን የነከርከኝ ደግሞ አንተ ነህ!! አን---ተ!!» አለ በጠቋሚ ጣቱ ጭምር እያመለከተውና አሱም በንዴት እየተንቀጠቀጠ።

«አንተ ነፋጠኛ አማራ ዛሬ ለሬሳህን ነው እዚ ቤት የሚወጣው!»

«አሃሃሃ! አንተው ነህ አማራ መሆኔን የነከርከኝ አላልኩም! ይኸው አሁንም አማራ መሆኔን አረጋገጥኸልኝ። ነፍጠኝነትን ለጠፍከበት ደግሞ። አባቴን አግኝተህ ዘሩን ብትጠይቀው 'አገሌ አገሌን ወለደ ይልና አያት ቅድመ አያቶቹን ቆጥሮ አሱ ላይ ይደርሳል። ጎጃሜ መሆኑን የሚነግርህ ምን አልባት የተወለደበትን አካባቢ ከጠየከው ነው። በአጋጣሚ ምከንያት አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ በመሆኑ አማራ ነኝ አይልህም። እርግጠኛ ነኝ። እኔን ልጁን ግን ዛሬ በግድ አማራ ነህ ትለኛለህ! እኔነቴን በቋንቋዬ መድበህ! የኢትዮጵያ ከልሎች በቋንቋ ሰም የተሰየሙት በአንተ ጊዜ ነው በ—አንተ! » አለ እሱም በጩኸት። ምላሱን ያዝ ቢያደርገውም መናገሩን አላቆመምም። ትግርኛ ተናጋሪው ሰው ለግልግል አያስቸገረ ነው።

«ስማ አንተ ጠባብ ዘረኛ! ያሚያምረውን--- እንደ ልብ የሚያዝናናውን ሰፊ ኢትዮጵያዊ ካባዬን በግድ አስወልቀህ ጠባብ ጥብቆ ያለበሰከኝ አንተ ነህ! አን---ተ!! ጥብቆው ጠቦኝ እንድጨነቅ የፈረድከብኝ አንተ ነህ!! አን---ተ!! ራስህ ባመጣኸው ጦስ አማርኛ ዘፈን እየሰማህ ተጨነቃት! ዛሬ እያንገሸገሸህም ቢሆን እውነቱን እነግርሀለሁ ልብ ካለህ ሰማ!!

የሰው ዘር መገኛ--- የሰው ልጅ ስልጣኔ መነሻ ባለረጅም ታሪክ የሆነችውን አገር አሳንሰህ በመቶ ዓመት ታሪክ የገደብካት አንተ ነህ!! አን---ተ!! እንደ ቀስተደመና ከሰማየ ሰማያት ወርዶ መለኮታዊ ክብር ያለው የሚመሰለውን ባንዲራችንን ጨርቅ ብለህ ያንቋሸሽከ አንተ ነህ!! አን---ተ!! አገር አንደ ቡና ቁርስ ዳቦ ቆራርሰህ አንሰህ ያሳነሰካት አንተ ነህ!! አን---ተ!! ተዋርደህ ያዋረድከን ትንሽ ጎጠኛ ሰው ብትኖር አንተ ነህ!! አን--ተ!! እግዜር በጥበቡ የቀይ ባህር በር ባለቤት ያደረጋትን ውብ አገር ነጥቀህ ለሌላ አሳልፈህ የሰጠህና ያለ ባህር በር ያስቀረሃት ለትውልድ የማታሰብ ከፉ ምቀኛ አንተ ነህ!! አን---ተ!! መልከህ እኔን ቢመስልም እኔን ያልሆንከ ሹምባሽ ነህ!! ጣሊያን ያልቋጨውን ሥራ ልትጨርስ የተነሳህ የጣሊያን ሹምባሽ!! በገዛ እጅህ ባመጣኸው መዘዝ አብረህ ከኔ ጋር ተቀጣ! ሄደህ ከጠባቧ ቤትህ ገብተህ ተዘጋ! ከዚያ የትግርኛ ዘፈንህን ለብቻህ ስማ!! ካልፈለግህ ደግሞ እዚህ ከአኛ ጋር የአማርኛ ዘፈን በግድህ ትሰማታለህ!! ኢትዮጵያዊነቴን ገፈህ በግድ አማራ እንድሆን እንደ ፈረድከብኝ ሁሉ!.......» ትግርኛ ይዘፈን ባዩ ከጎኑ ሸጦት የነበረውን ሽጉጥ ላጥ አድርጎ ወደ ሰውየው ተንደረደረ። አላመነታም በሽጉጡ ሰደፍ ግንባሩን አጎነው። ሰውየው ተቀምጦበት ከነበረው ወንበር ላይ ተንገዳግዶ ወደቀ። በአካባቢው የነበረ ወንበርና ጠረጴዛ ሁሉ ወዳደቀ። እላዩ ላይ የነበረው መጠጥ ሁሉ መሬቱ ላይ ሿ ብሎ ወለሉ ላይ ሲሰባበር ጩኸቱ ቤቱን ሞላው። ሁሉም ነገር ተተረማመሰ።

«ግደይ! ንዚህ ወዲ ከልቢ አድጊ ሰካራም ግደፈው! ካብ ነብሱ እይኮነን ይዛረብ ዘሎ» ( ግደይ! ይህንን ሰካራም የውሻ ልጅ አህያ ተወው! የሚናገረው ከልቡ አይደለም) አለ ጓደኛው፡፡ ተንደርድሮ መጥቶ እየያዘው፡፡ ጓደኞቹ ራሳቸው ተደፈርን ብለው ሲደነፉ ነበር፡፡ ሆኖም የሰውየው ድፍረት በሰካር መንፈስ ነው ብለው ሰላሙኑ ቀለል ለማድረግ እየሞከሩ ነው፡፡ ጓደኞቻቸውን እየገላገሉ፡፡

«ቆይ! አንተ ሀጣራው ሰካራም ነፍጠኛ! ነገ ከነብሰህ ጋር አገኝሃለሁ!» ዛተ ትግርኛ ይዘፈን ባዩ፡፡

«ሰውየው እኮ እየደማ ነው፡፡ አንቡላንስ ይጠራና ሕኪም ቤት ይሂድ» አሉ ይነበብና ድልነሳ፡፡ ሰውየውን ለማንሳት ወደዚያው እየተንደረደሩ፡፡

«ማንም ሰው እንዳያነሳው!» ብሎ አከታትሎ ሁለት ጥይት ወደ ላይ ተኮሰ፡፡ ሁሉም በያለበት ኩምሽሽ አለ፡፡ ከባለ መሳሪያ ጋር ማን ይታገላል? ትግርኛ ይዘፈን ባዩና ጓደኞቹ ብዙም ሳይቆዩ እየዛቱና እየተሳደቡ ወጥተው ሄዱ፡፡ መራቃቸው ሲረጋገጥ አንቡላስ ተጠርቶ በሰደፍ ተመትቶ የወደቀው ሰው ወደ ሀኪም ቤት ተወሰደ፡፡ እንዲህ እስከ አፍንጫው ነግሮት አለመግደሉም የተባረከው ገጥሞት ነው፡፡ ባረባ ነገር ሰንቱ ደሙ ደመ ከልብ ሆኖ ቀርቷል፡፡ በተፈጠረው ሁኔታ እነትሩፋት በጣም አዘኑ፡፡ የይነበብ ልብ ግን ቆስሎ እየደማ ነበር፡፡

«ከአንዱ እምባገነን መንግሥት ወደ ሌላው አምባገነን መንግሥት ለመሸጋገራችን ከዚህ በላይ ማረጋገጫ ሊኖር አይችልም፡፡ ትግል እንደ ገና 'ሀ' ብሎ መጀመር አለበት የምላችሁ ለዚህ ነበር» አለ ይነበብ፡፡ ወደ ቤታቸው ለመሄድ ታክሲ ሲይዙ፡፡

«እውነትከን ነው ይነበብ፡፡ ከነዚህ ሰዎች ጋር በተናጥል አፍ መካፈቱ ትርፉ እንደ ሰውየው በተናጥል መጎዳት ነው የሚሆነው፡፡ ግን ይተርፍ ይሆን? በጣም ተጎድቷል እኮ! ብዙ ደም ፈሶታል፡፡ እንዴት ያሳዝናል!» አለች ትሩፋት ከልቧ አዝና፡፡

«ምንም አይሆንም፡፡ ግንባሩ ላይ ነው የተመታው፡፡ ከመኪናው ላይ ስናወጣው ደሙም እየቆመ ነበር፡፡ ትንሽ ሞቅ ስላለው ነው እንጂ እመኚኝ ትሩፋት ብዙ ጉዳት የለውም፡፡ ግሰላ መስሎ እንደ መነሳቱ ተኩሶ ቢገለውስ ኖሮ ማን ጠያቂ ነበረው? ሕግ በሌለበት አገር መሳሪያ የየያዘ ሰው ሁሉ ራሱ ሕግ ነው፡፡ ሊያስር ሊፈታ ይችላል፤ ሲያስፈልገው ደግሞ እንደ ቅድሙ በሰደፍ ያጎናል፤ ሲያሻውም ሊገድል ሁሉ ይችላል፡፡ አድሜ ለሽጉጥ! ገደብ የሌለው ሙብት ሰነሱ ብቻ አጎናጽፏቸዋል» አለ ይነበብ በቁጭት፡፡

«ወይ ጉድ!! እንዴት ሰው ንቀዋል እባካችሁ! በዚህ አያያዛቸው ሰው በአገሩ ላይ በነፃነት እንዲኖር የሚያደርግ ሁኔታ እላየሁባቸውም፡፡ በሉ ዘመዶቼ ኢቃዬን ጠቅልዬ አገር ቤት





የመግባት ሀሳቤን አንስቼዋለሁ፡፡ የአሜሪካንን የነፃነት ኑሮ ለምጄ ይህንን የመሰለ ግፍ የምቋቋመው አይሆንም» አለ ድልነሳ፡፡

ትሩፋት ጧት ወደ ትምህርት ቤት ስትሄድ ሁሉ የትናንትናው ምሽት ሁኔታ እድሮም አልተረሳትም ነበር፡፡ በነዚህ ጎጠኛ ሰዎች እጅ ውሰጥ ይህ መከረኛ ሕዝብ መውደቁ አሰግቷታል፡፡ የዚች አገር እጣ ፈንታ አስፈርቷታል፡፡ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ከፍለ ጊዜዎች አስተምራ ስትወጣ ሁሉ የዚያ ባለመሳሪያ ሰውየ ማንአለብኝነትና ጥጋብ እየከነከናት ነበር፡፡

የእለቱ የማስተማር ሥራ አልቆ ወደ ቤቷ ስትሄድ ሁሉ በዚህ እድሜዋና አቅሟ ምን ልታደርግ እንደምትችል እያሰበች ነበር፡፡ ያ የትግል ጊዜ አልፎ ጉልበቷን ሁሉ ወደ ቤተሰቧ ባዞረችበት በዚህ ሰዓት ተንኳሽ ሁኔታ እየተፈጠረ እንደገና ለትግል የመነሳሳት ስሜት እየተፈታተናት ተቸግራለች፡፡

«ዘመድኩን ትክክል ነው እኛ የተፈጠርነው ለታሪክ ጥሪ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ይነበብም ትክክል ነው፡፡ ለዳግም ትግል መነሳት ሳያስፈልገን አይቀርም፡፡ እኛ ባንታደልም ልጆቻችን ዲሞክራሲ በሰፈነባት ባደገችና በበለጸገች አገር ውስጥ በነፃነት ሊኖሩ ይገባል፡፡ ይሄ ደግሞ መራር ትግልን ይጠይቃል፡፡» በአገሪቱ ውስጥ እንደአሸን የተፈለፈሉትን ድርጅቶች አንድ ባንድ አሰበቻቸው፡፡ ሕብረ ብሔር የሆኑትን ብቻ ለይታ ልትመረምራቸውና የትኛው ከየትኛው የተሻለ ፕሮግራም እንዳላቸው በሀሳቧ ልታወዳድራቸው ሞከረች፡፡ ያን ያህል አጥጋቢ ሆነው አላገኘቻቸውም፡፡

«ኢሕአፓንና መኢሶን ያን ያህል የጎላ ልዩነት ሳይኖራቸው በተናጥል ቆመው ለአምባገነኑ የደርግ በትር ተመቻችተው በመገኘታቸው በየተራ ወደቁ፡፡ ዛሬስ... ? ሕብረ-ብሔር ድርጅት ነን የሚሉት እንኳ ልዩነታቸውን አጥብበው ለምን አንድ ላይ ቆመው በጋራ አይታገሉም?» መልስ ያላገኘችለት የማይገባት ጥያቄ ነው፡፡ በዚህ የችግሩ ስፋት ባየለበት ሁኔታ እንዴት መታገል እንደሚቻል ብታውጠነጥንም የታያት መላ አልነበረም፡፡ ይህን ማሰቂያ የሌለው የዚህች አገር ችግር ምንም ብታሰብ ምንም መፍትሄ ልታገኝለት አልቻለችም---ቀጣዩ አገር ተረካቢ ትውልድ አሳዘናት፡፡

«ጥቁር ሌሊት»

«የከበደ ሰርግ እሁድ ነው ትሩፌ:: እንዴት እየሄደለት እንደሆነ ሄጄ ልይለት:: የጎደለ ነገር ቢኖር በእኔ አቅም ልረዳው የምችለው ነገር ካለ ጠይቄው ልመለስ:: ከሥራ ቀደም ብዬ የመጣሁት ለዚሁ ስል ነው» አለ ይነበብ:: ዐይን ዐይኗን እያየና እጇን ያዝ አድርጎ እያሻሸ::

«ለእሁድ ሰርግ ዛሬ ምን የሚሰራ ሥራ ይኖራል ብለህ ነው ይነበብ?» አለች ትሩፋት እንዳይሄድ መፈለጓ ፊቷ ላይ ያስታውቅባት::

«የሰርግ ሥራ ያልቃል ብለሽ ነው ትሩፌ? አንዱን ሲይዙት ሌላው ያፈተልካል:: ጣጣው ብዙ ነው:: ቀደም ብሎ ቢጀመርም እስከ መጨረሻዋ ቀን ድረስ አያልቅም:: የአንቺን ሰርግ አባትሽ ስለተወጡልሽ ከብደቱ ምን ያህል እንደ ሆነ አታውቂውም::

«መቼም በእርብ ምድር በሬ አይጣል---ድንኳን አይተከል:: ምን ሥራ ልትሠራ እንደምትሄድ አይገባኝም?»

«የጥንት የጠዋቱ ወዳጆችን አዲስ የሕይወት ምዕራፍ ሲከፍት ሲሰናዳ ማገዝና መጠየቅ አይገባም? ትሩፌ? የእለቱ እለትማ ሁሉም ሰው ይገኛል እኮ:: የቁርጥ ቀን ጓደኛን የሚለየው ቀደም ብሎ የጎደለውን በማሟላት መረዳዳቱ ነው:: የሚታገዝ ነገር ካለ ሄጄ ብጠይቀው ይሻላል:: እንደውም አብረን ብንሄድ ከበደን ደስ ይለው ነበር:: ሊያልፍ ቀን እዳያስተዛዝበን:: ጥብቅ ጓደኛን በቀላል ነገር እንደ ማጣት ያለ ከባድ ፀፀት የለም::»

«ዛሬን ቅርና ነገ አብረን እንሄዳለን ይነበብ በእናትህ!---በኔ ሞት!» አለችው በሚያባብል ዐይን እያየችው::

«እንኳን ሞትሽ እንቅልፍሽ እንደሚያሳዝነኝ እያወቅሽ ትሩፌ:: ምነው ልቤን እንዲህ የምታስጨንቂው? መቅረቱንስ ልቅር እሺ! ግን አያሳፍርም? ኧረ የወዳጅ ስራ አይደለም!» አለ ይነበብ በመሄድና ባለመሄድ መካከል ልቡ እየዋለለ::

«እንግዲያው ቶሎ ደርሰህ ተመለስ:: እንዲሁ ከቤን ደስ እንዲለው ነው እንጂ---ሥራው ያለው ነገ ነው::»

«የምረዳው ነገር ከሌለ አልቆኝም:: የኔ ፍቅር ሙች! ስበር ነው የምመጣልሽ::» አለና መሀል እጇን ቀስ አድርጎ መታ አደረገ::

ከበደ የቆየ ጓደኛቸው ነው:: ያውም የዚያ ትውልድ ውድ ጓደኛቸው:: እሷም መሄድ ነበረባት:: ግን ደግሞ ምክንያቱን ለይታ ባላወቀችው ነገር የይነበብን መሄድም





አልወደደችውም:: ደርሶ ልቧን ከብድ-- ከፍት የሚል ስሜት ተሰምቷታል:: በጣም ቅር እያላት ነው ተነስቶ የሄደው:: ከቤት እንደ ወጣ ብዙ አልቆየም::

«አራት ኪሎ.. አራት ኪሎ» አለ ረዳቱ-- ከታክሲው በላይ ግማሽ አካሉን አዝልቆ። ቤልጂየም ኤምባሲ ፊት ለፊት እያቆመ:: ይነበብ ገባ:: እንዳጋጣሚ ሆኖ ወደ ካዛንቺስ የሚሄደው ታክሲም ብዙ አላስቆመውም:: ታክሲ በመጠበቅ ጊዜ ባለማጥፋቱ ደስ አለው:: ከከበደ መኖርያ ቤት ባሰበው ሰዓት ደረሰ::

«እየመሸብህ ነው ይነበብ ትራንስፖርት ታጣለህ:: ይልቅ ነገ አንተም ትሩፋትም ማልዳችሁ እንድትመጡ:: ሸንኩርት መከተፍ--ሊጋ መዘልዘል የእሷ የሥራ ኃላፊነት ነው:: በኋላ እንዳንጣላ! ያለእናንተ ማንም እንደሌለኝ ታውቃላችሁ» አለ ከበደ:: ይነበብ ጋር ስለ ሰርጉ ብዙ ከተወያዩ በኋላ::

«ኧረ ለነገውስ አትስጋ በጧት እዚሁ ነን:: የራሳችን ሥራ እኮ ነው:: አደራ መባል አይገባንም» አለ ይነበብ:: በሬ ለመጣልና ድንኳን ለመትከል በጣም በጧት መምጣት እንዳለበት እያሰበ:: ቀጠል አደረገና «በቂ የመኝታ ቦታ የምታገኝልኝ ከሆነ እዚሁ ማደር እችላለሁ» አለ ይነበብ:: ከልቡ ነበር::

«በስርጌ እለት አብራኝ እንዳትውል ከትሩፌ ጋር ልታጣላኝ አስበህ ካልሆነ በስተቀር ማደርን አታስበውም» አለ ከበደ::

«እየቀለድኩ አይደለም ከቤ:: ትሩፌ እንዳታስብ ደውለን እንነግራታለን:: ብቻ አንተ የመኝታ ቦታ አግኝልኝ» አለ ይነበብ አሁንም ከምሩ::

«እኔ ትዳር ልመሰርት እየተውተረተርኩ የለው ትዳር አላፈርስም ጓድ!»

‹ሐይዞህ አትሰጋ! የእኔና የትሩፌ ትዳር መሰረቱ የጠበቀ ነው:: እንዲህ በቀላሉ የሚነቃነቅ አይደለም:: እንደ ወርቅ በእሳት ተፈትኖ አልፏል» አለ ይነበብ በኩራት::

«ግድ የለም! ነገ ለስራው በጣም በጧት ከመጣችሁ ይበቃል:: እሁድ ደግሞ እንገታችሁ ይታያል:: ባይሆን እንዳንተና እንደ ትሩፋት ሰርግ ጊዜ ዘፈኑን ወደ ፖለቲካ ቅስቀሳ የሚቀይር ትውልድ አይኖርም:: የእኔ ሰርግ ላይ የፖሊስ ከበባ አያስፈራም:: ያሻህን ግጥም እየገጠምክ መዝፈን ትችላለህ:: በተጎናጸፍነው ዲሞክራሲ በነጻነት መጨፈር መብትህ ነው» አለ ከበደ:: ጥይም ፊቱ ላይ ፈገግታ አይጠፋም:: ጎላ ጎላ ያሉት ዐይኖቹ እንቅልፍ የጠገቡ አይመስሉም:: ቀልተዋል::

«የአብዮት ቅስቀሳ ለማካሄድ ምን የተረፈ ወኔ አለ ብለህ ከቤ? ወኔያችንን ሁሉ ጨካኙ የደርግ መንግሥት ለልቦ ጨርሶት ሞቷል:: እንግዲያው ጭቆናውና ፍትህ መጓደሉ የዘር

ልዩነት ካባን ደርቦ ከትናንቱ ዛሬ ብሷል። ካልከሰ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅስቀሳና ትግል የሚያስፈልገው ዛሬ ነበር--- አሁን!» አለ ይነበብ በጠቋሚ ጣቱ ወደ መሬት እያመለከተ።

«በል--- በል ወንድሜ ስርጌን በሰላም ላካሂድበት! ወያኔዎች አንደ ሆኑ ገና ለገና በሆድህ ምን አለ ብለው የሚጨነቁና የሚፈሩ ጠርጣሪዎች ናቸው። ተጠራጣሪና ፈሪ ደግሞ አሳዶ አፈር ካላለበሰ አይመለሰም። ቆራጥ ጀግና ያልተወለደባት ባዶ አገር እንደ አገኙ አላወቁም። ከመሬት ተነስተው ይሰጋሉ። ይልቅስ ፖለቲካውን ተወውና ነገ በሌሊት እንድትመጣ በጊዜ እቤትህ ግባና ረፍት ውሰድ። ለነገና ለአሁድ ጉልበት ታገኛለህ» አለ ከበደ።

«አ!! የኔ ነገር ያለጊዜውና ያለቦታው ያልሆነ ነገር ውስጥ ገባሁ መሰል ይቅርታ ከቤ። ምን ላድርግ ብለህ ነው? ለልጆቼ የማወርሳት የነገይቱ ኢትዮጵያ ነገር በጣም ያስጨንቀኛል። የዚች ጣጠኛ አገር ጉዳይ በየተሄደበት ሁሉ መቼ የሚለቅ ሆነ። የመጣሁበትን ዋና ጉዳይ አሰረሳኝ እኮ! እንግዲህ ምንም የጎደለ ነገር የለም እያልከኝ ነው? ሥራ ካለ ግን ሰዓቱ ገና ነው። ትራንስፖርት ችግር የሚሆነው ከአስራ ሁለት ሰዓት በኋላ ነው።»

«ሙት ይነበብ ሁሉንም ነገር ከወር በፊት ነው አዘገጃጅተን የጨረስነው። እንዳንዋከብ ብለን።»

«እንግዲያው እኔም ትሩፋትም ነገ በጧት እንመጣለን ደህና እደር ከበደ።» ሊሰነባበቱ ሁለቱም የነገ ጧቱን ቀጠሮ እያሰቡ ነበር። ይነበብ ታክሲ ለመያዝ ሲወጣ የሚያዚያ ፀሐይ ንዳዷን ለቃዋለች-- እናት ትበሳለች። ሰዓቱ አስራ አንድ ሰዓት ቢሆንም ግለቷ ገና አልበረደም። ቀዩን መብራታቸውን አንቦግቡገው ካዛንችዝን ድምቅ የሚያደርጉት ጭፈራ ቤቶች አልተከፈቱም። ሰምሽት ጉልበት ቀኑን እንቀላፍተዋል። በዚያ ላይ ሙቀቱም ተኙ ተኙ ያሰኛል።

******

ድንገት «ቁም» የሚል ከባድ ድምፅ ሰማ ይነበብ። ለእሱ መሆኑን እየተጠራጠረ ድምጽ ወደ ሰማበት አቅጣጫ ዞር ከማለቱ ሲቪል የለበሱ አራት ሰዎች ከአንዲት ነጭ ቶዮታ መኪና ውስጥ በፍጥነት ወርደው በፍጥነት መሀል አስገቡት። ያልወረደው ሾፌሩ ብቻ ነበር። ወድያው ሽጉጥ አውጥተው ሲደግኑበት ፋታ አልሰጡትም። የትም መሄድ አይችልም። በጠራራ ፀሀይ ያውም በአገር ሰላም--መንግሥትና ሕግ አለባት በምትባል አገር ውስጥ እንዲህ ያለ የማፍያ ሥራ ይገጥመኛል ብሎ አልገመተም። በዚያው ፍጥነት አራቱም እየገፈታተሩና በሽጉጥ ሰደፍ እየጎሻሸሙ መኪናዋ ውስጥ ሲያስገቡት--ለመናገር ቀርቶ ለመተንፈስ ጊዜ አላገኘም። መኪናዋ ሽምጥ ጋልባ ከአካባቢው ተሰወረች።





«አንካ አሞ! በዚ ጨርቂ ለዐይኑን ግጥም አድርገህ እሰርልይ» አለ ከሾፌሩ ጎን የተቀመጠው።

«ቆይሞ! ምጅመር እጁ ካቴና ይግባለት። ቀሊል አይደልም። በስፖርት የዳበረ ጡንቻኛ ዎጠምሻ ነው» አለ ከአራቱ ፈርጠም ያለው ጉልበተኛ ነኝ ባይ። ይነበብ ላለመታሰር ሙከራ ሲያደርግ የሦስት ሰው እጅ ተረባረበበት። መተንፋስ አቃተው። እጁን ለኋሊት ጠምዝዘው ካቴና አስገቡለት። በጥቁር እራፊ ጨርቅ ዓይኑን ግጥም አድርገው አሰሩት።

«ቆይ! እናንተ እነማን ናችሁ? ከእኔ ምንድነው የምትፈልጉት?» አለ ይነበብ የሞት ሞቱን።

«ዞም በል! ለእሱን በኋላ ቱዶርሱበታሎህ!» አለው አንደኛው። ኃይለኛ የጫማ ርግጫ ታፋው ላይ አያሳረፈ።

«መንግሥትና ሕግ ባለበት አገር እንደ ሌባ ለምን ታፍኑኛላችሁ? ጥፋት ካለብኝ ለምን በሕግ አልጠየቅም?» አለ ይነበብ። ሰዎቹን የሰከንዶች እድሜ ያህል አይቷቸዋል። በፍጹም አያውቃቸውም። ከአሁን በፊት የትም አላያቸውም። የትም አግኝቷቸው አያውቅም። በግል የመጡ ጠላቶች እንዳልሆኑ አውቋል። በመሳርያና በመኪና አፍኖ የሚወስድ የግል ጠላት ብሎ ነገር የለውም። በኖረበት ዘመን ሁሉ የከረረ የግል ጠብ ከሰው ጋር ተጣልቶ አያውቅም።

«በሕግ የሙመራ መንግሥት ሞኖሩ አሁን ነው የሚገባህ ያሎ? እስካሁን የት ነበርከ? ቆይ ጠቡቅ ገና በደንብ ይገባሃል!» ብሎ ዐይኑን ያሰረው ሰው በጥፊ አጮለው። ሌላኛው ደግሞ በጡጫ ተቀበለው። እንዲህ ሲቀባበሉት ከመኪናው ወንበር ላይ ተንሸራቶ ወለል ላይ ሊወድቅ ሲል የፊት ለፊቱ ወንበር ብረት ግንባሩን ከፉኛ አገኘው።

«ከአሁን በኋላ ምንም ዓይነት ድምጽ አሰማሎህ ቡትል ለዚህን ጭንቅላትህን ብትንትን አደርገዋሎህ» አለ አንደኛው ሰው የድምጽ መከላከያ የተገጠመለትን መሳሪያ ጆሮው ላይ አስጠግቶ።

ይነበብ ድንገት የገጠመው ዱብዳ ነገር አስደንግጦታል። አፋኞቹ የት ቦታ እንደሚወስዱት ማወቅ አልቻለም። ሲገምት ግን ወደጦር ኃይሎች አቅጣጫ የሚነዱ መስሎታል። ለአንድ ሰዓት ያከል ከተጓዙ በኋላ ከአንድ ጸጥ ረጭ ካለና ብቻውን ካለ ግቢ ሲደርሱ ትልቅ የብረት በር ተከፍቶ መኪናዋ ገብታ ቆመች። ግቢው ረጅም የግንብ አጥር አለው። መሀል ላይ ጉብ ያለው ትልቁ ቪላ ቤት የቆየ ነው። በዱሮ ሞድ የተሰራ አሮጌ ሕንፃ። የጥሩ ሀብታም ቤት የነበረ ለመሆኑ ነጋሪ አያስፈልግም። የአሁኑ አያያዙ ግን የድሮ መስህብነቱን አሳጥቶታል። ዙሪያውን የተተከሉት አበቦች ተመልካችና ተንከባካቢ አጥተው ደርቀዋል። የቆየ ውበታቸው ከቅጠሎቻቸውና ከአበቦቻቸው ጋር አብሮ ረግፏል።

ይነበብ ዐይኑ እንደ ታሰረና እጁ ለኋሊት ካቴና እንደ ገባለት እየገፈታተሩ ከመኪናዋ አወረዱት፡፡ ከወዲያ ወዲህ እያንገላቱ ወሲደው ከትልቁ ቪላ ቤት ውለጥ በምትገኝ አንዲት ትንሽ ጠባብ ከፍል ውሰጥ አስገቡት ከፍሏ ከዚያ ትልቅ ቪላ ቤት ውሰጥ ለምን ተብላ እንደ ተሰራች መገመት ይከብዳል፡፡ ከጥበቷ መጨለሟ ይብሳል፡፡ ዐይኑ የታሰረበትን ጨርቅ ፈተውለት ራሱን ገና ሳይገዛ ወደ ከፍሏ ገፍትረው ሲያስገቡት ዐይን ቢወጉ በማይታየው ጨለማ ከፍል ውለጥ ተፍገምግሞ በአፍጢሙ ተደፋ፡፡ አፍንጫው በመጎዳቱ መድማት ጀመረ፡፡ ፊቱ ላይም መጋጋጥ ደረሰበት፡፡ እጁ ለኋሊት በመታሰሩ ለመነሳት ተቸግሮ ነበር፡፡ በለንት መፈራገጥ የቤቷን ግድግዳ በማግኘቱ ነበር ተነለቶ መቆም የቻለው፡፡ «መብራት እንዳታበሩ» የሚል ረጅም ድምጽ ከሌላኛው ከፍል ተሰማ፡፡

ይነበብ በጨለማው ውለጥ ዓይኑን አፈጠጠ፡፡ ምንም ነገር ሊታየው አልቻለም፡፡ እንደ ቆመ የከፍሉን ስፋት ለማወቅ ፈለገ፡፡ እጁን በካቴና ወደ ኋላ እንደ ታሰረ እንዳይወድቅ ሚዛኑን እየጠበቀ አንድ እግሩን ዘረጋ፡፡ ትንሽ እየተራማደ እንደ ገና እየዘረጋ የቤቱን ግድግዳ መፈለግ ያዘ፡፡ አንድ ሦሰት እርምጃዎች እንደ ተራመደ አንደኛው ከፍሉ ግድግዳ የተዘረጋ እግሩን አገኘው፡፡ ጀርባውን ለግድግዳው ሰጥቶ ለሰንት ሰዓት እንደ ሆነ ባያውቅም ብዙ ቆሞ ቆየ፡፡ ከውሻ ጩኸት በለተቀር በአካባቢው ምንም ድምጽ አይሰማም፡፡ እፍነው አዚህ ቦታ የወረወሩት ሰዎች ይመጡ ይሆናል ብሎ ጆሮውን አቆም አዳመጠ፡፡ ብቅ ያለ ለው አልነበረም፡፡ ፀጥ ረጭ ያለ ከባድ ጨለማ---ፀጥ ረጭ ያለ ከባድ ሌሊት--- መውጫ በሌለው በተወላሰበ ሀሳብ የተዋጠ ከባድ ረጅም ጥቁር ሌሊት.....

«ቶሎ እንድመለሰ እንዲያ ለትወተውተኝ ከናካቴው እንደ ወጣሁ ቀረሁባት፡፡ አቤት ጭንቀቷ!» ትሩፋት ነበረች ከተወላሰበው ሐሳቡ መሀል ብቅ ያለችው፡፡

«የደርግ መንግሥትን ጥሎ ሕዝባዊ መንግሥት ለመመስረት በተደረገው ትግል ገና በአፍላ የኮረዳነት ዘመኗ አሳር መከራዋን አየች፡፡ ለዚያ ሳይቋጭ ለቀረ ትግል ከአራት ዓመት በላይ ታስሬ ሰንቅ በማመላለሰና በመጠየቅ ብዙ ተንገላታች፡፡ ብቻዋን ቤተለብ በማሰተዳደርና ልጅ በማሳደግ ማሰነች....» የትሩፋትን ነገር ሲያሰበው በደለኝነት ተለማው፡፡ ቤተሰብ ለማሰተዳደር የከፈለችው መሰዋእትነት ልቡን ነካው፡፡ ድካሟ-- ደከመው፡፡ ከባለቤቷ ማግኘት የሚገባትን እንከብካቤና ፍቅር ሳታገኝ እሱ በታሰረ ቁጥር ለንቅ አቀባይ ሆና የልጅነት ጊዜዋ በከንቱ ማለፉ አንገበገበው፡፡ ልጆቹም አሳዘኑት፡፡ የጅማ ዩንቨርሲቲ የመጀመርያ ዓመት ተማሪ የሆነው የመጀመሪያ ልጁ የአባቱን ድጋፍና አይዞህ ባይነት ይፈልጋል፡፡ ራሳቸውን ያወቁ ትልልቆች ቢሆኑም ያባት እንከብካቤና ፍቅር ገና ያሰፈልጋቸዋል፡፡ ከእናታቸው ጋር ሆኖ የሕይወት ልምዱን ሊያካፍላቸው ይገባ ነበር፡፡ እየጎረመሱ በሄዱ ቁጥር መልካሙን የኑሮ አቅጣጫ ለመጠቆም አባት ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ ይህችን ውጣ ውረድ የበዛባትን ዓለም በእውቀት ዘልቀው በዘዴና በብልሃት እንዲኖሯት ከእንግዲህ ላያግዛቸው ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ በማን እንደ ታፈነ እንኳ አያውቅም፡፡ ፈጽሞ ባላለበውና ባልጠበቀው ለዓት እጁ የፍጥኝ ታስሮ ባዶ ጨለማ ከፍል





ውለጥ ተወርውሯል፡፡ አቤት ጭንቀት! ማለቂያ የሌለው ሐሳብ! መቋጫ የሌለው አታካች ከባድ ጥቁር ሌሊት......

ይነበብ ናላው እስኪዞር ተጨነቀ--- ትሩፋትን ላለማሰብ ብዙ ሞከረ፡፡ ብዙ ጣረ፡፡ ግን አልቻለም፡፡ ሙሉ እሱነቱን ተቆጣጥራ ከፊቱ አልጠፋልህ አለችው፡፡ ለሰሷ ያላለበው---- ለለሷ ያልተጨነቀው ምን ነገር ይኖራል? የቤተሰቡን ሸከም ለእሷ አሸክሞ እምባገነኑ የደርግ መንግሥት በወደቀ ማግሰት ዛሬም ዳግም በሌላ አፋኝ መንግሥት እጅ ላይ ወድቋል፡፡

ከሁሉም ይልቅ ከፋኛ ያሰጨነቀውና የገረመው ደግሞ ገና ከመጠንሰሱ «እንዴት ሊደርሱበት ቻሉ?» የሚለዉ ጥያቄ ነበር፡፡ ከሞት የተረፉ ጥቂት ጓዶች ሳይቋጭ የቀረውን የትግል ጉዞ ለመቋጨት አሰቡ፡፡ የጎጥ አደረጃጀት ለዚች አገር አደጋ ያመጣል ብለው የለጉ ጓዶች በከፍተኛ ምሥጢር ተወያዩ፡፡ በአገር ውሰጥና በውጭ አገር የሚኖሩ እንደ ነፍስ የሚዋደዱ እንደ ክርሰቶስ የሚተማመኑ ጥቂት ሰዎች ተደራጅተው እንደ ገና ሊታገሉ ይወሰናሉ፡፡ የሕወሀት አገር አፍራሽነት የቆረቆራቸው የዚያ ትውልድ አገር ወዳድ ጓዶች ለዳግም ትግል ይነሳሉ፡፡ ውጭ አገር ያሉት የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርጉና የዲፕሎማሲውን ሥራ እንዲያከናውኑ ወሰኑ፡፡ እነይነበብ ደግሞ አባላትን በሕቡዕ በማሰባለብ እንዲያደራጁና የፕሮፓጋዳውን ሥራ በሰፋት አገር ውሰጥ እንዲሰሩ ይሰማማሉ፡፡

የትግል መዋቅሩን በድብቅ በአገሩቱ በሙሉ ለመዘርጋት ይነሳሉ፡፡ በሕወሀት የስለላ መረብ ውሰጥ እንዳይወድቁ በከፍተኛ ጥንቃቄና በከፍተኛ ምሥጢር በጥብቅ የተያዘ ነበር፡፡ ገና ትግሉ ሳይጀመር--ገና የረባ ሥራ ላይሰራ---ገና በጥንሰሱ መታፈኑ ለይነበብ እንቆቅልሽ ሆኖበታል፡፡ «ምሥጢር እንዴት ሊወጣ ቻለ?» ለሚለው ጥያቄ መልሰ እላገኘም፡፡ ማንን ይጠርጥር? እንደ ቆመ ብዙ አወጣ አወረደ፡፡ መድከሙ የታወቀው ጎልበቱ ሲንቀጠቀጥ ነበር፡፡ እጁ የኋሊት በካቴና እንደ ተጠፈረ ግድግዳውን ተደግፎ ጉልበቱን እጥፍ አድርጎ ተቀመጠ፡፡ በኋላም ሊብሰበት እግሩን ዘረጋ፡፡ የወለሉ ለሚንቶ ቅዝቃዜ የለበሰውን ሱሪ አልፎ አጥንቱ ድረሰ ተሰማው፡፡ አንቅልፍ ሳይወሰደው አድሮ ሊነጋጋ ሲል ነበር ሸለብ ያደረገው፡፡ ወድያው ግን በሩ ተከፈተና ሁለት ሰዎች ገቡ፡፡ በሰላም ነበር ያነጋገሩት፡፡

«እንደምን አደርከ አቶ ይነበብ» አለ አንድ ቀጠን ያለ ፊተ መጣጣ ሰው አተኩሮ እየተመለከተው፡፡ አብሮት አንድ ወፈር ረዘም ያለ ጥሩር ሰው አለ፡፡ የሚሆነውን ዝም ብሎ ያዳምጣል፡፡

«ሰላም፤ ደህና አደራችሁ?» አለ ይነበብ አጸፋውን፡፡ ይኸ ፊተ መጣጣ ሰው እንዴት በሰሙ ሊጠራው እንደቻለ ገርሞታል፡፡ ከአሁን ቀደም የትም እንዳላየው እርግጠኛ ነው፡፡

«ይቅሬታ! ስቱሲቃይ እንዳደርከ ገቡቶኛል፡፡ ለሙንጠይቅህን ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ከሰጠህ ግን ዛሬውኑ ወደ ቤትህ በመመለስ እከስሃሎሁ» አለው፡፡ ጸጉሩ ሚዶ ነክቶት የሚያውቅ አይመስልም፡፡ ይነበብ ምንም መልስ አልሰጠም፡፡ ይዘውት ወደ ሌላ ክፍል ሄዱ፡፡ ክፍሉ ውስጥ ፋይል የተከመረበት ጠረጴዛ በአራት ወንበሮች ተከቦ መሀል ላይ ይታያል፡፡ የቆሻሻ ማስቀመጫ ቅርጫት ቢኖርም በአግባቡ ጥቅም ላይ አልዋለም፡፡ በየቦታው የወዳደቁ ወረቀቶችና ቆሻሻ ክፍሉን ሞልተውታል፡፡ ክፍሉ በንጽህናና በአያያዝ ጉድለት የተነሳ አይን አይስብም፤ እንደውም ቅፍፍ ይላል፡፡

«ሂድ--ሂድ ቁልፉን ከሀብቶም ተቀበል ቀልጥፍ፡፡ ለሥራ ጉዳይ ልኬዋለሁህና ፎጠን በል ሳያመልጥህ ድረሱበት» አለው ያን አብሮት የነበረውን ሰው፡፡ ሰውየው ሆዱንና መቀመጫውን እያንከባከለ ሮጥ ሮጥ ለማለት ሞከረ፡፡ ቁልፉን ይዞ ሲመለስ ጫን ጫን ይተነፍስ ነበር፡፡ ከይነበብ እጅ ላይ ካቴናው ወለቀ፡፡ እጁን ወደ ፊቱ ወደ ቀድሞ የተፈጥሮ ቦታው ለመመለስ በጣም ተሰቃየ፡፡ የራሱ እጅ አልመስለው እስኪል ድረስ ወደ ፊቱ አልመለስ አለው፡፡

«ቁጭ በል አቶ ይነበብ» አለ ያው ፊተ መጣጣ ሰው፡፡ ቢያዘልቅለት ትህትናው ለጉድ ነው፡፡ ይነበብ ፊቱ ካለ ወንበር ላይ ተቀመጠ፡፡

«ቱስማሎህ አቶ ይነበብ! ደርግ ኢሰፓን ያንበረከክነው ለስንት ታጋዮቻችንስ ሰውተን ነው፡፡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ንጸነትና ዴሞክራሲ ያጎናጸፍነው ስንቱ ታጋዮቻችን ደማቸ አፍሰው አጥንታቸ ከስክሰው በከፈሉት ምስዋዕትነት ነው፡፡ ለስንት ተጋዳላይ ደም የፈሰሰለት ዴሞክራሲና ንጸነትስ ነፉጠኞች እንደ ገና ሲነጥቁት አሰፍስፈዋል፡፡ እኛ ራሳችን በሰጠነውን የመናገርና የመጻፍ ንጸነት እኛኑ መልሳቹህ ስትኮንኑ ትገኛላቹህ፡፡ ነፉጠኞችና አንዳንድ የበሰበሱ ሙሁር ነን ባዮች ጸጥታ ለማደፍረስና የእርስ በርስ ቡጥቡጥ ለማስነሳት እየጧሩ መሆኑ ደርሰንበታል፡፡ በተለይ መእሕድና ኢመማ የሚሏቸው ድርጅቶች ለዚህ ዓይነተኛ መገለጫዎች ናቸው» አለና ትኩር ብሎ ተመለከተው፡፡

ይነበብ ዝም ብሎ ያዳምጣል፡፡ ብዙ ተናገረ፡፡ ሰለ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊው የኢሕአዴግ መንግሥት የተዋጣለት መልካም አስተዳደር ብዙ-- በጣም ብዙ ለፈለፈ፡፡ መጨረሻ ላይ ይነበብ የታፈነበት ዋና ነጥብ ተነገረው፡፡ ከእንጋፋው ኢመማ ዋና ጸሐፊ ጋር በመሆን ጸጥታ ለማደፍረስ፣ አገር ለመናድና በኃይል መንግሥት ለመገልበጥ መደራጀታቸውን መንግሥት የደረሰበት መሆኑን ገለጸለት፡፡ ከመእሕድ ጋር ውስጥ ለውስጥ በትብብር እየሰሩ መሆኑ መታወቁን ሁሉ ነገረው፡፡ ሌሎች ሌሎች ወንጀሎችም ተዘረዘሩለት፡፡ ከዚህ ገለጻና ማስፈራሪያ በኋላ ለሚቀርቡለት ሦስት ጥያቄዎች ተፈላጊውን መልስ ከሰጠ አሁኑኑ ወደ ቤቱ ሄዶ ከቤተሰቡ ጋር እንደሚቀላቀል ተበሰረለት፡፡





1. ድርጅታቸው በውጭና በአገር ውስጥ ስንት አባላት እንዳሉትና የስም ዝርዝራቸውን እንዲሰጥ፣

2. ድርጅታቸው በተለይ ከኢትዮጵያ መምህራን ማህበር (ኢመማ)ና ከመእሕድ ጋር ያለውን ትብብርና ግንኙነት እንዲያብራራ፡፡ በተለይ የመእሕድ ፕሬዝዳንትና የኢመማ ዋና ጸሐፊ ጋር ያላቸውን ሚና እንዲያጋልጥ፤

3. በኢትዮጵያ ውስጥ ነፍጥ አንስተው የኢህአዴግን መንግሥት በኃይል ለመገልበጥ ካሴሩ ድርጅቶች ከነማን ጋር በትብብር ሊሠሩ እንዳሰቡ በዝርዝር የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት ተገለጸለት፡፡ መንግሥት ለእነዚህ ሦስት ጥያቄዎች ቀጥተኛ መልስ ይጠብቃል፡፡ ትክክለኛውን መረጃ ለመስጠት ትብብሩን ካሳየ ነገሩ ሁሉ ቀላል እንደሚሆንለት ተነገረው፡፡ ያን የማያደርግ ሆኖ ከተገኘ ግን አይቀጡ ቅጣት ይጠብቀዋል፡፡ የተሰጠውን እድል ካልጠጠቀመበት እስከወዲያኛው ቤተሰብ ብሎ ነገር አያየውም፡፡ ቀጭኑኑና ፊተ መጣጣው ሰው መጀመርያ ላይ ያሳይ የነበረው ትህትናና ሀዘኔታ እየጠፋ ዛቻና ማስፈራራት ተከተለ፡፡

«በመሰረቱ እናንተ በሕቡዕ ተደራጀ ለለምትሉት ድርጅት እኔ የማውቀው ነገር የለም፡፡ እናንተ የምታውቁት ነገር ካለና ማስረጃ ካላችሁ በአገሪቱ ሕግና ደንብ መሰረት በፍርድ ቤት ልጠየቅበት ይገባኛል፡፡ በማስረጃ ተደግፎ በምስክር ከተረጋገጠብኝ ተገቢውን ቅጣት ማግትኘት ይኖርብኛል፡፡ የጠቀሳችኋቸው ሰዎችም ሆኑ ድርጅቶች እንዲሁ ፀጥታ ለማደፍረስ-- በኃይል -መንግሥት ለመገልበጥና አገር ለመናድ ከተነሱ ወንጀል ነው፡፡ ለዚህ ተግባራቸው መረጃ ካላችሁ አሁንም ጉዳዩን ፍርድ ቤት አቅርቦ አስፈላጊውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል፡፡ አገሪቱ የምትተዳደረው በሕግ ነው ከተባለ ሁላችንም ሕግ ይዳኘን፡፡ ትናንት አምባገነኑ የደርግ መንግሥት ሲያደርግ እንደ ነበረው ወንጀል ሲሰራ እጅ ከፍንጅ ያልተያዘን ሰው መንገድ ላይ አፍኖ ይዞ ማንገላታት ግን ተገቢ አይደለም፡፡ አምባገነኑና አፋኙን የደርግ ኢሰፓን መንግሥት ጥሎ በትግል ከመጣና በትግል ከተመሰረተ መንግሥት ይህ የሚጠበቅ አይመስለኝም፡፡ ታድያ ወንጀለኛንና አጥፊን በመቅጣት ግልጋሎት ካልሰጡ የፍትህ ተቋማት ለምን አስፈለጉ?» አለ ይነበብ የመጣው ይምጣ ከሚል ድፍረት፡፡ ቀጭኑ ሰው እንዲያ ሲደነፋ እንዳልነበር ሁሉ እስኪ ጨርስ ድረስ በጽሞና ነበር ያዳመጠው፡፡

«አቶ ይነበብ» አለው በምጸት «አቶ ይነበብ እናንተስ ቡቱሆኑ በአዋጅን ተፈቅዶላቹህ ሳለ ለሙን በግልጽ ተደራጅታቹህ በግልፅ አትታገሉም ነበር? ሕቡዕ ሙን አስገባቹህ? ሕጋዊ ሆነን እንዳንቀርባቹህማ ሕጋዊ መንገድ አልተከተላቹህም፡፡ በድብቅ የጀመራቹህትን ፀረ-ሰላም እንቅስቃሴ በድቡቅ ሞከታተል ነበረብን፡፡ ለዋናውን ደርሰንበታል፡፡ የቀረው ጭፋራው--ጭፋፍራው ነው፡፡ ለአውራውን ሲመታ ጭፋራው መበታተኑ ዶሞ አይቀርም» አለ ያው ቀጭን ሰው፡፡

«ሕግ የሚያስፈልገው ሕገወጥን ለመቅጣት ነው:: የአገሪቱን ሕግና ደንብ ተላልፌ ከሆነ ማስረጃ ይቅረብብኝና ፍርድ ቤት አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጠኝ እያልኩ ነው እኮ» አለ ይነበብ::

«'ጨዎ ለራስህን ቡትል ጣፍጥ ያለዙያ ዱንጋይ ነዎ ብለዎ የትም ይጥሎሃል' ነዎ የምትሉት እይደል እናንተ አማሮች ስትቶሩቱ:: መቼም ለተረትስ እያልቅባቹህም:: እየቀለድኩ እንዳይመስሎህ:: አዲስ አበበን እስከንቆጣጠር ድረሰ ለስንት ታጋዮቻችን ደም ገብረን ነው ለደርግ ኢስፓን መንግሥት ጥለን ሰልጣን ላይ የወጣነው:: ለስንትና ሰንት ተጋዳዮቻችን ሙጃ ሆነው ቀርቶዋል:: ከቶማ እያውደለደላቹ ሙቾታቹህ ስትጠብቁ የኖራቹህ የነፍጠኞች ጥርቅም ሁሉ እርማቹህን አውጡ:: በስንት ተጋድሎ ላገኘነውን ሱልጣን እንዲሁ በዋዛ የምንለቅ መስሏቹህ ከሆነ ገና አላወቃቹህንም ማለት ነው:: ደሙተንና ሞተን ላገኘነውን ሱልጣን ለምንጠቅ ሱትነሱ እጃችን እጣጡፈን የሚንቀመጥ መሰሏቹህ ከሆነ ተሳሰታቹኋል» አለ ሰውየው ተቆጥቶ::

ከእንግዲህ ወዲያ ከዚህ ሰው ጋር አፍ መካፈቱ ምንም ዋጋ እንደ ሌለው ተገንዝበ ዝም አለ ይነበብ:: ለተዘጋጀው ተውኔት ተባባሪ እንደማይሆን ለውስጡ ነግሮ የመጣውን መከራ ሁሉ ለመቀበል ዝግጁ ሆነ::

«ለሕሊና ማደር እንዴት ጥሩ ነው! ሰው የእምላከኑት ባህሪ የሚኖረው በአዕምሮው ያሰበውን ሐሳብ ልበናው እመዛዝኖ ትክከለኛ ፍርድ ለራሱ የሰጠ ጊዜ ነው» አለ በውሰጡ:: እሱ ለራሱ በሰጠው ውሳኔ መንፈሱን ቅልል አለው:: ውስጡ ጥንካሬ ሲያገኝ ተሰማው::

«ሰማእ እታ! ልንገርህ የነፍጠኛ ድርቅና እያዋጣህም:: ቤተሰቦቹህ ለአንድ ሰምን ነው የሚንጫጩት:: ፎቶህ በየእጥሩ፣ በየግንዱና በየግድግዳው ላይ ይለጡፋሉ:: በሬድዮ ያፋልጉኝ ጥሪ ያስተላልፏሉ:: በየጋዜጣውን ላይ ያፋልጉኝ ጩኸታቸውን ያሰማሉ:: ግፋ ቢል በየኢምባሲ ድጅ ይሮጣሉ በቃ! ምን ያምጣሉ!? እንኳ የእንተ የአንድ ቤተሶብ ጩኸት ይቅርና የሕንጻ ኮንስትራክሽን ስራተኞች በቡድን ሆነውስ ለስንት ወር ዝናቡና ጸሐይ እየተፎራረረቀባቾ ሲለለፉ--- የርሀብ አድማ ሲያደርጉ ሙን ፎጠሩ? ለኛስ እምስት ሳንቲም ሸግር እልፎጠሩብንም:: ራሳቸውና ለቤተሰባቸው ጎዱ-- በበሽታ ማቀቁ:: ለሞትም ተዳረጉ:: በቃ! የሞተው ሞቶ--የታመመው ታሞ--- እንግልትና ስቃይ እትርፎው ሲደከማቾ ለቤታቸውን ገቡ:: የባንክ ሰራተኞችስ ቢሆኑ ሙን እመጡ? ቶንጫጩ-ቶወራጩ ---ተጋጋጡ---ተሞላለጡ እርፈው ተቀሞጡ:: እንተ አንድ ሰውስ ከንቱ ሙንም ለውጥ ላታመጣ ይልቅ ለቀረበልህን መልካም እጋጣሚ ተጦቁመህ ከቤተሰቦቹህ ጋር ብቱቀላቀል ይሻልሃል» አለው::





ምንም ዓይነት ማበበያ ቢጠቀምም--- ምንም ዓይነት ማስፈራሪያ ቢያደርግም-- ቤተሰቡ ላይ ሊደርስ የሚችለውን የስነ ልቦናና የአካል ስቃይ እየገለጸ ቢፈታተነውም--ይነበብ በአቋሙ ጸና::

******

ትሩፋት ይነበብ ጋር እንዲያ ተነጋግረው ከሄደ በኋላ ይህ ነው ብላ ምክንያቱን ያላወቀችው ነገር አዕምሮዋን ደርሶ ብጥብጥ እያደረገው ተቸግራለች:: የነካትን አታውቅም:: ሰውነቷን ርብሽብሽ የሚያደርግ ስሜት እየተፈታተናት ነው:: በእንቅልፍ እንዲያልፍላት ጋደም ብትልም ሊወስዳት አልቻለም:: ተመልሳ ፍዝዝ ብላ ቁጭ አለች:: ረስታው ነው እንጂ የነረቤት ለቅሶም ነበረባት:: ትዝ ሲላት ነጠላዋን እንጠልጥላ ወደ ዚያው አመራች::

ከለቅሶ ቤት ስትመለስ ልጆቹ ተኝተዋል:: ሰራተኛዋ ብቻዋን ቁጭ ብላ ቴሌቪዥን ትመለከታለች:: ይነበብ እቤት አልገባም:: ሰዓቷን ተመለከተች:: ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ተኩል ሆኗል:: «እዚህ ነኝ» ሳይላት እስከዚህ ሰዓት ድረስ እያመሽም:: ልቧን ጭንቅ አላት:: አልጋዋ ላይ ጋደም ብላ እንደ ሁልጊዜው መጽሐፍ ለማንበብ ሞከረች:: አንድ መስመር እንኳ ሐሳቧን ሰብሰብ አድርጋ ማንበብ አልቻለችም:: ሰራተኛዋ ቴሌቪዥኑን አጥፍታ ተኝታለች:: ቴሌቪዥኑን ከፍታ የሆነ ፊልም ለማየት ሞከረች:: መንፈሷ ዘና ሊል አልቻለም:: ቴሌቪዥኑን ዘግታ ወደ መኝታ ቤት ሄዳ እንደገና ጋደም አለች:: ራሷ የዞረ መሰላትና ተነሰታ ቁጭ አለች:: ሰዓቷን ተመለከተች:: ምሽቱ እየገፋ ነው:: ይነበብ ብቅ አላለም:: የትሩፋት ልብ እየተነሳች ትወድቅ ጀመር:: በዐይኗ እንቅልፍ ሳይዞር እንዲሁ ቁጭ ብድግ እንዳለች ምሽቱ አልፎ ሌሊቱ ተጋመሰ:: ጭንቅ--ጥብብ ብላ በሐሳብ ስትብከነከን ይዞላት የሚመጣውን ነገር ባታውቅም ሌሊቱ አልፎ ቀኑ ተተካ::

ጧት ምኒልክና ሀና ወደ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ አደረገች:: በአጋጣሚ ቴዎድሮስ ከጅማ ዩንቨርስቲ ለእረፍት መጥቶ እቤት ነው ያለው:: ለራሔል ሁኔታውን በስልክ ስትነግራት ለእለቃዋ እንኳን አላሳወቀችም:: በርሳዋን አንጠልጠላ ከቢሮ ወጣች:: ከፒያሳ ቀበና ያለው መንገድ ከሁልጊዜው የራቀ ታከሲውም የተጎተተ መሰላት:: የስልኩን መልዕከት እንኳ በእግባቡ የተረዳችው አልመሰላትም:: በጭንቀት እንደተዋጠች እቤት ስትደርስ ያገኟቻት ያች ጠንካራዋንና ጽኑዋን ትሩፋትን አልነበረም:: በአካልም በመንፈስም የደቀቀችና ድከም ያለች ትሩፋትን ነበር:: ድንገት በደረሰው ሁኔታ ከተነጋገሩ በኋላ ያገኙት ውጤት ባይኖርም በእነሱ አቅም ማድረግ የሚገባቸውን ሁሉ አድርገዋል:: የይነበብን ዱካ ግን ማግኘት ሳይችሉ ቀሩ::

ይነበብ ከተሰወረ ከተወሰኑ ቀኖች በኋላ ትሩፋት ወደ መምህራን ማሕበር ጽህፈት ቤት ስልክ ደወለች:: ስልኩን ያነሳችው ሴት ነበረች:: የኢመማውን ዋና ጸሐፊ እንድታገናኛት

ጠየቀች ትሩፋት፡፡ በተረበሸና በሚንቀጠቀጥ ድምጿ የሰጠቻት መልሰ ግን ትሩፋን ዐይኗን እፍጦ ባላቻበት ድር--ቅ እንድትል አደረጋት፡፡ የሰልኩ እጀታ እጇ ላይ ተንሸራቶ መሬት ላይ ሲወድቅ እንኳ አልሰማችውም፡፡

«አልሰሙም እንዴ! ዛሬ ጧት ከቤታቸው ወደ ሥራቸው ሲመጡ ባልታወቁ ኃይሎች ተገደሉ እኮ! አስከሬናቸው ሚኒሊክ ሆስፒታል ተወስዷል፡፡ ጽህፈት ቤቱ በወታደር ተከበ እኛም ሰራተኞቹ እንዳንወጣ እንዳንገባ ታግተናል» ነበር ያሰቻት፡፡ መልእከቱ አንድ ያለፈ ነገር ብልጭ አደረገባት፡፡ አንድ ቀን ሁለቱ እዚችው ቤቷ ውሰጥ ሆነው በቁም ነገር ይነጋገሩ እንደ ነበር እስታወሰች፡፡ አንድ የሆነ ሰነድ ላይ አጥብቀው ይከራከሩና ይወያዩ እንደ ነበር ወሰል ብሎ ታያት፡፡ እልተተራጠረችም የሆነ የከፋ ችግር እንደ ተፈጠረ እርግጠኛ ናት ትሩፋት፡፡

ይነበብ ከአንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ዋና ጸሐፊ ጋር ከእድገት በሕብረት የእውቀትና የሥራ ዘመቻ ጀምሮ ጥብቅ ግንኙነት እንዳላቸው ታውቃለች፡፡ ይነበብ ሚያዚያ 24 ቀን 1989 ዓ.ም ከቤቱ እንደ ወጣ አልተመለሰም፡፡ ሚያዚያ 30 ቀን 1989ዓ.ም ጓደኛው የአንጋፋው የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ዋና ጸሐፊ ባልታወቁ ኃይሎች ተገደለ፡፡ ግጥምጥሞሹ የአጋጣሚ ጉዳይ ሊሆን አይችልም፡፡ ፍርሀት ዋጣት፡፡ ሰውነቷ ሁሉ ተንቀጠቀጠ--- ልቧ ከዳቻት--- ራሷ ዞረ--- ሶፋዉ ላይ በግንባሯ ድፍት አለች፡፡ የኢመማው ዋና ጸሐፊ መገደል እንገበገባት፡፡ ማልቀስ ፈለገች፡፡ እንባዋ ደርቋል፡፡ ራሔልም ከትሩፋት አልተሻለችም፡፡ የስልኩን ዝርዝር ጉዳይ ባትሰማውም ደግ ወሬ እንዳልሆነ ከፊቷ ላይ እንብባለች፡፡ ግራ ገብቷት ፍዝዝ ድንዝዝ ብላ ቆመች፡፡

«መንግሥትና ሕግ እለባት በምትባል አገር ውስጥ በአደባባይ ሰው መግደል? በሰላም ከቤቱ የወጣን ሰው አፍኖ መሰወር? ታሪከ ራሷን እየደገመች ይሆን?» እለች ትሩፋት በውስጧ፡፡ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ጊዜ ጠፍተው የቀሩት አባቷ-- የግር እሳት ሆነውባት እንደሚኖሩ ስትተርከላት የነበረችው ሰሳማዊትና ፊቷ ላይ ይታይ የነበረው የፀፀት ስሜት ዛሬ ይበልጥ ጎልቶ ታያት፡፡ ንጉሡ ለሰልጣናቸው እስጊ የሚመስሏቸውን ሰዎች አሳፍነው ደብዛቸው እንዲጠፋ ያስደርጉ ነበር፡፡ ወታደራዊው የደርግ መንግሥት ለስልጣኑ ያሰጉኛል የሚላቸውን ሰዎች ዕድሜ፣ ፆታ፣ ቋንቋ፣ ዘር፣ ሀይማኖት ሳይለይ በጅምላ ገድሎ በጅምላ አፈር መልሶባቸዋል፡፡ በጭካኔ ግንባር ግንባራቸውን በጥይት በርቅሶ አደባባይ ላይ ዘርግቷቸዋል፡፡

እንደ በዓሉ ግርማ የመመሳሰሉትን ደግሞ አፍኖ ደብዛቸውን ሰውሯል፡፡ የስቃይን ዓይነት በሕዝብ ላይ ለማብዛት ካልሆነ በስተቀር እሁን ማ ይሙት! ደርግ ደግሞ የፍየል ወጠጤ እያሰፎከረ በግልጽ ያሻውን ሲገደል ማንን ይፈራ ነበር? እግዜሩንም ሕዝቡንም የናቀ መንግሥት ነበር፡፡ «የሕዝብ ብሶት ከወለደው ከግንቦት 20» ድል በኋላም ይኸው በጠራራ ፀሐይ ሰው ይገደላል፡፡ ብዙ ሰዎች የደረሱበት ሳይታወቅ ተሰውረው ቀርተዋል፡፡





በቅርብ ጊዜ እንኳን በወጡበት ደብዛቸው ጠፍቶ የቀረውን እነዚያን ሁለት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ታውቃለች ትሩፋት፡፡ ዛሬ የእሷን ቤት አንኳኩቷል፡፡ ነገ ተረኛው ማን ሊሆን እንደሚችል ከራሳቸው ከገዥዎች በስተቀር ማንም እያውቅም፡፡ ታሪከ በኢትዮጵያ ራሱን ስመደጋገሙ ከዚህ በላይ ምን ማስረጃ ይኖራል? ትሩፋት የምታደርገው ነገር ጠፋት፡፡ መጨረሻ ላይ ነበር የመጨረሻ እድሏን ለመሞከር በተለይ ይመለከታቸዋል ለምትላቸው መስሪያ ቤቶች ሁሉ የአቤቱታ ደብዳቤዎቿን ያስገባች፡፡

ለጠቅላይ ሚኒስትሩ በግል

ለጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ

ለፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን

ለክልል ፖሊስ ኮሚሽን

ለፌደራል ፍትህ ሚኒስትር

ለምክር ቤት

ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ

ለአምነስቲ፡፡

ሁሉም ደብዳቤዎቿን ተቀብለዋታል፡፡ ኢሰመጉ በወቅቱ ባወጣው መጽሔቱ ላይ ከቤቱ ወጥቶ የተሰወረ መሆኑን ፎቶግራፉን አሰደግፎ ከማውጣቱ በስተቀር ሌሎቹ ተቋሞች ተከፍቶ--- ተጨንቆ--- አዝኖ--- ቆስሎ ደም ለሚያነባ ቤተሰብ ማጽናኛ የሚሆን እንዳችም መልስ አልሰጡም፡፡

******

ትሩፋት መቀነቷን ጠበቅ አድርጋ ቤተሰብ መምራቱን ዛሬም እንደ ገና በብቸኝነት ተያይዛዋለች፡፡ በደርግ ውድቀት ማግስት እንደ ገና ለዳግም ብቸኝነት ተዳርጋለች፡፡ በዘመነ ደርግ ጊዜ የወደቀበትን አግኝታው ነበር፡፡ ስንቅና ልብስ ማቀበል ችላ ነበር፡፡ የቀይ ሽብር ሰለባ ካልሆነ አንድ ቀን ከስር ተፈቶ እንደሚገናኙ እርግጠኛ ነበረች፡፡ ዛሬ ግን የት እንደ ገባ እንኳ አታውቅም፡፡ የሚንሰፈሰፍላቸው ልጆቹ እንደ ሁልጊዜው ከሄደበት ይመጣል ብለው ደጅ---ደጁን እያዩ ብዙ ቀን ጠብቀውታል፡፡ እሱ ግን በወጣበት ቀረ፡፡ ዛሬ አባታቸው በሕይወት ይኑር አይኑር የሚያውቁት አንዳች ነገር የለም፡፡ ልክ በዘመነ ኃይለስላሴ እንደ ተሰወሩት የሰላማዊት አባት--- በደርግ ጊዜ የውሃ ሽታ ሆኖ እንደ ቀረው

በእሱ ግርማ--- የትሩፋት ልጆች የአባታቸው መሰወር የእግር እሳት ሆኖ እያንገበገባቸው ይገኛሉ:: ባላጠፉት ጥፋት በአባት ናፍቆት እንዲቀጡ በጨካኞች ተፈርዶባቸዋል:: ትሩፋት ልጆቿን አልቅሳ ማስለቀስ አልፈለገችም:: ይልቁንስ እውነታውን ማወቅ ይገባቸዋል::

«ቴዎድሮስ፣ ምኒልክ፣ ሀና ኑ እዚህ ተቀመጡ እፈልጋችኋለሁ» አለች። አባታቸው ከቤቱ ወጥቶ ከተሰወረ ከጥቂት ቀናት በኋላ:: ያላትን ኃይል ሁሉ አሰባሰባ ልክ መርዶ እንደሚያረዳ ሰው እየተጨነቀች ሁኔታውን ለመግለጽ ሞከረች:: ቢቸግራት ነው እንጂ ማምሸት እንኳ የማያውቁበት አባታቸው ጭራሹኑ እንደ ወጣ ሲቀር አንድ ችግር እንደ ተፈጠረ ገብቷቸዋል:: ያላወቁ መስለው ዝም ያሉት እናታቸውን ላለማስጨነቅ ነበር::

«ልጆቼ! ዛሬ ከበድ ያለ ቁምነገር እንወያያለን» ምን ብላ መጀመር እንዳለባት ግራ ገባት:: ትንፋሿን ካስተካከለች በኋላ እንደ ምንም ተደፋፍራ ንግግሯን ቀጠለች:: «አባታችሁ ከምንም በላይ እንደሚወዳችሁ ታውቃላችሁ አይደል?» አለች መስማማታቸውን በአንገት ንቅናቄ ብቻ ገለጹ:: «አርጎት የማያውቀውን ባልተለመደ ሁኔታ ከቤቱ እንደ ወጣ ይኸው እስከ አሁን አልተመለሰም:: ምን እንደ ገጠመው የታወቀ ነገር የለም» ጉሮሮዋን የሆነ ነገር እን--ቅ! ያደረጋት መሰላት:: ጸጥ አለች:: ልጆቹ በጽሞና ዐይን ዐይኗን ይመለከታሉ:: በፀጥታ እያዳመጧት ነው:: አንጋጣ ጣራ ጣራውን ተመለከተች:: እንባዋ ከልጆቿ ፊት እንዳይወርድ ፈራች:: ሁለት ሦስት ጊዜ ምራቋን ዋጠች:: «እህ--ህህ» ብላ ጉሮሮዋን አጸዳች:: እንደ ምንም ራሷን አረጋግታ አሁንም ንግግሯን ቀጠለች::

«እኔንና እናንተን ከድቶ እንዳልሆነ ግን ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ::» ልትነግራቸው ያሰበችው ሐሳብ ሁሉ ተምታታባት:: እንግዲያው ብዙ አውጥታ አውርዳ ተዘጋጅታበት ነበር::

«አባታችሁ ሁሌም ሲመኘውና ሲለፋላችሁ የነበረው እናንተ ጎበዝ ተማሪዎች እንድትሆኑ ነው:: ሕይወታችሁ የተሳካ እንዲሆን ከምንም በላይ ሲጥር ኖሯል:: ለአገርና ለወገን የምትጠቅሙ ታላላቅ ሰዎች እንድትሆኑ ከፍተኛ ምኞት ነበረው:: አባታችሁ በሕይወት ኖረም አልኖረም ጥረቱ ግብ እንዲመታ አድርጉ::» አሁን ግን እንባዋን መግታት አልቻለችም:: ሦስቱም ልጆቿ አንገቷ ላይ ተጠመጠሙ:: አምቀው ይዘውት የነበረ እንባቸው ገንፍሎ እንዳሻው መውረድ ጀመረ:: ተቃቅፈው ለረጅም ሰዓት አነቡ:: የውስጥ ቁስላቸውን--- የውስጥ ሀዘናቸውን--- የውስጥ ብሶታቸውን በእንባ አጥበው ትንሽ ትንፋሽ አገኙ:: ከጥቂት ጸጥታ በኋላ ትሩፋት ንግግሯን ቀጠለች::

«'ልጆቻችን ያደገች--የበለጸገች-- ዳር ድንበሯ የተከበረች-- ትክክለኛ ፍትህ የሚገኝባት-- ዲሞክራሲና ነጻነት የሰፈነባት-- ሰላማዊት አገር ከኛ ከወላጆቻችው መረከብ ይኖርባቸዋል' የሚል ጽኑ አቋም ነበረው:: ለዚሁ ሲል ከኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ ሲታገል





ኖሯል:: ሕይወቱን በሙሉ ማለት ይቻላል ሲታሰር ሲፈታ ብዙ መስዋዕትነት ከፍሏል:: የታሰበው ዲሞክራሲ--ነፃነትና ፍትህ--እድገትና ብልፅግና ግን ገና እስከ አሁን አልመጣም:: ዛሬም አዲስ ትግል በአዲስ ምዕራፍ መከፈት አለበት ብሎ አጥብቆ ያስብ ነበር:: ይኸ የሱ ሐሳብ ደግሞ በመንግሥት የሚደገፍ አይደለም:: ከቤቱ ወጥቶ እንዲሰወር ያደረገው እንደ ገና ለትግል የመነሳሳቱ ሐሳብ ሊሆን ይችላል ብዬ እሰባለሁ:: ከአንዱ እሰር ቤት ዘግተውበት ከሆነ አመኑኝ አፈላልጌ አገኘዋለሁ:: ካልሆነም ሁሉንም ነገር ጊዜ ያወጣዋል:: ሁሉንም ነገር ጊዜ ይፈታዋል:: ትክክለኛውን የአባታችሁን ታሪክ በጊዜ ውስጥ ታገኙታላችሁ:: እስከ ዚያው ግን እናንተ ጎበዝና ጠንካራ ልጆች መሆን ይጠበቅባችኋል:: አባታችሁ ሞተ የሚባለው እናንተ ተልፋሰፍላችሁ የትም ወድቃችሁ የቀራችሁ ጊዜ ነው:: ጠንክራችሁና በርትታችሁ ትምህርታችሁን ተምራችሁ ታላላቅ ሰዎች ከደረሱበት ደረጃ ልትደርሱ ቃል ግቡልኝ» አለቻቸው:: ጉልበቷን በመምታትና ጉንጯን በመሳም ቃል ገቡ:: ደግነቱ እድገዋል:: ሀና እንኳን ስምንተኛ ክፍል ደርሳለች::

ትሩፋት የአሁኑን ብቸኝነቷን በጭራሽ ያልጠበቀችው ነው:: ወታደራዊውን የደርግ መንግሥት ለመጣል በተደረገው ትግል ውስጥ የሕይወት መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ነበረች:: ይነበብ ከአራት ዓመት በላይ ታስሮ ሰትንገላታ የትግሉ አንድ አካል እንደ ሆነ አድርጋ ነበር የወሰደችው:: ቤተሰቡን በብቸኝነት ስታስተዳድር እጅ አጥሯታል:: የሞራል እጥረት ግን አልደረሰባትም ነበር:: በድርጅቷ ላይ በነበራት ጽኑ ዓላማ ኩራት እንጂ ፍርሀት አላደረባትም ነበር:: መሽቶ በነጋ ቁጥር ለሕዝባዊ መንግሥት መቋቋም የቻለችውን ሁሉ በወኔ ፈጽማለች:: የአሁኑ ሁኔታ ያኔ አጋጥሟት ቢሆን ኖሮ በጸጋ ለመቀበል የበቃ ዝግጁነትና ጥንካሬ ነበራት::

ያ ሁሉ መስዋዕትነት የተከፈለለት ትግል ግቡን ስቶ እንደጉም በነነ:: የደርግ መንግሥት ባልተጠበቀ ሁኔታ ወደቀ:: ይባስ ደግሞ አገር በጎጥ ታጋዮች እጅ ወደቀች:: ውስጥ አንጀቷ እየቆሰለም ቢሆን ፊቷን ወደ ግል ሕይወቷ ባዞረችበት በዚህ ሰዓት ትዳሯ ለዳግም ችግር ይጋለጣል ብላ አልጠበቀችም:: ለዳግም ብቸኝነት እዳረጋለሁ ብላ አላሰበችውም::

የምታፈቅረው ባለቤቷ በአፋኞች እጅ ወድቆ ደብዛዉ ይጠፋል የሚል ቅንጣት ታክል ጥርጣሬ አላደረባትም:: ለዚያውም ስንቅ ማቀበል፣ መጠየቅና ማየት በማትችልበት በዚህ ሁኔታ:: ብቸኝነት--- ንዴት--- ሽንፈት እኝከው-- አላምጠው-- ሰብልበው--- አቃጥለው እንዳይጨርሷት መለሳለሻዋ የቤተሰብ ኃላፊትና እባት የሌላቸው ልጆች እናት መሆኗ ብቻ ነበር:: ጥርሷን ነክሳ ልጆቿን ማስተማር ግድ ይላታል:: ሌላው ቢቀር ይነበብ ለልጆቹ ይጥር የነበረው ሁሉ ግቡን መምታት ይኖርበታል:: ይህ እንዲሆን ደግሞ የግድ የእሷን ያላሰለሰ ብርታትና ጥንካሬ ይጠይቃል:: ልጆቿን አስተምራ ለወግ ማዕረግ ማብቃት:: አዎ! ከአልተሳካው ሰፊ አገራዊና ሕዝባዊ ዓላማ ባሻገር እንደ ሬት እየመረራትም ቢሆን ወደ ጠባቡ ቤተሰቧ ፊቷን መመለስ እንዳለባት ወሰነች::

******

ይነበብ ከተዘጋበት ጨለማ ክፍል ውስጥ ሆኖ ብዙ ያሰባል፡፡ ይጨነቃል፡፡ እንዳይሞት እንዳይድን በቀን አንድ ዳቦ እንደ ውሻ ይወረወርለታል፡፡ በየጊዜው እየመጡ ለምርመራ ይጠሩታል፡፡ ጥያቄያቸውም አልተለወጡም አነዚያው ሦስት ጥያቄዎች ብቻ ናቸው፡፡ የእሱም መልሰ አንድ ነው፡፡ «ምንም ወንጀል አልሰራሁም፡፡ ከምትሏቸው ሰዎችና ድርጅቶች ጋር ምንም ዓይነት ሕገወጥ ግንኙነት አላደረኩም» የሚል፡፡ ፍርድ ቤት እንዲቀርብና በቤተሰብ እንዲጎበኝ ደጋግሞ ጠይቋል፡፡ ሰሚ ግን አላገኘም፡፡ ለአንድ ቀን እንኳ ትሩፋትን ቢያገኛት ይመኛል፡፡ እሱ ራሱ አምኖበት ለጀመረው ጥንስስ ሁሉንም መከራና ስቃይ ለመቀበል ዝግጁ ሆኗል፡፡ ትሩፋት ግን በማታውቀው ጉዳይ ለዳግም ብቸኝነት መዳረጓን ሲያስበው ልቡ ይደማል፡፡ አግኝቷት አይዞሽ በርቺ እንዲላት ይመኛል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ አንድ የሚያስጠነቅቃት ነገር ነበረው፡፡

ድንገት ቤቱ ቢፈተሽ ቦርሳው ውስጥ ያስቀመጠው ሰነድ ብዙ ጉዳይ ይዟል፡፡ ሊመሰርቱት ስለ አሰቡት ድርጅት ብዙ ሚሥጢራዊ ነገር አለው፡፡ ለጥንቃቄ ሲባል በሚሥጢርና በኮድ የተጻፈ ቢሆንም ኮዱን በባለ ሙያ ሊያስፈቱት ይችሉ ይሆናል ብሎ ሰግቷል፡፡ ትሩፋትንም በማታውቀው ነገር ይንገላቷት እንደሆን ብሎ ይጨነቃል፡፡ ይነበብ ቀንኑንና ሌሊቱን በማይለይባት በዚያች ጠባብ ጨለማ ክፍል ውስጥ ሆኖ የማያነሳ የማይጥለው ሐሳብ የለውም፡፡ ሲጨነቅ ውሎ ሲጨነቅ ያድራል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ውጥኑ ግቡን ባለመምታቱ ይናደዳል፡፡ ይቆጫል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሰልችት የሚለው ነገር ቢኖር በየጊዜው ለምርመራ መጠራቱ ነበር፡፡ አንድ ቀን እንዲሁ ተጠርቶ ሲሄድ ያን አሰልች የተለመደ ጥያቄያቸውን እያሰበ ነበር፡፡ ከምርመራ ክፍሉ ሲገባ የሁልጊዜው ያ ፊተ መጣጣ መርማሪ አልነበረም፡፡ የጠበቀው ሌላ አዲስ ሰው ነበር፡፡

«ሳጅን ቁምላቸው አባላለሁ» አለው መርማሪው እጁን ለሰላምታ እየዘረጋና የሞቀ ፈገግታ እየለገሰው፡፡ ይነበብ ስሙን ነግሮ በአክብሮት ጨበጠው፡፡ ሳጅን ቁምላቸው የሆነ ፋይል እያገላበጠ ተራ ወሬ ሲወራው ቆየ፡፡ ከቆይታ በኋላ ነበር ወደ መጣበት ዋና ጉዳይ የገባው፡፡

«አቶ ይነበብ እንደ ሰማሁትና እንዳረጋገጥሁት ከሆነ ባለ ትዳርና የሦስት የልጆች አባት ነህ፡፡ በአምባገነኑ የደርግ ኢሰፓ መንግሥት ጊዜ አንተም ሆነ ቤተሰብህ የቀይ ሽብር ሰለባ ባትሆኑም ለእስር ተዳርጋችሁ በእጅጉ የተንገላታችሁና የተጎዳችሁ መሆናችሁን ደርሸበታለሁ፡፡ ስላንተና ቤተሰብህ ብዙ መረጃዎች እጃችን ላይ ገብቷል» አለ ፋይሉን እያገላበጠ፡፡

ይነበብ «ምን አዲስ ማስረጃ አገኙ ይሆን? እቤት ሄደው ፍተሻ አካሂደው ይሆን? ትሩፌን አሰቃይተዋት ይሆን» እያለ ውሰጥ ውስጡን በጭንቀት ተብሰለሰለ፡፡ እዚያ ብሪፍኬዝ





ውስጥ ያስቀመጠውን ሰነድ እያሰበ፡፡ ትሩፋት ግን በዚያች ጭንቅ ጥቁር ሌሊት በሐሳብና በጭንቀት ለትባዝን ስታድር ቦርሳው ውሰጥ ያገኘችውን በኮድ የተጻፈ ሰነድ በዋዛ አላየችም፡፡ ደጋግማ መርምራዋለች፡፡ ኮዱን ፈታ ሚሥጢሩን ባትረዳውም አንድ የሆነ ቁምነገር እንዳያዘ ገብቷቷል፡፡ ቤቷ ውስጥ ድንገት ፍተሻ ቢካሄድ ይህ በኮድ የተጻፈ ሰነድ በፍጹም እጃቸው ውስጥ መግባት የለበትም፡፡ ጊዜ አላባከነችም ወድያው ነበር እንዳይገኝ አድርጋ ያጠፋችው፡፡ ይህንን የትሩፋት ጥንቃቄ ይነበብ እንዴት ይወቅና ከጭንቀቱ ይገላገል?

«ያ በግፍ ያስቃያችሁ መንግሥት በሕዝብ አመጽ ተደምስሶ ኢሕአደግ ስልጣን ከያዘ በኋላ ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም የሕዝብ መብት ተከብሯል፡፡ አገሪቱም በተሻለ የእድገት ጎዳና ላይ ትገኛለች፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ሁሉም ነገር መቶ በመቶ ትክክል እየተከናወነ ነው ብለን እኛም አናምንም፡፡ ሕዝብ ተጠቃሚ እንዲሆንና አገር እንድታድግ የመምህራንን እርዳታ እንፈልጋለን፡፡ አንተን የመሰሉ ጠንካራ አገር ወዳድ ሰዎች ውስጣችን ገብተው ሊያግዙን ይገባል፡፡ እስከ ዛሬ ባላመግባባትና በጠላትነት ተጉዘን አይተነዋል፡፡ የተገኘ የአገርም ሆነ የሕዝብ ጥቅም የለም፡፡ የሚሻለው አብሮ ተባብሮ መስራቱ ነው፡፡» አለና ፊቱን የሚያነብ ይመስል አተኩሮ ተመለከተው፡፡ ይነበብ ጸጥ ብሎ ያዳምጣል፡፡ ሳጅን ቁምላቸው ቀጠለ ንግግሩን

«አንተም በዚህ እድሜህ ከቤተሰብና ከልጆችህ ጋር መለያየት ያለብህ አይመስለኝም፡፡ እስካሁን በዚህ ሁኔታ የተሰቃየኸው ይበቃሀል ስለዚህ በመግባባት እንድንሰራ ነው እኔ የመጣሁት፡፡ እርግጠኛ ነኝ ግንኙነታችን በመልካም ሁኔታ ይጠናቀቃል» አለ ሳጅን ቁምላቸው ሙሉ ፈገግታ እየለገሰው፡፡

«እኔም ሁሉም ነገር ሰላም እንዲሆን ነው ፍላጎቴ» አለ ይነበብ ረጋ ብሎና አዲሱን ስምምነት ለማዳመጥ ራሱን እያዘጋጀ፡፡

«አቶ ይነበብ እኔ የመጣሁት ከፖሊስ መርመራ ክፍል ታዝዤ ነው፡፡ ይኸ የምታየው ፋይል የአንተን ሕገ-ወጥነት የሚገልጽ ማስረጃ የያዘ ሰነድ ነው፡፡ መንግሥትን በኃይል ለመናድና የአገር ሰላም ለማደፍረስ ከተደራጁ ቡድኖች ጋር አብረህ መስራትህን የሚያረጋግጡ ከበቂ በላይ ማስርጃዎችን አግኝተናል» ብሎ ፋይሉን አገላበጠው፡፡

«በአስካሁኑ አያያዝህ አዝናለሁ፡፡ የተገኘብህን ማስረጃ አምነህ የተጠየቅሃቸውን ጥያቄዎች በአግባቡ ከመለስክና ምስክርነትህን ከሰጠህ እንዲሁም ህገወጥ ሥራ ስትሰራ መያዝህን አምነህ በአደባባይ ይቅርታ ከጠየቅህ የኢህአዴግ መንግሥት መሀሪ ነው ዛሬውኑ ተለቀህ ከቤተሰብህ ጋር ትቀላቀላለህ፡፡ አትሞኝ አቶ ይነበብ በሕቡዕ ተደራጅታችሁ መንቀሳቀስ መጀመራችሁን የደረስንበት እኮ የራሳችሁ አባል የሆነ ሰው ባደረሰን ጥቆማ መሰረት ነው፡፡ ያለዚያማ እንዴት ማወቅ እንችል ነበር? ስለዚህ አንተ ለማን ብለህ ትሰቃያለህ? ሁሉም

የራሱን የስልጣን መወጣጫ መንገድ እየፈለገ ነው መጠቀሚያ ያደገህ:: ቤተሰብህን አሰብ:: ልጆችህን ልታዝንላቸው ይገባል:: አንተስ ብትሆን እድሜ ዘላለምህን በእስር ተሰቃይተህ መሞትን ተመርጣለህ? መንግሥት ሙያህን ይፈልገዋል:: ደህና ቦታ እንድታገኝ ይደረጋል::»

ይነበብ ከቤት ሄደው ፍተሻ እንዳላደረጉ ከሳጅን ቁምላቸው የማወጣጫ ጥያቄ ተገንዝቧል:: የተጨበጠ ማስረጃ እጁ ላይ ቢኖር ኖሮ እፊቱ አቅርቦ ይሞግተው ነበር:: ቃላት ከማላመር ውጭ ከሌላው ጊዜ የተለየ ሀሳብ እንኳ አላገኘበትም:: ምንም ይሁን ምን እቤት ሄደው ትሩፋትን አላሰቃዩዋትም ብሎ ስለገመተ ለጊዜውም ቢሆን ሕሊናው ረፍት አገኘ::

«አመሰግናለሁ ሳጅን በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ ጊዜ ተጠርቼ አውነቱን ነግሬያለሁ:: ያልሰራሁትን ሰርቻለሁ ብዬ ለመናገር እድሜዬም ሆነ ህሊናዬ አይፈቅድልኝም:: የፈለጋችሁትን ውሳኔ ልትሰጡ ትችላላችሁ» አለ ይነበብ ኮስተር ብሎ:: ሳጅን ቁምላቸው መናደዱ ያስታውቃል:: ዐይኖቹ ፈጠው ደም የጎረሱ መሰለዋል::

«ልረዳህ አስቤ ነበር የመጣሁት:: እውነታውን መቀበል የማትችል ደረቅ ሰው ነህ:: እውነቱን ልንገርህ! ይኸ የያዝኩት ሰነድ ሕገ-መንግሥቱን በመጣስ መንግሥት ለመገልበጥና የአገር ጸጥታ ለማወክ ከተነሱ ድርጅቶች ጋር በሕብረት ልትሰራ መዘጋጀትህን የሚያሳይ ማስረጃ ነው:: ከተፈለገም የሰው ምስክር ሁሉ ማቅረብ ይቻላል:: ወንጀልህ ለሞት የሚያበቃ ነው:: ዘመንከን ሁሉ እዚሁ በስብሰህ ትቀራለህ:: ማንም አስታዋሽ አይኖርህም ቢቃ!!» አለውና ወደ በሩ በንዴት ወጣ ብሎ «ማነህ!! ዘብ ና ከነበረበት ክፍል መልሰው!!» አለ ሳጅን ቁምላቸው ጮክ ብሎ:: ዘብ ወታደሩ እያዳፋ እዚያችው ጨለማ ክፍል ውስጥ አስገብቶ ከውጭ ቆልፎበት ተመለሰ:: ይነበብ እስከ መቼ በዚች ጠባብ ጨለማ ክፍል ውስጥ ተቆልፎበት በሕወት እንደሚቆይ አያውቅም:: አቤቱታውን የሚያሰማበት ምንም ዓይነት መንገድ አላገኘም:: የሚሆነው ሁሉ የሚሆነው በሌላ ሰው ይሁንታ ነው:: ጭንቀቱንና ትካዜውን ይዞ እዚያችው ጠባብ ጨለማ ክፍል ውስጥ ተዘጋ::





## ጅማ አባ ጅፋር

ትሩፋት ረጅሙ የሕይወት ጉዞዋ መጨረሻው የት እንደሆነ ባታውቅም በብቸኝነት ተያይዛዋለች:: ባለቤቷ አብሯት እያለ በቸልታ ትመለከተው የነበረው የልጆቿን ነገር ቁጥር አንድ ትኩረት ሰጥታ የምትንቀሳቀስበት ጉዳይ ሆኗል:: የተሻለ ሕይወት እንዲኖሩ ትጥራለች:: በትምህርታቸው እንዲጠነክሩ በማቴርያልም ሆነ በሞራል አቅሟ የፈቀደውን ሁሉ እያደረገች ትገኛለች:: ልጆቿም የአባታቸው እገዛ የቀረ ቢሆንም አላሳፈሯትም:: ቴዎድሮስ ከጅማ ዩንቨርሲቲ በሕክምና ሳይንስ መመረቂያ ጊዜው ተቃርቧል:: ሚኒልክ እንኳ የዚያው የጅማ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ከሆነ ቆይቷል::

ትሩፋት ወደ ጅማ ለመሄድ ለራሷ፣ ለራሄልና ለህና ትኬት ስትቆርጥ በሐሳቧ ይነበብን እየፈለገች ነበር:: ምንጊዜም ጉዞ ላይ አብረው ሲሆኑ ልዩ ደስታ ይሰጣት ነበር:: የመጀመርያ ልጃቸው በሜዲካል ሳይንስ ሲመረቅ ለመገኘት---በዚች ለቤተሰቡ ልዩ በሆነች ቀን አብረው ወደ ጅማ እንዲጓዙ ልቧ አጥብቃ ተመኘች:: ሁሌም ጉዞ ላይ ያደርግ እንደ ነበረው በመንገድ አለመስተካከል ምክንያት የሚመጣውን የመኪና እንግልት ሁሉ ጉያው ውስጥ እቅፍ እያደረገ እንዲከላከልላት--- ስፊ ትከሻውን ሰጥቷት ትንሽ እረፍ በይ እንዲላት-- ዛሬም እንደ ሕጻን ልጅ ጸጉሯን እያሻሸ ጭኑ ላይ ጋደም በይና እንቀላፊ እንዲላት ተመኘች:: ሦስቱ ወደ ጅማ ጉዞ ጀምረው እንኳ እንደ ሁልጊዜው በአውቶብሱ መስኮት አሻግራ እየተመለከተች ተፈጥሮን አላደነቀችም:: እንደ ሁልጊዜው ተፈጥሮ ጫካ ውስጥ ገብታ አልም አላለችም:: እሷነቷ በሙሉ

«ይነበብ ው--ዴ! የት ነው ያለ--ኸው!? በምድር ወይስ በሰማይ!?» እያለ ይጮሃል!

የአባ ጅፋር ቤተመንግስት በአረንጓዴ ዛፎች ተከቦ በልምላሜ ተውቦ በኩራት ጉብ ብሎ ይታያል:: ገዢ መሬቱ ላይ ሆኖ ውቧን የጅማ ከተማ አሻግሮ ቁልቁል እየተመለከተ ታሪክ ይዘክራል:: ድሮ ከአባጅፋር ቤተመንግሥት ግርጌ የመምህራን ተቋም ነበር:: ዛሬ ጤና ኮሌጅ ተብሎ የመጀመሪያ ልጇ ቴዎድሮስ የተመረቀበት ተቋም መሆኑ ነው:: እርግጥ ነው በተቋሙ ግቢ ውስጥ ብዙ የተሰሩና የተጀመሩ ሕንጻዎች መኖራቸውን አይታለች:: ግቢው ውጭ ያሉት የኗሪው ቤቶች ግን ድሮ የነበረው የጣሪያ ቆርቆሯቸው አርጅቶ መልኩን ቀይሯል:: ምርጋቸው የተላላጠ ቋሚ እንጨቶቻቸውና ማገሮቻቸው በእርጅና ምክንያት ዘመው እንደ ነገሩ ያሉ ብዙ ቤቶች ይታያሉ:: የአዲስ ዘመንን ቤቶች አስታወሷት:: አልፎ አልፎ አዲስ የተሰሩ ግንብ ቤቶች ቢኖሩም የደቀቀውን የአብዛኛውን ሰው ቤት መሸፈን አልቻሉም:: በዚህን ያህል ዓመት ጅማ ማደግ የሚገባትን ያህል አድጋለች ከማለት ይልቅ ኮስሳለች--ደከማለች ማለቱ ይቀርባታል:: ለአዲስ ዘመን ከተማ አለማደግ ያዘነችውን ያህል ለጅማ ከተማም አዘነችላት::

የጅማ ዩኒቨርሲቲ ግቢ በጥቁር ጋዎንና ትከሻቸው ላይ ተደርቦ በወረደው ሰፊ ቀይ ተደራቢ ባኔጡ የጤና ተመራቂ ዶክተሮች አምሮባታል:: ወላጆች በደስታ ፊታቸው በርቷል:: ግቢው ውስጥ በምትገኝ አነስተኛ የኳስ ሜዳ ውስጥ ነበር የበዓሉ ዝግጅት የተደረገው:: በጅማ የአየር ፀባይ አዳራሽ ውስጥ አለመሆኑን ወዳዋለች ትሩፋት:: የቆየ እስሟ እንዳይነሳባት አየሰጋች ነበር ጅማ የመጣችው:: በትንሿ ካስ ሜዳ ውስጥ ለተማሪዎች ወላጆችና ለእንግዳ ማረፊያ እንዲሆን ሰፊ ድንኳን ተጥሏል:: ትሩፋት፣ ራሄል ምኒልክና ሀና ጥሩ ቦታ አግኝተዋል:: እንደ አለመታደል ሆኖ በዚህ ጊዜ መገኘት የነበረበት ግን እድሉን ያላገኘው አንድ ሰው ብቻ ቀርቷል---ይነበብ--- እንዲያ ለልጆቹ ስፍሰፍ የሚለው ይነበብ ታሪኩ ብቻ አልተገኘም:: ያውም በመጀመሪያ ልጁ የምረቃ ስነ--ስርዓት ላይ!

«የፎቶና የቪዲዮ ካሜራዎችን ይዞ ወደ ዝግጅቱ መግባት አይፈቀድም» የሚሉ ማስታወቂያዎች በየቦታው ተሰጥፈው ይታያሉ:: የምኒልክ የዚያው የጅማ ዩኒቨርስቲ ተማሪ መሆን ግን ለዚህ ጠቅሟል:: ከዝግጅቱ ቦታ አስቀድሞ ይዞ የመግባት እድል አጋጥሚታል:: የተመራቂ ወላጆችና ቤተሰቦች በተዘጋጀላቸው ቦታ የተገኙት ቀደም ብለው ነው:: የሜዲካል ዶክተር ተመራቂዎች ወደ ተዘጋጀላቸው ቦታ ሲመጡ እልልታው፣ ጭብጨባውና ፉጨቱ ድብልቅልቁ ወጣ:: ቴዎድሮስ ከጋዎኑና ከቆቡ ጋር ስታየው ቁመት የጨመረ መሰላት ትሩፋት:: ለነገሩ እሱም እንደ አባቱ ረጅም ነው:: ራሔልን ዞር ብላ አየቻት:: እንባ ያቆረዘዙ ዐይኖቿ እላዩ ላይ ተሰክተዋል:: በዚች ሰዓት-- በዚች ቦታ ልጁ በሜዲካል ዶክተር ጋዎን እንዲህ አምሮበት እንዲያየው የአባቱን መገኘት አሁንም አጥብቃ ተመኘች ትሩፋት::

ቴዎድሮሰ የማትሪክ ውጤቱ በሙሉ ኤ ሲሆን ይነበብ እንዴት ደስ ብሎት እንደ ነበር አፊቷ መጥቶ ድቅን አለባት:: ምድቡ አዲስ አበባ ባለመሆኑ መከፋቱን ስታይ የወቀሰችውን ደግሞ አስታወሰች::

«ምነው ይነበብ በየትኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ቢመደብ ሁሉስ አገሩ አይደል? ሲመረቅ እኮ ሳይማር ያስተማረውን ወገኑን ለማገልገል ገና በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ሁሉ መግባት ይጠበቅበታል:: ከትግል ዓለም ብንለይም ይህን ያህል እራስ ወዳድ ልንሆን አይገባም» ብላ ነበር የወቀሰችው::

«ያኔማ በአካልም በመንፈስም ያድጋል:: አሁን ግን ልጅ ነው፤ ገና አልበሰለም:: የሕክምና ትምህርት ከባድ ነው:: ከጎኑ ሆኜ ላግዘው ይገባ ነበር» ብሎ ሲመልስላት በጣም አያዘነ ነበር:: ጅማ ተቋሙ ድረስ አብሮት መጥቶ ሳምንት አብሮት ቆይቷል:: ወደ አዲስ አበባ ሲመለስ የድሮ ወዳጁ ስሆነው በንቲና ለባለቤቱ አምሳለ አደራውን ሰጥቶ ነበር::

«ደብዛው ጠፍቶ ከቀረ ስንት ጊዜ ሆነው?» አለች በውስጧ ዓመቱን ቆጥራ:: «ድፍን ስድስት አመት» አለች:: ሳታስበው በረዥሙ ተንፍሳ:: በድጋሚ ዞር ብላ ራሔልን





ተመለከተቻት:: ታለቅስ ነበር:: እሷም ዐይኗን ቆጠቆጣት:: ምኒልክ ቪዲዮ ይቀርጻል:: ሀና ፎቶ ታነሳለች:: ቴዎድሮስ ከሕዝቡ መሀል በዐይኑ ፈለጋቸው:: እጃቸውን አውለበለቡለት:: አያቸው:: ምኒልክና ሀና በአውራ ጣታቸው ምልክት እያሳዩ በአንድ ላይ <you did it bro—you did it!> አያሉ ጮሁ:: ቴዎድሮስም ሁለት እጆቹን ብድግ አድርጎ አውራ ጣቶቹን በማሳየት አጸፋውን መለሰላቸው:: አባታቸው በዚህ ስነ-ሥርዓት ላይ ተገኝቶ የልፋቱን ውጤት ለማየት ባይታደልም ልጆቹ የተመኘውን ሁነውለታል:: ሚኒልክ ከሁለት ዓመት በኋላ በኢንጅነርነት ማዕረግ ይመረቃል:: ሀና ደግሞ ከአራት ዓመት ቆይታ በኋላ ትመረቃለች::

«አውነት ግን አስከዚያ ድረስ አለ ወይም የለም ሳይባል ደብዛው እንደጠፋ ሊቀር ይሆን?» አለች ትሩፋት አሁንም ለራሷ:: የምረቃው ሰነ-ስራዓት አስኪያልቅ ድረስ ይነበብ ከዐይኗ ስር አልሄድልሽ አላት::

ጧት ጧት አገር ምድሩን አፍን ከሚያደርገው ጭጋጋማ አየሯ በስተቀር ጅማን ትወዳት ነበር ትሩፋት:: በተለይ ሩህሩሁና የዋህ ሕዝቧ መቼም ቢሆን ከልቧ አይጠፉም:: እንግዳ መቀበልና ማስተናገድ ኢትዮጵያዊ ወግና ልማድ መሆኑን ያረጋገጠችው አለመራ ያየችውን ደግነት ጅማ ተደግሞ ስታየው ነበር::

«የእነዚህ እኩይ ገዥዎች ተንኮልና ሴራ መልካም ግንኙነቱን ያልፈቱበት ውብ ሕዝብ:: ይህን አብሮ መኖር አዋቂ ሕዝብ ይኸ ሁሉ የማለያየትና የመበታተን ፕሮፓጋንዳ እየተሰራበት እንኳ ይኸው አንደ ጥንት ጧቱ ተቻችሎ አብሮ እየኖረ ነው:: እንደ ገዥዎቻችን ተንኮልና ቅስቀሳ ቢሆን ኖሮ እዚሁ አፍሪካ ውስጥ እንዳየናቸው አገሮች እርስ በእርስ ተጫርሰን ባለቅን ነበር:: በዚህ ደግ ሕዝብ ላይ ምን ያልተደገሰበት-- ምን ያልተዶለተበት የመለያየት ሴራ ነበር? በዘር መከፋፈሉ አልሆን ሲላቸው በሀይማኖቱ መጥተውበት ነበር:: ሰምቶ እንዳልሰማ ዝም ብሎ አብሮ ተስማምቶ በመኖሩ ዘልቋል» አያለች ትሩፋት ከውሰጧ ጋር የራሷን ጨዋታ ይዛለች:: የተቋሙ የክብር እንግዳ ያደረጉትን ረጅም ንግግር አንዱንም አልሰማች::

ትሩፋት ቴዎድሮስ ጅማ በመመደቡ ደስ ሲላት ምኒልክም ተደገመ:: አሁንማ ጅማ ሌላዋ ቤቷ ትመስላት ጀምራለች:: ጥብቅ ወዳጆቿ የሆኑት የአምሳለና የበንቲ ሁኔታስ እንዴት ይረሳል? እልፃ ሰቀው የሚያስተናግዱ ደጎች:: እሷና ራሔል በተመላለሱ ቁጥር በፍቅር እቅፍ ውስጥ የሚቀበሉ የዋሆች:: ቴዎድሮሰንም ሆነ ምኒልክን ልክ እንደ ልጆቻቸው ድግስ ደግሰው ያስመረቁ ወዳጆች:: ምን ይዋልላቸዋል? ለምለሚቱ ጅማ አምሳለንና በንቲን የመሳሰሉ የብዙ ደጋግ አገር ናት::

ከዝግጅቱ በኋላ ተመራቂ ዶክተሮች ሁሉ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ተቀላቀሉ:: በየቦታው ፎቶግራፍ መነሳት ሆነ:: ራሔል ከደስታዋ ብዛት የተነሳ የምትሰራውንም ሆነ

የምትናገረውን ምኑንም አታውቀውም:: መጠጥ ጠጥቶ ሞቅ ያለው ሰው ትመስላለች:: ቆሎ ቆሎ ትሰቃለች:: ቆሎ ቆሎ እየሄደች ቴዎድሮስን ታቅፈዋለች፤ ትስመዋለች:: ምኒልክንና ሀናን ደግሞ «ኑ ፎቶ አንሱን---ቪዲዮ ቅረጹን» እያለች ትወተውታለች:: ትሩፋት የመጀመሪያ ልጇ ለዚህ ወግ ማዕረግ መድረሱ ከሁሉም በላይ አስደስቷታል:: ግን ይነበብ--- ይነበብ አሁንም አሁንም በዐይነ-ሕሊናዋ እየመጣ ደስታዋን ጎደሎ አድርጎባታል:: ነፍሷ እሱኑ ፍለጋ ትቃትታለች::

ከአምሳለና ከበንቲ ቤት የመመረቂያ ድግስ ተደግሶ ነው የጠበቃቸው:: ከድግሱም በላይ የሁለቱን ደስታ ስትመለከት ትሩፋት

«ከቶ ምን ባደርግ የአምሳለንና የበንቲን ውለታ ከፍየ እዘልቀው ይሆን?» አለች በውስጧ::





## የመከነ ተስፋ

ዓለም ጎደለችም-- ሞላች---- እሷ ፈለገችም--- አልፈለገች ሕይወት ጉዞዋን ቀጥላለች:: ዓለም ራሷ በፈለገችው መንገድ በምህዋሯ ይዛት እየተሽከረከረች እየኖረች ነው ትሩፋት:: ኑሮዋ ግን መኖር ሆኖ አይሰማትም:: ዝም ብሎ በዘልማድ ይመሽ ይነጋላታል:: ቀን ይሄዳል ቀን ይመጣል:: ወራቶች ያልፋሉ ዓመታት ይቆጠራሉ:: አንዳንዴ እንደ እንስሳ ዝም ብላ በደመነፍስ የምትጓዝ ይመስላታል:: ምንጊዜም ጎዶሎነት ይሰማታል:: ለትሩፋት ሁሉም ነገር ሙሉ አይደለም:: ጎደሎ ነው--ጎደሎ ብቻ!! ፖለቲካው ጎዶሎ---ኢኮኖሚው ጎዶሎ-- ማኅበራዊ ኑሮው ጎዶሎ--- አገሪቷ ራሷ ጎዶሎ--- የሷ የራሷ የግል ሕይወት ጎዶሎ-- እንዴት ብሎ ሙሉነት ይሰማት? ደከሟት ያልተወችው--- ሰልችቷት ወይም ተስፋ ቆርጣ እርፋ ያልተቀመጠችበት ጉዳይ ውስጧ ተቀብሮ ሁሌም እረፍት ይነሳታል:: ይከነከናታል---ያምሰለስላታል--- ኑሮዋን ሁሉ ጎደሎ እንዲሆን አድርጎባታል:: ይነበብ!! ድንገት ከቤቱ ወጥቶ ባላሰበችውና ባልጠበቀችው ጊዜና ሁኔታ የውሃ ሽታ ሆኖ የቀረው ይነበብ!! መኖሩ ወይ አለመኖሩ አሁንም ድረስ ገና እንቆቅልሹ ያልተፈታው ይነበብ....

እቤቱታዋን ያላሰማችበትና ያላንኳኳችው የመንግሥት መሥሪያ ቤት የለም:: ሲሆንማ ከቤቱ በሰላም ወጥቶ የጠፋ ዜጋውን የማፈላለግና የደረሰበትን የማሳወቅ ግዴታ የእንድ መንግሥት ነኝ ባይ ተቋም ኃላፊነት ነበር:: እገሪቱ ለዚህ አልታደለችም:: ለዜጋው የሚቆረቆር ሳይሆን ቀን ከሌት ስልጣኑ የሚጎለብትበትንና የግዛት ዘመኑ የሚራዘምበትን ከሚያስብ መንግሥት ጥላ ሰር ትገኛለች:: ለሕዝብ ሰላም፣ ለእገር እንድነትና እድገት ከመትጋት ይልቅ ለሰልጣን ብቻ ከሚሯሯጥ መንግሥት መዳፍ ሥር ወድቃለች:: በዘመነ ደርግ ጊዜ የወደቀበትን ታውቅ ነበር:: ስንቅ እቀብላለች:: መቀየሪያ ልብስ መስጠት ትችል ነበር:: አሁን ግን ይህንን የማድረግ መብት እንኳ አላገኘችም:: ልጆቿ አባታቸውን የማየትና የመጠየቅ መብት ተነፍገዋል:: ያለጥፋታቸው በአባት ናፍቆት እንዲቀጡ ተፈርዶባቸዋል::

«ግፍ ነው!! የግፍ ግፍ!! መጨረሻ የሌለው ከፋት! መለኪያ---መስፈሪያ-- ልክ የሌለው የጭካኔዎች ሁሉ ጭካኔ! » ትላለች ትሩፋት ይነበብን ባሰበች ቁጥር:: «እቤት!! እንደዋዛ ወጥቶ ከቀረ ስንት ጊዜ ሆነው?» ከእሷ ተለይቶ የተሰወረባቸውን እመታት ታሰላለች:: «እግዜር ሳይደግስ አይጣላም» እንዲሉ ለመኖሯ ልጆቿ ምክንያት ሆኗት:: ምንም ቢሆን ውስጧን ደስ የሚለው ልጆቿ የደረሱበትን ደረጃ ስታስብ ነው:: እሷ ራሷ ከአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ይዛለች:: ይህን ያደረገችው እንደ በፊቱ ለትምህርትና ለእውቀት ጓጉታ አልነበረም:: ከይነበብ መሰወር በኋላ ሁሉም ነገር እንዳልነበር ሆኖባታል:: ግን ለሁለት ነገሮች ሰትል ነበር ለመማር የወሰነችው:: አንድም ለልጆቿ መልካም እርእያ ሆና ለመገኘትና ሞራላቸውን ለመገንባት ስትል:: ሁለተኛው ምክንያቷ ደግሞ ለትንሽ ዓመታትም ቢሆን ራሷን መደበቂያ ያገኘች መሰሏት ነበር:: ቀን በሥራ ማታ

በትምህርትና በጥናት ከጠመደች ይነበብን የምታስታውስበትን ጊዜ ያሳጠረች መሰሏት ነበር:: እንዳሰበችው ግን አልሆነም::

መቼም ጊዜ ይነበብ ከአዕምሮዋ ወጥቶ አያውቅም:: ሳታስታውሰው ውላ ያደረችበት ቀን በፍጹም የለም:: ከጥናቷ ወይም ከስራዋ ማሀል የሚያስጨንቅና የሚያስፈራ ሐሳብ ድንገት ብልጭ ይልባታል:: ትደነግጣለች:: ከምድር በታች በተሰራ ቀዝቃዛና ጨለማ እስር ቤት ውስጥ ተጥሎ--- ፀጉሩ ሸብቶ--- አካሉ ደክሞ--- ከብርሀን እጦት የተነሳ መልኩ ገርጥቶ--- ዐይኑ ደክሞ--- ሰውነቱ አልቆ ምንምን ብሎ ከስቶ--- አጥንቱ ብቻ ገጦ ይታያታል:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የጊዜውን እርዝመት ታስብና «ይኖራል» የሚለው ተስፋዋ ጨርሶ ከውስጧ ብን ብሎ ይጠፋል:: በሕይወት የሚገናኙ አይመስላትም--- እና ታዝናለች--- በጣም ታዝናለች:: የራሷን መኖር እንኳ አትፈልገውም:: ስለ ይነበብ መኖር ወይ አለመኖር ቁርጥ ያለ አቋም ሳይኖራት እንዲሁ እየዋለለች ባለችበት ሰዓት በኢትዮጵያ ምድር አንድ አዲስ ተስፋ ሰጭ ክስተት ተከሰተ:: ምርጫ 97----

******

ከ1966 ዓመተ ምህረት ወዲህ የፖለቲካ ነፋስ በኢትዮጵያ ምድር ዳር እስከ ዳር የነፈሰው በዘጠና ሰባት ነው:: የለውጥ ትኩሳት ዳግም በኢትዮጵያ ምድር ናኘ:: ሥልጣን ላይ ያሰው የወያኔ ኢህአዴግ መንግሥት «ትክክለኛ የሕዝብ ምርጫ ለማካሄድ ቆርጬ ተነስቻለሁ» አለ:: «ሥልጣንን ኮሮጆ ውስጥ አገኝታለሁ እንጂ በመሳርያ ኃይል በጉልበት ይዣት አልቀርም!» ሲል ፎከረ:: «ተፎካካሪ ድርጅቶች ሁሉ ያለፍርሀት ኑ ቅረቡኝ በምርጫ ተወዳደራችሁ ከተመረጣችሁ እሰየው ስልጣኔን አስረክባለሁ ለዚህም የዓለም ሕዝብ ይታዘበኝ» ብሎ በዲሞክራሲ ስም ማለ--ተገዘተ:: በመገናኛ ብዙሀን በከፍተኛ ቅስቀሳ የሕዝብን ልብ ሁሉ አማለለ:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚመርጠው መሪ ሲመራ ቀኑ ደረሰ:: በሰላማዊ መንገድ በሕዝብ ድምጽ የመንግሥት ለውጥ ማድረግ እንደሚቻል ሁሉም አመነ:: የለውጥ መንፈስ በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ እንደ ገና ነፍስ ዘራ::

በአገሪቱ በሙሉ ከተከሰተው የፖለቲካ ትኩሳት ባሻገር ትሩፋት ሌላም ተጨማሪ የግሏ የሆነ ውስጣዊ ፍላጎትና ምኞት ነበራት:: አንደኛው ምኞቷ ይሄ የተፋፋመው ፖለቲካ እውነት ሆኖ በሕዝብ ይሁንታና ምርጫ መንግሥት ከተመሰረተ--- ያ የታገለችለት ዓላማ ግቡን መታ ማለት ነው:: ሕዝብ መሪዎቹን መምረጥ ከቻለ--- ከኃይለሥላሴ ዘውዳዊው መንግሥት ጀምሮ ሲታገል የኖረው ያ አልፍ እአላፍ ወጣት የተሰዋለት--- ያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጆቹን የገበረለት ሕዝባዊ መንግሥት ተመሰረተ ማለት ነው:: ይነበብ እድሜ ልኩን ለልጆቹ ሲያወርሳት የሚፈልጋት ኢትዮጵያ ተፈጠረች ማለት ነው:: ሌላውና ሁለተኛው ደግሞ የእሷ የግሏ ጉዳይ ነው:: የትዳሯ ጉዳይ:: የልጆቿ አባት ጉዳይ:: ምናልባት ይነበብን ከማይታወቅ ከአንዱ እስር ቤት ውስጥ ወርውረውት በሕይወት ካለ





ሕዝብ የመረጠው መንግሥት ሲቋቋም—ማን ያውቃል? ከእስር ተለቆ ይገናኙ ይሆናል:: በሕይወት ካልኖረ ደግሞ ቁርጧን ታውቃለች:: ከዚያ በኋላ የእሷ ድርሻ በግፈኞችና በስልጣን ጥመኛ ሴራ በስውር ተይዞ--- በስውር ተሰቃይቶ--- በስውር እንዲሞት የተፈረደበትን የይነበብን ታሪክ ይፋ ማውጣት ይሆናል:: በአስተሳሰብ ልዩነት ምክንያት ቤተሰብ እንዳያየውንና እንዳይጠይቀው ጨካኝ ውሳኔ የተፈረደበትን የይነበብን ታሪክ ለሕዝብ ይፋ የማድረግ አጋጣሚ ይፈጠርላታል:: በአገራቸው ላይ እሷ ባለቤቷን የመጠየቅ--- ልጆቿ የሚወዱትን አባታቸውን የማየት መብት ተነፍገው በናፍቆት ሲንገበገቡ ኖረዋል:: ከበደል ላይ በደል ደርሶባቸዋል:: ባልሰሩት ወንጀል አለከፊ ቅጣት ተፈጽምባቸዋል:: እሷና ልጆቿ የደረሰባቸውን ግፍና መከራ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳታሰማ አፏ የተለጎመበት ይኸ ክፉ ዘመን ያበቃል ማለት ነው:: ምርጫ ዘጠና ሰባት ለእሷ ሁለት ወርቃማ እድሎችን ይዞላት እንደ መጣ ነው የቆጠረችው::

«ይሄ ሁሉ ሥራ ሲሰራ የት ነበርኩ» ስትል ራሷን ጠየቀች ትሩፋት:: በዚህ በተጋጋለ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ ባለመሆኗ ራሷን ወቀሰች:: በክርክሩ ወቅት በቴሌቪዥን መስኮት እስኪታያቸው ድረስ እንዲህ የተጠናከሩ ድርጅቶች መኖራቸውን ባለማወቋ ተቆጨች::

«የዳር ተመልካች መሆን አልነበረብኝም:: ይነበብ ይናገረው የነበረው ከልብ የመነጨ የለውጥ ፍላጎት ቢኖረኝ ኖሮ ቀደም ብዬ የዚህ ለውጥ ሙሉ ተካፋይ መሆን እችል ነበር» ስትል ተፀፀተች::

******

በሕዝብ ልብ ውስጥ ሙሉ ተስፋ ተጥሎበት የነበረው ምርጫ ዘጠና ሰባት ልክ እንደ እለፉት አብዮቶች ሁሉ መክኖ ቀረ:: ሕዝብ ለሦስተኛ ጊዜ ሊጎናጸፈው የነበረውን ድል በጠራራ ፀሐይ ተነጠቀ:: ተቀጣጥሎ የነበረው ሰላማዊ በሆነ መንገድ በሕዝብ ድምጽ መንግሥትን የመለወጥ የዲሞክራሲ ጭላንጭል ተዳፈነ:: «እንከን የለሽ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ ቆርጬ ተነስቻለሁ» ብሎ ሲምል ሲገዘት የነበረው የወያኔ መንግሥት ቃሉን ሲያጥፍ መሽቶ አልነጋም:: ይባስ ብሎ «ድምጻችን ይከበር» ብለው ባዶ እጃቸውን በወጡ ዜጎች ላይ ቃታ ስቦ ደም ሲያፈስ ለቀሪ የታሪክ አሻራው አላዘነም:: በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን እንዲህ ያለ ኢ-ዲሞክራሲያዊ ድርጊት በሕዝብ ላይ ሲፈጽም የዓለም ሕዝብ ትዝብት ለገዥው መንግሥት ከአቁብ የሚቆጠር አልነበረም:: ገና የመከራ ጉዞዋ የአላለቀላት መከረኛ አገር..... ኢትዮጵያ ዳግም በንጹህ ልጆቿ ደም ታጠበች::

ትሩፋት ዛሬም እንደ ወጣትነት ጊዜዋ-- እንደ ዚያ የትግል ዘመኗ «ድምጻችን ይከበር» ብለው ከወጡ ሰልፈኞች መካከል ነበረች:: እነዚያን ሁለት ወርቃማ ተስፋዎቿን ለማስፈጸም:: ከዚያ ሁሉ የኢጋእዚ ተኩስ ተርፋ ዛሬ በሕይወት መኖሯን ስታስበው እረፍት

በሌለው ግማሽ ምዕተ ዓመት በዘለለው እድሜዋ ውስጥ «ሰጉድ የጎሰተኝ!» ትላሰች ባግራሞት::





## መቃብር ደርሶ መልስ

ሐምሌ 24/ 1999

ውሃ ሰሚያዊ አይሉት ውሃ አረንጓዴ ብቻ ዐይን ያነሆልላል:: ልብን በሀሴት ይሞላል:: ሲያዩት ውለው ሲያዩት ቢያድሩ ውበቱ አይጠገብም:: እንዲያው ዝም ብሎ ያሰደምማል—! ያለገርማል---! አትላንቲክ ውቅያኖስ:: ማዕበሉ እንደ ተራራ ቆሞ መልሶ ይወድቃል:: ሞገዱ ኃይለኛ ነው:: ውሰጡ ያለውን ሁሉ ያንገላታል:: ዳር ሆኖ ለተመለከተው ግን ግሩም ድንቅ ተፈጥሮ! ያሰኛል:: ሌላ ነገር እንዲያስቡ እድል አይሰጥም:: ቀልብን ቆንጥጦ ይይዛል::

ዐይኗን በረጅሙ ለቃ ዳርቻው የማይታየውን ውቅያኖስ አሻግራ ትመለከታሰች:: ልቧ ከሞገዱ ጋር አብሮ እየተነሳ ይወድቃል:: የተጓዘችውን ውጣ ውረድ የበዛበት የሕይወት ጉዞዋን እየለካች--- ገና ያልተቋጨ ጉዞዋን ደግሞ እየገመተች:: እንዳንዴም እዚህ አትላንቲክ ውቅያኖስ ዳርቻ ላይ የመገኘቷ አጋጣሚ እየገረማት!-- ህልም ህልም አንጂ አውን አውን አልመስል ብሏት--- ግን እውነት ነው:: እሷ--- ራሷ ናት--- ትሩፋት::

ምድረ ነጭ ያልተለበለበ ሸከላ የመሰለ ገላውን ላንቃዋን እስከ መጨረሻው ለከፈተችው ፀሐይ ሰጥቷል:: ከውቅያኖሱ ዳርቻ አሸዋው ላይ ተሰጥቷል:: ነጫጭባ ገላውን ለማጠየም:: ድንገት ለተመለካታቸው ውሃ ሙላት አምጥቶ የተፋው አባዛ አሳ ይመስላሉ:: ሕጻናቱ ይሯሯጣሉ:: የአሸዋ ቤት እየገነቡ ያፈርሳሉ:: የአሸዋ ተራራ ይቆልላሉ--- ይንዳሉ:: የአሸዋ ቤት መገንባቱና ተራራ መቆለሉ ሲሰለቻቸው እየተሯሯጡ ውቃያኖሱ ዳርቻ ላይ ሄደው ይቆማሉ:: ፈራ ተባ እያሉ በኃይለኛ ሞገድ የሚታመሰውን ውቅያኖሰ ይመለከታሉ:: ትንሽ ቆይተው ደፈር ሲሉ ዳሩ ላይ ገብተው ይንቦጫረቃሉ:: የፈረንጅ ትንንሽ ልጆች ደስ ይላሉ:: ምንስ የልጅ የሚያሰጠላ ባይኖረውም::

ፈረንጆች መዝናናት ያውቁበታል:: ይቺ ቀን ታልፋለች የተባሉ ይመስል እያንዳንዷን ቀን በደስታ ለማሳለፍ የማያደርጉት ጥረት የለም:: አንዳንዱ ትንሽ ዝርግ ጣውላ በመሰሰች ነገር ያን ማዕበሉ የሚያሰፈራ ውቅያኖስ እንደ ፈረስ ይጋልበዋል:: ማዕበሉ ቁጣው ሲያይል እላይ አጉኖ ታች ይደፍቃቸዋል:: እንደ ትሩፋት አይቶ ስማያውቅ ሰው ዘግጠው የቀሩ ሁሉ ሊመሰሰው ይችላል ግን ብዙም ሳይቆዩ በሌላኛው የሞገዱ ጫፍ ብቅ ይላሉ:: አደጋ ተከላካይ ቃፊሮች በመኪና እየተዘዋወሩ ሰፊው ውቅያኖስ ላይ ዐይናቸውን ጥሰው አካባቢውን ይቆጣጠራሉ:: ሻርክ መምጣቱን የሚያሳውቁበት የማስጠንቀቂያ ፊሽካቸውን ለሰከንድ ከአፋቸው ላይ አያነሷትም:: ለሕይወት አስጊ የሆነ ኃይለኛ ማዕበል ወይም ነጎድጓዳዊ መብረቅ የሚመጣ ከሆነ ከወዲሁ ያሰጠነቅቃሉ:: ለሰው ልጅ ሕይወት የሚደረገው ጥንቃቄ ያስቀናል:: ከዚህ ሁሉ ትርኢት ባሻገር ምድርን በሙሉ የያዘ መሰሎ